4

ትምህርት

መንፈስ ቅዱስ
ጠቢብ አስተዳዳሪ

ኢየሱስ ለተከታዮቹ "እኔ ብሄድ ይሻላችኋል" (ዮሐ 16:7) በማለት ለምን እንደነገራቸው አስበህ ታውቃለህ? ይህንን ያለው በስብዕናው ምክንያት ውሱን ስሰነበረና በአንድ ጊዜ አንድ ቦታ ብቻ ስለሚገኝ ነበር። ይሁን እንጂ መንፈስ ቅዱስ በእርሱ ምትክ በሚመጣበት ጊዜ በምድር ሰሚቆይበት ወቅትም ሆነ ሊሰራ ሰሚችሰው ሥራ ውሱንነት እንደማይኖረው ያውቃል።


ስለሆነም በመንፈስ ቅዱስ አማካይነት እግዚአብሔር እኛን ሰሥራ መመደብ ብቻ ሳይሆን ከእኛ ጋር ይሆናል አገልግሎታችንንም እንድንፈጽም ያስቸለናል። ከዚህም በላይ በእኛ ሕይወት ውስጥ መኖሪያውን በማድረግ ሰመንፈሳዊ ሕይወታችን የሚያስፈልጉንን የግል ምሪት፣ ሕብረት፣ መጽናናትና ብርታትን ይሰጠናል።

ቀደም ብለን በተመለከትናቸው ትምህርቶች ለሰዎች መቤዠት እግዚአብሔር የሰጠውን ትኩረት አይተናል። ባለፈው ትምህርታችን ሰው ሰመሆን ራሱን ዝቅ እስከሚያደርግ ድረስ ከርስቶስ እያንዳንዱን ሰው እንደወደደ ተመልክተናል። አሁን ወደ መንፈስ ቅዱስ ስንመሰስ ያንኑ ለሰዎች ያለውን ፍቅርና እነዚያኑ ድንቅ የሆኑ የአካላዊነት መታወቂያ ባህርያት እናስታውሳለን።

ይህንን ትምህርት በምታጠናበት ጊዜ የመንፈስ ቅዱስ ማንነትና ሥራው ከመቼውም ጊዜ ይልቅ ታሳቅ ትርጉም እየሰጠህ ወደ አንተ በሙሳት እንዲቀርብ ጸሎታችን ነው። ይህም በሚሆንበት ጊዜ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለህ የግል ግንኙነት ያድጋል፤ ሰሌሎች በምትሰጠውም አገልግሎት ዕድገት ተንበባርቆ ይታያል (2ቆሮ 3:18)።

የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- የመንፈስ ቅዱስ መለኮትነት
- የመንፈስ ቅዱስ አካልነት
- የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት



የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህንን ትምህርት ስታጠናቅቅ የሚከተሉትን ማድረግ መቻል ይኖርሃል።

- የመንፈስ ቅዱስ መሰኮትነትን የሚገልጹ መረጃዎችን ማቅረብ።
- መንፈስ ቅዱስ ያሉትን መሠረታዊ አካላዊ ባህርያት መዘርዘርና አስፈላጊነታቸውን መግለጽ።
- ከማያምኑ ሰዎች፣ ከአማኞችና ከቤተክርስቲያን ጋር መንፈስ ቅዱስ ያሰውን አገልግሎት መግለጽ።
- በዕሰታዊ የክርስትና ኑሮህ የመንፈስ ቅዱስን ፍሬዎች ማፍራት።

የትምህርቱ መመሪያዎች

1. በክፍሰ ትምህርት 1 የተሰጠውን መመሪያ ተከተል። ትምህርቱን በሚገባ ለመረዳት ጠቃሚ ስለሆኑ በትምህርቱ ውስጥ የተካተቱትን ጥቅሶች በመጽሐፍ ቅዱስህ ውስጥ አግኝተህ ማንበብህ በጣም አስፈላጊ ነው።

2. በትምህርቱ በስተመጨርሻ የቀረቡትን የሙከራ ፈተናዎች ከሰራህ በኋላ የሰጠኸውን መልሶች አመሳክር ።

3. ከትምህርት 1-4 የቀረቡትን ትምህርቶች ከልሳቸው።

የመንፈስ ቅዱስ መለኮትነት

በክፍለ ትምህርት 1 ስለ እግዚአብሔር ማንነት ለንመለከት ሊታወቅ ወይም ሊገለጽ የሚችል ማንነት እንዳለው ገልጸን የሚከተሉትን ነጥቦች ተገንዝበናል፦

1. እግዚአብሔር መንፈስ ነው።
2. አንድ አምላክ ነው።
3. አካላዊ ነው።
4. ሥሉስነት ያለው አምላክ ነው
5. ዘላለማዊ ነው።
6. የማይለወጥ ነው።

እነዚህ ልዩ የእግዚአብሔር መታወቂያዎች ለአብ፣ ለወልድና ለመንፈስ ቅዱስ በእኩል ደረጃ ሊጠቀሱ እንደሚችሉም ተመልክተናል። ሦስቱ አካላት በክብር እኩል ናቸው፣ የተገናኙትም ማርማ የጋራና ዘላለማዊም ነው። በእግዚአብሔር ሕልውና ያሉት አካላት እነዚህን ገጽታዎች ስለሚጋሩ ስለ ክርስቶስ በተመለከትንበት ጊዜ በድጋሚ አላየናቸውም፣ የመንፈስ ቅዱስንም ማንነት በምናጠናበት ጊዜ በሙላት በድጋሚ የምናቀርብበት ምክንያት አያኖርም። ይሁን እንጂ መንፈስ ቅዱስ በእርግጥ አምላክ የመሆኑንና የአካልነት ልዩ የመታወቂያ በህርያት እንዳሉት በድጋሚ በመጠኑ ለማጠናከር እንፈልጋለን። በቅድሚያ መለኮትነቱን እንመለከታለን።

የመንፈስ ቅዱስ መለኮትነት በማንነት መታወቂያዎቹ፣ በሥላሴ ውስጥ ካሉት ሌሎች አካላት ጋር ባለው ዝምድና፣ በተሰጡት መለኮታዊ ስሞችና በሚያከናውናቸው ሥራዎች የተረጋገጠ ነው።

የመለኮታዊ ማንነቱ መታወቂያዎች

ዓላማ 1 የመንፈስ ቅዱስን የመለኮት ማንነት መታወቂያዎችን ለይቶ ማወቅ

መንፈስ ቅዱስ የመለኮት ማንነት መታወቂያዎች አሉት። ለምሳሌ ያህል መንፈስ ቅዱስ ዘላለማዊ ነው። "ዘላለማዊ" ማለት "ከጊዜ አንፃር ጅማሬና ፍጻሜ የሌለው ወይም ያለገደብ የሆነ" ማለት ነው። ስለሆነም ይህ የእግዚአብሔር መታወቂያ ባህርይ ነው። ዘመንፈስ ቅዱስ ምሪት የዕብራውያንን መልእክት የጻፈው መንፈስ ቅዱስ ዘላለማዊ ነው ብሏል (ዕብ 9:14)። በዚህ ላይ ዘላለም ተብሎ የተጠቀሰው ቃል የእግዚአብሔር አብንና የእግዚአብሔር ልጅ የኢየሱስ ክርስቶስን ዘላለማዊነት ለመግለጽ የዋለው ነው።

መንፈስ ቅዱስ የሚከተሉት መታወቂያ ባህርያትም አሉት።

❶. በአንድ ጊዜ በሁሉም ሥፍራ ይገኛል። መዝሙረኛው ዳዊት እንዲህ ሲል ተናግሮ ነበር "ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ? ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ" (መዝ 139:7-10)።

❷. ሁሉን አዋቂ ነው። ይህንን የመለኮት ማንነት መታወቂያ ለቆሮንቶስ አማኞች በገለጸበት ጊዜ ጳውሎስ ". . . ከእግዚአብሔር መንፈስ በቀር ለእግዚአብሔር ያለውን ማንም አያውቅም" (1ቆሮ 2:10-11) በማለት በማለተዋል ተናግሯል። ከዚህም በተጨማሪ የእግዚአብሔርን ሃሳብ የሚያውቀው የእግዚአብሔርንም ፈቃድ ያውቃል። በዚህም ምክንያት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንድንጸልይ ያስችለናል (ሮሜ 8:26-17)።

❸. ሁሉን ቻይ ነው። ይህም ማለት እግዚአብሔር የፈቀደው ሁሉ ያለምንም ገደብ እንዲፈጸም የማድረግ ኃይል አለው (ሉቃ 1:35፣ የሐዋ 1:8)።

(1). ከዚህ ቀጥሎ ከ1-4 የቀረቡትን የማንነት መታወቂያዎች ከሀ-መ ከቀረቡት ትክክለኛ መግለጫዎች ጋር በማቀናጀት ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የሚዛመዱትን እያንዳንዳቸውን የመለኮት ማንነት መታወቂያዎች ለይተህ አሳያቸው።

1. ሁሉን ቻይነት
2. ሁሉን አዋቂነት
3. በሁሉም ስፍራ መገኘት
4. ዘላለማዊነት

ሀ. ከጊዜ ጋር በተገናዘበ ሁኔታ ገደብ የለሽ ወይም የማይወሰን።
ለ. በሁሉም ሥፍራ እስከሚገኝ ድረስ ዓለማትን ሁሉ የመሙላት ችሎታ።
ሐ. ያለ ምንም ገደብ እግዚአብሔር የፈቀደውን ሁሉ እንዲያደርግ የሚያስችለው የተለየ የማንነት መለያ።
መ. ወሰን የሌለው እውቀት።

የመለኮታዊ ማንነት መታወቂያ መጠሪያዎች

ሐዋርያው ጴጥሮስ አታላዩን ሐናንያን በተናገረው ጊዜ ሐናንያ በመንፈስ ቅዱስ ላይ ሲዋሽ በእግዚአብሔር ላይ ዋሽተሃል ማለቱን ስናስተውል እንደነቃለን (የሐዋ 5:1-4)። በዚህም መንገድ ሐዋርያው ጴጥሮስ መለኮትነትን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያያይዘዋል። ጌታ በሚሆን በመንፈስ ቅዱስ ወደ ክርስቶስ መልክ እንለወጣለን (2ቆሮ 3:17-18) የሚለውን እውነት በመግለጽ ሐዋርያው ጳውሎስም ይህንኑ ያረጋግጣል። በጳውሎስ ዘመን ጌታ ተብሎ የሚጠራው መለኮት ብቻ ነበር። እንደ እውነቱ ከሆነ በዚያን ዘመን የነበሩ የሮምና የግብጽ ገዢዎች በደፋ በራሳቸው ላይ የመለኮትነትን ክብር እስከወሰዱ ጊዜ ድረስ ሕዝቦቻቸው "ጌታ" በሚለው መጠሪያ እንዲጠሩአቸው አይፈቅዱላቸውም ነበር። ይህን መላዩ አቀራረብ

ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስን ጌታ ብሎ የመጥራቱ እውነት መለኮትነቱን መቀበሉን ያረጋግጣል።

(2). ከሚከተሉት የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ለመንፈስ ቅዱስ መለኮትነት ማረጋገጫ ሊሆኑ የሚችሉት የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ ጌታ መሆኑን ጠቅሷል።
ለ. ኢየሱስ መንፈስ ቅዱስ አጽናኝ መሆኑን ጠቅሷል።
ሐ. ኢሳያስ ስለ ጌታ መንፈስ ጠቅሷል (ኢሳ 11:2)።
መ. ጴጥሮስ በመንፈስ ቅዱስ ላይ መዋሸት በእግዚአብሔር ላይ መዋሸት መሆኑን ገልጿል።

በመለኮታዊ ማንነቱ የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች

ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የመንፈስ ቅዱስን መለኮትነት በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ይገልጹታል። ከዚህ በታች በቀረቡት የመጀመሪያዎቹ ሁለት ምሳሌዎች የመንፈስ ቅዱስ መለኮትነት ከሌሎቹ የሥላሴ አካላት ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች አማካይነት ተገልጿል። እዚህ ላይ በአካላቱ መካከል የሚታይ ወይም ግልጽ የሆነ እኩልነት እንደዚሁም መሰኮትነት እንመለከታለን።

❶. ማቴ 28:19 - *የጥምቀት ሥርአት* "በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው . . ."

❷. 2ቆሮ 13:14 - *የሐዋርያው የሰንብት ቃል* "የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ፀጋ የእግዚአብሔርም ፍቅር የመንፈስ ቅዱስም ሕብረት. . ."

❸. 1ቆሮ 12 - በዚህ ምዕራፍ ቤተክርስቲያንን እንደ ክርስቶስ አካል (ቁ. 27) እንመለከታለን። ለዕድገቱዋ አስተዋጽኦ ያደርጉ ዘንድ እግዚአብሔር በዚህች ቤተ ክርስቲያን ላይ አገልግሎት መድቧል። ለዚች አካል በሉአላዊ ሥልጣኑ ስጦታዎችን የሚያከፋፍለው መንፈስ ቅዱስ ነው (ቁ. 11) ።

እዚህ ላይ የምንመለከተው የእርስ በርስ ግንኙነት ተገቢ መግለጫ ሊያገኝ የሚችለው በተባረከው የሥላሴ ሕልውና እያንዳንዱ አካል በሚኖረው ሙሉ የእኩልነት መሠረት ላይ ነው። ይህንን መሠረት በማድረግ ብቻ ነው መንፈስ ቅዱስ በሉአላዊነቱ እንደፈቀደ ስጦታዎችን የማከፋፈል መለኮታዊ ሥልጣኑን ተግባራዊ የሚያደርገው (2ቆሮ 12:4-6፣ 11)።

❹. የሐዋ 28:25-28 በኢሳ 6:9-10 ላይ ያሰውን ቃል የተናገረው መንፈስ ቅዱስ ነው በማለቱ ጳውሎስ በዚህ ጉዳይ ላይ ጠቃሚ መረዳት እንድናገኝ ረድቶናል። በነቢዩ በኢሳይያስ መሠረት በምዕራፍ 6:9-10 ላይ የተጠቀሰውን ቃል የተናገረው እግዚአብሔር ነው። እነዚህን ሁለት ክፍሎች አነፃፅራቸው።

መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር አብ ተወካይ ወይም ሥራ አስፈጻሚ በመሆኑ ይህ ንፅፅር መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር አብ ሥፍራ በመሆን በምድር ላይ ሥራውን እንደሚያከናውን ያመለክታል። ይሄው ሁኔታ በሚከተሉት ምሳሌዎች በይበልጥ ግልጽ ሆኖ ይታያል። ስዎችን ወደ ክርስቶስ ያቀርባቸዋል (ዮሐ 6:44)፣ እውነትን ይገልጻል (ዮሐ 14:26፣ 16:13) ደግሞም ምሪትን ይሰጣል (ሮሜ 8:14)።

❺. ዘፍ 1 የእግዚአብሔር አብ፣ የወልድና የመንፈስ ቅዱስ የተቀናጀ ተግባር እግዚአብሔር ሰውን "በመልካችን እንደ ምሳሌያችን እንፍጠር" ብሎ በተናገረበት በዘፍ 1:26 ላይ ይታያል። ቡትምሀርት 1 እንደተመለከትነው በብዙ ቁጥር ተውላጠ ስም መነገሩ በእግዚአብሔር ሕልውና ዘንድ ከአንድ በላይ የሆኑ አካላት እንዳሉ ያመለክታል። ይህ የሚያስተላልፈው መልእክት ሦስቱም በመፍጠር ሥራ ውስጥ ተሳታፊዎች እንደነበሩ ነው።

እነዚህ ጥቅሶች መንፈስ ቅዱስ ከሥላሴ ሌሎች አካላት ጋር ያለውን ግንኙነት ከአብና ከወልድ ጋር እኩል አምላክ መሆኑንም ያስረዳሉ።

(3). ከዚህ ቀጥሎ ከተራ ቁጥር 1-4 የተመለከቱትን ማስረጃዎች ከሀ-ሠ በቀረቡት የእግዚአብሔር ቃል ክፍሎች ውስጥ ከቀረቡት የመንፈስ ቅዱስ መሰኮትነት ጋር አቀናጃቸው።

1. በሥነ-ፍጥረት ወቅት በእግዚአብሔር ሕልውና ውስጥ ከአንደ በላይ አካላት መኖራቸው።
2. የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በምድር።
3. መለኮታዊ ሉአላዊነት።
4. በእግዚአብሔር ሕልውና ውስጥ ባሉት አካላት መካከል ያለው መለኮታዊ እኩልነት።

ሀ. የሐዋ 28:25-28 እና ኢሳ 6:9-10
ለ. 1ቆሮ 12
ሐ. 2ቆሮ 13:14
መ. ዘፍ 1
ሠ. ማቴ 28:19

የመንፈስ ቅዱስ አካልነት

ዓላማ 2 የመንፈስ ቅዱስን ዋና ዋና አካላዊ ገጽታዎች ለይቶ ማወቅ

አበይት አካላዊ ገጽታዎች

በትምህርት 1 ላይ ሦስት አካላዊ ገጽታዎች እንደነበሩ አስተውሰናል፦

1. *አውቀት* (የማስብ ችሎታ)
2. *ስሜታዊነት* (ስሜትን የማገናዘብ ችሎታ)
3. *ፈቃድ* (ውሳኔን የማድረግ ችሎታ)

ስለ መንፈስ ቅዱስ የሚጠቅሱትን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በመመርመር እነዚህ የማንነት መታወቂያዎች ከርሱ ጋር እንዴት እንደሚገናዘቡ እስቲ እንመልከት።

መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ የመንፈስ ቅዱስን አካላዊነት በተመለከተ ይነግረናል። ጥበብ በተሞላው ሁኔታ በመንፈስ ስለምንኖረው ኑሮ ሐዋርያው ጳውሎስ "የመንፈሰ አሳብ" የሚለውን በመጥቀስ ያጠቃልለዋል (ሮሜ 8:27)፤ ይህም የመንፈስ ቅዱስን የማስብ ችሎታ ለይቶ ያሳያል። ሐዋርያው በስሜት የመነካትን ጉዳይ ከመንፈሰ ቅዱስ ጋር ያያይዘዋል (ሮሜ 15:30)። ይህም ማለት የመንፈስ ቅዱስን ሰሜት የማገናዘብ ችሎታን ጠቅሷል ማለት ነው። ከዚህም ጋር በተያያዘ ሁኔታ የፍቅር ስሜት እንደሚሰማውና ስሜቱን የመግለጽ ችሎታ እንዳለው ማመልከት ማለት ነው። የመንፈስ ቅዱስን ሉአላዊ ተግባር በሚመለከት ሐዋርያው ለቆሮንቶስ አማኞች ሲናገር መንፈስ ቅዱስ እንደወደደ ለአማኞች ስጦታዎችን መስጠቱ (1ቆሮ 12:11) የራሱ ፈቃድ እንዳለው ይገልጻል። እነዚህ ክፍሎች መንፈስ ቅዱስ አካላዊ ባህርያት እንዳሉት ያመለክታሉ።

(4). በሚከተለው መልመጃ ከ1-3 የቀረቡትን የአካል ባህርያት ከሀ-ሐ ካለው ትክክለኛ ትርጉም ወይም መግለጫ ጋር አዛምዳቸው።

1. ዕውቀት 2. ስሜታዊነት 3. ፈቃድ

ሀ. ውሳኔዎችን ለመወሰን የሚያስችል ችሎታ
ለ. የማስብ፣ የማመዛዘንና የማወቅ ችሎታ
ሐ. ስሜትን የማገናዘብና የመግለጽ ችሎታ

የአካላዊነት ሌሎች ባህርያት

ከዚህ በላይ ከተገለጹት ጉልህ የአካላዊነት መገለጫዎች በተጨማሪ ስለ አካላዊነት ያሰንን መረዳት የሚያስፉልን አንዳንድ ሌሎች ባህርያትም አሉ። እነርሱም፦

1. አካላዊነትን ገለጭ ግንኙነቶች
2. አካላዊነትን ገለጭ ድርጊቶች
3. አካላዊነትን ገለጭ ሰሞች
4. አካላዊነትን ገለጭ ተውላጠ ስሞች
5. አካላዊነትን ገለጭ እርምጃዎች ናቸው።

አሁን እንደምንመለከተው እነዚህ ሁሉ የማንነት መታወቂያዎች ከመንፈስ ቅዱስ አካላዊነት ጋር ሊገናዘቡ ይችላሉ።

❶. *አካላዊነትን ገለጭ ግንኙነቶች።* ቀደም ሲል የውሃ ጥምቀት ሥርዓት አፈጻጸምንና የሐዋርያውን የስንብት ቃል ስንመለከት መንፈስ ቅዱስ

ከእግዚአብሔር አብና ከወልድ ጋር አንድ እንደሆነ ተገንዝበናል። ይህ ከሥላሴ አብላት ጋር የሚደረገው ግንኙነት የአካልነትን መኖር ያመለክታል። አንድን ሰው በአብ በወልድና በ"ግፊት"፣ "በእስትንፋስ"፣ "በኃይል" ወይም "በንፋስ" (ማቴ 28:19) ስም እንዲያጠምቅ ማዘዝ ሞኝነት አይመስልም? በእርግጥ ይመሰላል፤ ምክንያቱም ከሌሎች አካላት ጋር ሊተባበርና ተግባርን ሊፈጽም የሚችለው ራሱ እኔ የሚል አካል ያለው ብቻ ነውና።

በኢየሩሳሌም ጉባኤ የተቀመጡት ሐዋርያተና ሽማግሌዎች "... ከዚህ ከሚያስፈልገው በቀር ሌላ ሸክም እንዳንጭንባችሁ እኛና መንፈስ ቅዱስ ፈቅደናልና ..." (የሐዋ 15:28) በማለት ለጻፏቸው ቃላት በጣም እርግጠኛ መሠረቱ ይህ ነው። በሥላሴ ውስጥ ካሉት ሌሎች አካላት ጋር ባደረጋቸው ግንኙነቶች መንፈስ ቅዱስ አካል ያለው እንደሆነ በግልጽ ሊታይ ይችላል።

❷. *አካላዊነትን ገለጭ ድርጊቶች* በእግዚአብሔር ቃል የተገለጹትን የመንፈስ ቅዱስ ተግባራት በምናስብበት ጊዜ ለአካላዊነቱ ምን ያህል የላቀና የተሟላ ትርጉም እንደሚሰጡ እንመከታለን። የሚከተሉትን ክፍሎች ማንበብህን እርግጠኛ ሁን።

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል	አካላዊነትን የሚያሳዩ ተግባራት
2ጴጥ 1:21	መንፈስ ቅዱስ ይገልጻል፤ ያነቃቃል ደግሞም ያስችላል።
1ቆሮ 2:10	ሁሉን ይመረምራል።
የሐዋ 13:2	ይናገራል፤ ሰዎችን ለአገልግሎት ይጠራል።
ራዕ 2:7	
ዮሐ 15:26	ይመሰክራል።
የሐዋ 18:8-7	በአገልግሎት ወቅት ሕዝቡን ይመራል፤ አብዛኛውንም ጊዜ አንድን ተግባር እንዳያከናውኑ ወይም ከማድረግ እንዲቆጠቡ ያደርጋል።
ሮሜ 8:26	ይማልድልናል።
ዮሐ 14:26	ያስተምራል።
ዮሐ 16:8-11	ይወቅሳል።
ዮሐ 16:13	ይመራል።
ዮሐ 16:14	ክርስቶስን ያከብራል።
ዮሐ 3:5	ዳግም ልደትን ያስገኝልናል።

(5). ከፍ ብለው የተገለጹት ተግባራት ስለ መንፈስ ቅዱስ ማንነት ምን ያመለክታሉ? ለዚህ ጥያቄ የምትሰጠውን ምላሽ በማስታወሻ ደብተርህ ጻፈው።

❸. *አካላዊነትን ገለጭ ሰሞች፦* ኢየሱስ በስቅላቱ ዋዜማ ደቀ መዛሙርቱን ትቶአቸው እንደሚሄድ ገልጾ ነበር። የእርሱ ከእነርሱ ተለይቶ መሄድ አመራሩን፣ የሚሰጣቸውን ዋስትናና ምክር እንደሚያርቅባቸው

በማወቅ ኢየሱስ "እኔም እብን አለምናለሁ ለዘላለምም ከእናንተ ጋር እንዲኖር ሌላ አጽናኝ ይሰጣችኋል" (ዮሐ 14:16) ብሏል።

ኢየሱስ በእርሱ ቦታ የሚተካው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ (ዮሐ 14:26) ወዲያውኑ ለይቶ አሳወቀ። እራሱ የመጣው ስለ አብ ሊያውጅ እንደሆነም ተናግሮአል። እንደዚሁም ሁሉ መንፈስ ቅዱስ የኢየሱስን ማንነትና ለሰዎች ያለውን ፈቃድ ያብራራል፣ ይገልጸል፣ ይተረጉማል። (የሚከተሉትን ክፍሎች እነዓዕር፡- ዮሐ 14:15-18፣ 26፤ 15:26 ደግሞም 16:13-15)። ስለሆነም መንፈስ ቅዱስ እጽናኝ ተብሎ ተጠርቷል፣ የኢየሱስንም ቦታ በመተካትና ሌላው አጽናኝ ተብሎ የክርስቶስን አገልግሎት እንዲፈጽም ተልኳል። ይህንን ኃላፊነት መወጣት ይቻል ዘንድ፣ የሚለይ ስሜትን የሚያገናዝብና የሌሎች ጉዳይ የሚገደው አካላዊ ማንነት ያለውን ማግኘት ጠይቋል፣ ይህም አካል በእግዚአብሔር ልጅ ሥፍራ በመሆን ተግባሩን ያከናውናል።

መንፈስ ቅዱስ ወልድ ባቀረበው ጥያቄ መሠረት በአብ ተልኳል (ዮሐ 15:26) የተሳከውም ወልድን እንዲያከብርና አማኞችን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የሚያስፈልጋቸውን እንዲያገሰግል ነው። የእውነት መንፈስ (ዮሐ 14:17)፤ የሕይወት መንፈስ (ሮሜ 8:2)፤ የፀጋው መንፈስ (ዕብ 10:29)፤ የልጅነት መንፈስ (ሮሜ 8:15፤ ገላ 4:5-7)፤ የተስፋው መንፈስ (የሐዋ 1:5)፤ የቅድስና መንፈስ (ሮሜ 1:4) እንዲሁም ጠበቃ (1ዮሐ 2:1) ወይም አጽናኝ (ዮሐ 14:16 ፣26) ተብሎ ተጠርቷል። እነዚህ ስሞች ሁሉ የተስጡት መንፈስ ቅዱስ ኢየሱስን የሚያከብረው፣ ለእኛም እውን እንዲሆንልን የሚያደርገውና ምድራዊ አገልግሎቱንም እየቀጠለ ያለው ያው መንፈስ ቅዱስ ነው።

አጽናኙ መንፈስ ቅዱስ (ኤፌ 4:30)፤ የኢየሱስ መንፈስ (የሐዋ 16:7)፤ የክርስቶስ መንፈስ (ሮሜ 8:9)፤ የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ (ፊልጵ 1:19) እንዲሁም የእግዚአብሔር መንፈስ (1ዮሐ 4:2) ተብሎም ተጠርቷል። ስሞቹ የተለያዩ ቢሆኑም የሚናገሩት ግን በሰ አንድ አካል ነው። የተለያዩት ስሞች በቀላሉ ለይተው የሚያሳዩት የመንፈስ ቅዱስን ልዩ ልዩ የማንነትና የተግባር ገጽታዎችን ነው።

❹. *አካላዊነትን ገላጭ ተውላጠ ስሞች።* በዮሐንስ ወንጌል ምዕ 14፣ 15 እና 16 ሳይ መንፈስ ቅዱስ ትኩረት እንደተስጠው ምናልባት ልብ ብለህ ይሆናል። የመንፈስ ቅዱስ አካላዊነት ትኩረት ይስጠው ዘንድ ዮሐንስ ተውላጠ ስሞችን መጠቀሙ አስፈላጊ ጉዳይ ነው። ለምሳሌ ያህልም በግሪክ ቋንቋ "ኤኬይኖስ" የተባሰው ተውላጠ ስም በዮሐ 16:13 ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ተያይዞ ተጠቅሷል፣ ይህም አካልነት እንዳለው ያረጋግጣል። ይሄው ተውላጠ ስም 1ዮሐ 2:6፤ 3:3፣ 5፣ 7 እና 16 ስኢየሱስ የተጠቀስው ያው ተውላጠ ስም ነው።

❺. *አካላዊነትን ገላጭ እርምጃዎች።* በመጨረሻም መንፈስ ቅዱስ ሰዎች በአሱነቱ፡ ደረጃ እርምጃ ሊወስዱበት የሚችሉ ሆኖ መገኘቱ እካላዊነት እንዳሰው ያመለክታል። መንፈስ ቅዱስን ሰዎች ሊፈታተኑት ወይም ሊፈትኑት (የሐዋ 5:9) እንደሚችሉ፤ እንደሚያዘን (ኤፌ 4:30)፤ ሊዋሹበት እንደሚችሉ (የሐዋ 5:3)፤ ሊስደብ ወይም ክፉ ቃል ሊናገሩበት እንደሚችሉ (ማቴ 12:31-32) ሊቃወሙት እንደሚችሉ (የሐዋ 7:51)፤ ሊያክሩት እንደሚችሉ (ዕብ 10:29) የእግዚአብሔር ቃል ያስረዳል። እካላዊ ያልሆነን ኃይል እነዚህን የመሰሉ እርምጃዎች ሊወስዱበት አይችሉም፤ ደግሞም እነዚህን የመሰሉ ምላሽንም መስጠት አይችልም።

(6). ከሚከተሉት ቃላት መንፈስ ቅዱስን በትክክል ሰመግለጽ ልንጠቀም ባቸው የምንችሰው የትኞቹን ነው? ትክክለኛ ናቸው ከምትላቸው ቃላት ወይም ሐረጎች እንባር ያሱትን ፊደሎች ክበባቸው።

ሀ. እጽናኝ	ሸ. ልንፈታተነው የምንችሰው
ለ. መሪ	ቀ. አካላዊነት ያሰው
ሐ. እካላዊ ያልሆነ ኃይል	በ. እስተማሪ
መ. እርስ	እ. ስሜት ያሰው
ሠ. መለኮት	ተ. እውቀት
ረ. ጠበቃ	ቸ. ልዕልና
ሰ. ይሄ (ሰዕቃ)	ኘ. ልናክፋፋው የምንችለው

የመንፈስ ቅዱስን እካላዊነት መገንዘባችን አስፈላጊ ነገር ነው። በእግዚአብሔር ሕልውና ውስጥ በራሱ አካላዊነት እንዳሰው ስንረዳ አምልኮአችንን፣ እምነታችንን፣ ፍቅራችንን እንዲሁም እክብሮታችንን ሊቀበል እንደሚገባው እንመስከታስን። የኛ ትኩረት ሊሆን የሚገባው እርሱ እኛን ገንዘቡ እንዲያደርገን ሰታላቅነቱና ለክብሩም እንዲጠቀምብን መፍቀድ ነው።

የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት

በመፍጠር ሥራ ውስጥ ከእብና ከወልድ ጋር በመሆን ባከናወነው ተግባር የመንፈስ ቅዱስን እገልግሎት እንድ ገጽታ ቀደም ብሰን ተመልክተናል። በዚህ ተግባር መንፈስ ቅዱስ ያደረገውን ተሳትፎ እስመልክቶ መዝሙረኛው፡ "መንፈስህን ትልካለህ ይፈጠራሉም፣ የምድርንም ፊት ታድሳለህ" (መዝ 104:30) ብሏል። ይህ ጥቅስ ፍጥረቱን በመንከባከብ ወይም ለፍጥረቱ በመጠንቀቅ በኩል መንፈስ ቅዱስ ስለሚፈጽመው ተግባርም ይናገራል።

ነቢዩ ኢሳይያስ በፍጥረቱና በመግቡ (መሰኮታዊ ምሪትና እንክብካቤ) እግዚአብሔር ስላለው ወሰን የሌለው ታላቅ ኃይል በሚገልጽበት ጊዜ "የእግዚአብሔርን መንፈስ ያዘዘ፣ ወይስ እማካሪ ሆኖ ያስተማረው ማን

ነው?" ይላል (ኢሳ 40:13) ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት በምናስብበት ጊዜ የእግዚአብሔርን ምሰጢራት ለማወቅ ያለው የሰው ችሎታ ገደብ እንዳለው መገንዘብ አንጀምራለን። ስለሆነም ስለ መንፈስ ቅዱስ እጅግም መረዳት አንችልም። ሆኖም በሕልውናው ልንነካ፣ ልንባረክና ምሪት ልናገኝ እንዲሁም በኃይሉ ልንበረታ አንችላለን በማለት ለዚህ ጥያቄ ያለንን ምላሽ መስጠት እንችላለን። ምንም እንኳን ምሥጢሩን ባንረዳም የነፋስን ውጤት እንደምንመለከት ሁሉ (ዮሐ 3:8) የመንፈስ ቅዱስንም የአገልግሎት ውጤት አንመለከታለን።

ውሱን የሆነው ሰው ወሰን የሌለውን የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ሙሉ በሙሉ መረዳት ባይችልም በእግዚአብሔር ቃል እንደተገለጸው የእሰራሩን አንዳንድ አጠቃላይ አቅጣጫዎች ሊመረምር ይችላል። እነዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስለ መንፈስ ቅዱስ አካላዊነት በአማካይ ሙሉ የሆነ ገጽታና ስለ አገልግሎቱም ሰፊ ይዘት ያቀርባሉ። አገልግሎቱን ከሚከተሉት ሁኔታዎች ጋር በማዛመድ እንመለከተዋለን።

1. ስማያምነው ዓለም
2. ስግለሰብ አማኞች
3. በአጠቃላይ ለቤተክርስቲያን

የማያምነውን ዓለም በተመለከት

ዓላማ 3 መንፈስ ቅዱስ ለማያምነው ዓለም፣ ለግለሰብ አማኞችና ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ስለሚለጥባቸው መንገዶች ምሳሌዎችን መርጠ መመልከት

በተፈጥሮና በመለኮታዊ ችሮታ ከሚያከናውነው ሥራዎች ባሻገር መንፈስ ቅዱስ በማያምነው ዓለምም ዘንድ ተሳትፎ ያደርጋል። በዮሐ 16:8-11 መሠረት ስለ ኃጢአት፣ ስለ ጽድቅና ስለ ፍርድ ይወቅሳል።

❶. *ስለ ኃጢአት ይወቅሳል።* መንፈስ ቅዱስ በመጣ ጊዜ "ስለ ኃጢአት፣ ስለ ጽድቅም ስለ ፍርድም ዓለምን ይወቅሳል፤ ስለ ኃጢአት፣ በእኔ ስለማያምኑ ነው፤" (ዮሐ 16:8-9) በማለት ኢየሱስ ተናግሯል። መንፈስ ቅዱስ በኢየሱስ ክርስቶስ ስለ አለማመን ኃጢአተኛ ሰዎችን ይወቅሳል።

❷. *ስለ ጽድቅ ይወቅሳል።* " ስለ ጽድቅም፣ ወደ አብ ስለምሄድ ከዚህም በኋላ ስለማታዩኝ ነው" (ዮሐ 16:10)። ይህም ማለት መንፈስ ቅዱስ ለሰዎች የጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ጽድቅ እንዲሁም የሌሎችን ጻድቅ ያስመሆን ይገልጻል። እግዚአብሔር ኃጢአተኞችን አሁን ጻድቃን አድርጎ የሚቆጥራቸው ኢየሱስ በኃጢአት ላይ ባገኘው ድል ምክንያት መሆኑን ያሳስባቸዋል፣ ደግሞም በእርሱ ላይ በሚኖራቸው እምነት ጻድቃን እንዲሆኑ ያስችላቸዋል።

❸. *ስለ ፍርድ ይወቅሳል።* "ስለ ፍርድም የዚህ ዓለም ገዢ ስለተፈረደበት ነው" (ዮሐ 16:11)። መንፈስ ቅዱስ የማያምኑትን ስለ ፍርድ የሚወቅሳቸው የክርስቶስ ሞትና ትንሳኤ በዓለም ላይ ከሚመጣው ፍርድ ጋር ያለውን ዝምድና በማመልከት ነው። በሞቱና በትንሳኤው ምክንያት የዘላለም ሞት ቦተፈረደበት ስጠላት በሰይጣን ላይ ድል ነስቷል። በመሆኑም መስቀል የኃጢአት ፅዳ ቅጣት መከፈሉን ያመለክታል። የክርስቶስን ሞትና ትንሳኤ እምነው ለተቀበሉት ሁሉ ቤዛነትንና ከሰይጣንና ከኃጢአት ኃይል ነፃ መውጣትንም ያመለክታል።

ጌታ ኢየሱስ ስለመንፈስ ቅዱስ እገልግሎት ያስተማረው (ዮሐ 14:16-17፣ 26፤ 15:26፤ 16:5-15) ትምህርት ጌታችን ኢየሱስ በምድር በማይኖርበት ጊዜና በእግዚአብሔር አብ ሥፍራ በመሆን ለማያምኑት ሰዎች የሚመሰክርላቸው መንፈስ ቅዱስ ነው ብለን እንድናምንም ይገፋፋናል። መንፈስ ቅዱስ የማያምነውን ሰው ስለ ኃጢአት ይወቅሰዋል፤ ወደ ክርስቶስም ያቀርበዋል (ዮሐ 6:44)፤ ከዚህ በኋላ መንፈሳዊ ኃላፊነቶችን በተመለከተ አማኙ መረዳት እንዲኖረው ያደርጋል (1ዮሐ 1:9)።

(7). *መንፈስ ቅዱስ ለማያምነው ዓለም የሚሰጣቸውን የአገልግሎት መንገዶች በተመለከተ ከሚከተሉት መግለጫዎች እውነተኛ ምሳሌዎች የትኞቹ ናቸው? ከትክክለኛው ምርጫህ አንባር ያለውን ፈደል ክበበው።*

ሀ. *መንፈስ ቅዱስ ጻድቅ ያልሆነ ሰው ጻድቅ መሆን የሚችልበት ብቸኛው መንገድ በክርስቶስ ቤዛነት በማመን እንደሆነ ይገልጸልታል።*
ለ. *መንፈስ ቅዱስ በዓለም ውስጥ በመኖሩ በሰይጣን ላይ የመጨረሻውን ድል ተቀዳጅቷል።*
ሐ. *ክርስቶስ ለአንድ ጊዜና ለዘላለም የኃጢአትን ፅዳ እንደከፈለ በመግለጽ ነው መንፈስ ቅዱስ በማያምኑት ላይ መለኮታዊ ፍርድ እንዳሰባቸው የሚያሰገነዝባቸው።*
መ. *መንፈስ ቅዱስ የማያምኑትን ስለ ኃጢአት ይወቅሳቸዋል።*

ግለሰብ አማኞችን በተመለከተ

የሚያደርግልን ዕርዳታ

ዓላማ 4 መንፈስ ቅዱስ አማኞችን የሚረዳባቸውን ሰድስት መንገዶች መግለጽ

መንፈስ ቅዱስ ለአማኞች የሚሰጠውን እገልግሎት በሁለት ዘርፍ ከፍለን እስቲ እንመልከተው፡- 1. ረድኤቱ 2. ጥምቀቱ

መንፈስ ቅዱስ ስለሚመጣና ስለሚረዳቸው (ዮሐ 16:7) የእርሱ መሄድ ስአነርሱ መልካም እንደሆነ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ይነግራቸው ነበር።

እማኞች ምን ያህል ልዩ ልዩ ዓይነት ዕርዳታዎችን እንደሚያገኙ ሳስብ እደነቃለሁ።

1. *ለማኞች የምንሆነው ስመንፈስ ቅዱስ ሥራ ለማካይነት ነው።* እማኞች ባልነበርንበት ጊዜ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ሙታን ነበርን። ሆኖም በንስሃና በእምነት ወደ እግዚአብሔር በቀረብን ጊዜ በመንፈስ ተወለድን። አዲስ ፍጥረት ሆንን (2ቆሮ 5:17)። በእግዚአብሔር መንፈስ ዳግመኛ ተወለድን፣ ደግሞም አዲስ ፍጥረትነትን ተቀበልን። ይህም ዳግም ልደት ተብሎ ይጠራል (ዮሐ 3:5-7፣ ኤፌ 2:5 እንዲሁም ቲቶ 3:5)።

2. *ለምስክርነት ከመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንቀበላለን* (የሐዋ 1:8) የምሥራቹን ቃል ለሌሎች ለማካፈል በምንወስንበት ጊዜ ችግሮች መታየት ይጀምራሉ። ልዩ ልዩ ሁኔታዎች፣ እንዳንድ ሰዎች፣ እንዲሁም ርኩሳን መናፍስት ሊቋቋሙን ይሞክራሉ። ወሰናክሎቻችንን ሁሉ በድል ለማለፍ የተለየ ኃይል ሊኖረን ይገባል። ለተዋጣ የምስክርነት አገልግሎታችን የኃይል ምንጫችን ሊሆን የሚገባው የእግዚአብሔር መንፈስ ነው።

3. *መንፈስ ቅዱስ መምህራችን ሆኖ ያገለግለናል* (ዮሐ 14:26፣ 15:26፣ 16:13)። እኔ ምናልባት ከተማሩ ወገን ሳልሆን እችላለሁ፣ ሆኖም እንዲያግዘኝ ወደ መንፈስ ቅዱስ በምመጣበት ጊዜ ያስተምረኛል። ለማንኛውም ሰው እንደሚያደርገው ሁሉ ለእኔም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመግለጽ ፈቃደኛ ነው (1ቆሮ 2:12-14)።

4. *በእኛ ሥፍራ ሆኖ በሚፈጽመው ምልጃ ከመንፈስ ቅዱስ ረድኤትን እንቀበላለን* ይህም ማለት ፍላጎቶቻችንን በስማያዊው አባታችን ፊት ያቀርብልናል ማለት ነው። እኔ እንደተሰማኝ ሁሉ እናንተስ በእንዳንድ ሁኔታዎች ላይ እንዴት መጸለይ እንደሚገባችሁ ለማወቅ አልተቸገራችሁም? እንዳንድ ጊዜ መጸለይ እንኳን የምንችል አይመስለንም። ይህንን የመሰለ ሁኔታ ባጋጠመን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በእኛ ውስጥ በሚጸልየው ጸሎት ልንታመን እንችላለን።

5. *መንፈስ ቅዱስ ዕለት በዕለት ወደ ድል አድራጊና ክርስቶስን ወደሚመስል ሕይወት ይመራናል።* ዳግም በምንወለድበትና መንፈስ ቅዱስም በሕይወታችን መኖር በሚጀምርበት ወቅት ሁለት ማንነት እንዳለን እንገነዘባለን። እንደኛው ማንነታችን ስለ ተፈጥሮአዊው ወይም ስለማዙፉ አካል የሚያስብ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ስለ መንፈሳዊው የሚገደው ነው። ይህም ሆኖ አካላችን ለሥጋዊ ፈተናዎች የተጋለጠ መሆኑን እንረዳለን። በውስጣችን በክፉና በበጎ ተፅዕኖዎች ምክንያት በሚካሄደው ትግል ስለምንለማመደው ልምምድ የሮሜ መልእክት ምዕራፍ 7 በዝርዝር ይገልጸዋል። ጳውሎስ "በእኔ" ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር እውቃለሁና ፈቃድ አለኝና መልካሙን ግን ማድረግ የለኝም" (ሮሜ 7:18) ብሏል። በዚህ ላይ ሐዋርያው የመንፈስ ቅዱስን ረድኤት አላገናዘበም፣ በምዕራፍ 8 ላይ ግን ከድል አድራጊ ሕይወት ጋር በማገናዘብ ስለ መንፈስ

ቅዱስ 19 ጊዜ ይጠቅሳል። ክርስቲያን በኃጢአት ላይ ለሚነናጸፈው ድል ምስጢሩ *መንፈስ ቅዱስ* በሕይወቱ ላይ ገዢ መሆኑ ነው። መንፈስ ቅዱስን ግድ የሚለው የእኛ መንፈሳዊ ጉዳይ ነው፣ ራስ ወዳድነታችንን እንዴት ማሸነፍ እንደሚገባን ሊያሳየን ይፈልጋል (ሮሜ 8:1-14)።

በሕይወታችን ለመንፈስ ቅዱስ የምንሰጠው ሰፍራና እስፈላጊነት በሚኖረን ባሕርይ ላይ ወሳኝ ነው። ሰው የተወሰኑ ጠባዮች ብቻ እንዲኖሩት ሆኖ አልተወለደም። ባሕርይ ደጋግመን ከምናደርጋቸው ድርጊቶች የሚከሰቱ ጠባዮች ውጤት ነው። *ሥጋዊ* ፍላጎቱን ብቻ ለማርካት የሚሯሯጥ የፍጥረታዊ ሰው ባሕርይ የሚያንገፈግፍና የሚያሳዝንም ትዕይንት ነው። መንፈስ ቅዱስ ሕይወቱን እንዲመራ የሚፈቅድለት መንፈሳዊ ሰው ባሕርይ ከዚህ በኋላ እንደምንመለከተው በፍጹም የተለየ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ መፍትሔ እድርጎ ያቀረበው ቃል "በመንፈስ ተመላለሱ፣ የሥጋንም ምኞት ከቶ እትፈጽሙ" (ገላ 5:16) የሚል ነው።

6. *መንፈስ ቅዱስ በክርስቲያኖች ሕይወት የሚታዩትን የተባረኩ ፍሬዎች ያስገኛል።* እንድ ጊዜ እንድ ጓደኛዬ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በጣም የቀረበ ግንኙነት አለን የሚሉ እንዳንድ ቡድኖች ስለ መንፈሳዊነታቸው በመኩራራት ለምን ለሌሎች ለዎች ይናገራሉ? ብሎ ጠየቀኝ። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በለ ራሱ በመኩራራት ይናገራል ብሎ እንደማይገምት ነገረኝ። እኔም ሙሉ በሙሉ ጓደኛዬ በተናገረው ነገር ተስማማሁ። ሥጋዊነትን (ለሥጋዊ ፍላጎታችን መማረክን) ወይም ግልብ የሆነ መንፈሳዊነትን ለማስወገድ በመንፈስ ልንመላለስ ይገባናል።

በመንፈስ መመላለስ የሚያመለክተው እንድ እማኝ ዘወትር በመንፈስ ቅዱስ ላይ እንደሚደገፍና በእማኙ ማንኛውም የሕይወት እቅጣጫ መንፈስ ቅዱስ ድል የመስጠት ችሎታ እንዳለው ማመኑን ነው። ኃጢአት እልባ የሆነ ፍጹም ሕይወት እንደምንኖር ተስፋ የተገባልን ባይሆንም በመንፈስ ቅዱስ በተሞላንና በእርሱም ቁጥጥር ሥር በምንሆንበት ጊዜ በእስደናቂ ሁኔታ እንለወጣለን። የሥጋ ሥራዎችን በሕይወታችን ከመግለጽ ይልቅ (ገላ 5:19-21) የመንፈስ ቅዱስ ፍሬዎችን "ፍቅርን፣ ደስታን፣ ሰላምን ትዕግሥትን፣ ቸርነትን፣ በጎነትን፣ እምነትን፣ የዋህነትንና ራስን መግዛትን" (ገላ 5:22-23) እናፈራለን። እነዚህ ልዩ *መታወቂያዎች* ወይም ፍሬዎች የመንፈስ ቅዱስ *ማንነት መታወቂያዎች* ናቸው። ዝንባሌዎቻችንን፣ ግንኙነቶቻችንና ተግባሮቻችንን በቅርበት በመመልከት እነዚህን ልዩ *መታወቂያዎች* እንገልጽ እንደሆነ ወይም እነዚህ ፍሬዎች ጎድለውን እንደሆነ ማረጋገጥ ይኖርብናል።

(8). ከዚህ በታች የተሰጡትን ስድስት ቃላት መሠረት በማድረግ መንፈስ ቅዱስ እማኞችን የሚረዳባቸውን ስድስት መንገዶች ግለጽ።

ሀ. ዳግም ልደት
ለ. ምስክርነት
ሐ. ማስተማር
መ. መማለድ
ሠ. ምሪት
ረ. ፍሬ

ዓላማ 5 ከመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ጋር ዝምድና ያላቸውን መግለጫዎች ለይቶ ማወቅ

መንፈስ ቅዱስ ከአማኞች ጋር ያለው ቅርብ ግንኙነት በመጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌያዊ በሆኑ በርካታ ገላጭ ቃላት እማካይነት ቀርቧል። ከእነዚህም አንዱ ጥምቀት የሚለው ሲሆን ይህም ቀደም ብለን እንደተመለከትነው ትርጉሙ "መጥለቅ" ማለት ነው (ማቴ 3:11፤ የሐዋ 1:5)። አንድ ሰው በውሃ ውስጥ በሚጠልቅበት ጊዜ ምንድን ነው የሚሆነው? ሙሉ በሙሉ ይረጥባል! በሁለመናውም ላይ ውሃ ይሆናል። እግዚአብሔር በማንነቱ ሙሉ በሙሉ እንደሚያረሰርሰን (ፍጹም እንደሚሞላን) ማወቁ ለኛ ለምሰኪን ሰዎች ምን ያህል የከበረ ነገር ነው!

መንፈስ ቅዱስ ከአማኙ ጋር ያለውን ግንኙነት ለመግለጽ የምንጠቀምበት ሌላው መግለጫ "መሞላት" የሚለው ነው (የሐዋ 2:4፤4:31) አንድ ጎድጓዳ ሳህን ሙሉ ከሆነ ተጨማሪ ነገር ለመቀበል ሥፍራ አይኖረውም። በዚሁ ዓይነት መንገድ ምንም ተጨማሪ መቀበል እስከማንችል ድረስ መንፈስ ቅዱስ የኃይሉንና የክብሩን ሙላት ሊሰጠን ይፈልጋል። የዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘትና በክርስቶስ አካል ውስጥ በተሳካ ሁኔታ እንድናገለግለው የሚያስፈልገን ኃይል፣ ጥበብና ቅባት ይኖረናል። በተደጋጋሚ ጊዜያት የጥንቶቹ ክርስቲያኖች እንደተሞሉት ሁሉ እኛም ልንሞላ እንችላለን። የእኛ የመቀበል ችሎታ ባደገ መጠን በአዲስና ከፍ ባለ ደረጃ በመለኮቱ ሙላት እኛን መሙላቱን ይቀጥላል። አማኞች "መንፈስ ይሙላባችሁ" (ኤፌ 5:18) የሚል ምክር ተሰጥቷቸዋል። ምን ጊዜም በመንፈስ ቅዱስ ሙላት ውስጥ የመቆየት ፍላጎት ይኑረን!

ይህንን ግንኙነት ልንመለከት የምንችልበት ሦስተኛው መንገድ መንፈስ ቅዱስ በእኛ ላይ እንደፈሰሰ መናገር ነው (ኢዩ 2:28-29)። ኢዩኤል የሚናገረው ሰብላቸው በወቅቱ ሙሉ በሙሉ ይደርሰላቸው ዘንድ በእሥራኤል የሚገኙ ገበሬዎች በጉጉት ስለሚጠባበቁት የበልግ ዝናብ ነው። የእግዚአብሔርን ክብር ለመግለጽ የሚያስችለንን ብርታት በሙሉ ማግኘት እንችል ዘንድ በአብያተ ክርስቲያናችንና በግል ሕይወታችን መንፈስ ቅዱስ እንዲፈስልን እኛም ይህንኑ የመሰለ ናፍቆት ይኑረን።

ቀደም ብዬ ባቀረብኩት አገላለጽ መሠረት የመንፈስ ቅዱስ ልዩ የሆነ እሰራር በሕይወታችን ይጀመር ዘንድ አዲስ ኪዳን እንደሚያመለክተን ቅድመ ልምምድ ሊኖረን ይገባል። ይሁን እንጂ በጅማሬው ላይ የተለማመድነው የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ልንጓዝ የጀመርነው ጉዞ መደምደሚያ ተደርጎ ሊታይ አይገባውም።

በሐዋርያት ሥራ ከሰፈረው የአማኞች ልምምድ እንደምንረዳው በጅማሬው ላይ ከተለማመዱት የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በኋላ (የሐዋ 2) ተጨማሪ የመንፈስ ቅዱስ ሙላት ተለማምደዋል (የሐዋ 4:31)። በመንፈስ ቅዱስ ወደሚመራው ሕይወት በመግባታቸው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር

ተራመዱ በመንፈሳዊ አቋማቸውም አደጉ። ለምሳሌ ያህል 2ቆሮ 3:18ንና ሮሜ 8:29 ከ2ጴጥ 3:18 ጋር እንነፅራቸው። ይሄኛው ግንኙነት ከዕለት ወደ ዕለት እየተዋበ ሊሄድ ይገባል። ጊዜው እያለፈ በሄደ መጠን እስተማማኝ መንፈሳዊ ዕድገት ልናይ ይገባናል። በእኛ ውስጥ መልካሙን ሥራ በመጀመሩ ከእርሱ ጋር እስከተራመድን ድረስ በእኛ የጀመረውን ወደ ፍጻሜ ያደርሰዋል (ፊልጵ 1:6)።

(9). ለሚከተሉት ቃላት ለተሰጡት መግለጫዎች የበለጠ ተስማሚ የሆኑትን በክፍት ሥፍራዎች በመሙላት መግለጫዎቹን አጠናቅቁ።

1. ጥምቀት 2. መሞላት 3. መፍሰስ

ሀ. ከመለኮት እንባር ሲታይ የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት እንደ ይታያል።

ለ. በመንፈስ ቅዱስ ወደሚመራ ሕይወት የመጀመሪያ እርምጃ በመራመድ ላይ ያሉ መንፈስ ቅዱስ ያልተሞሉ አማኞች የመንፈስ ቅዱስ ያስፈልጋቸዋል።

ሐ. አማኙ ለመንፈስ ቅዱስ አቀባበል ያለውን አቅም የሚያመለክተው ፅንሰ ሃሳብ ነው።

መለያ ምልክቶች

ዓላማ 6 ጌታን በተሻለ መንገድ ለማገልገል ትችል ዘንድ የተወከለውን የመንፈስ ቅዱስ ምልክት በሕይወትህ እንዴት በሥራ እንደምታውለው መግለጽ

በእስተምህሮ መንፈስ ቅዱስ ላይ የተመሠረተውን ይህንን ጥናት የመንፈስ ቅዱስን እገልግሎት አንዳንድ ገጽታ ስለሚገልጹት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምልክቶች ሳንጠቅስ አናጠቃልለውም። ምልክቶቹ በምን ሁኔታ ጥቅም ላይ እንደዋሉ ማወቅ እንድትችል ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥቅሶች እያንዳንዳቸውን መጽሐፍ ቅዱስህን ገልጠህ ተመልከታቸው።

ጥቅስ	ምልክት	መግለጫ
1. ማቴ 3:11	እሳት	እሳት ንፁህ ያልሆነውን ያቃጥላል።
2. ማቴ 3:16	ርግብ	ርግብ ገርነትን ትወክላለች።
3. 1ነገ 19: 16 1ዮሐ 2:20	የቅባት ዘይት በመንፈስ ቅዱስ መቀባት	የብሉይ ኪዳን ነገሥታትና ነቢያት፣ እግዚአብሔር እገልግሎታቸውን ለመቀበሉ ምልክት በመሆኑ ብዙውን ጊዜ በዘይት ይቀቡ ነበር።
4. ሉቃ 11:13	ስጦታ	መንፈስ ቅዱስ እግዚአብሔር ለእኛ የሰጠን ስጦታ ነው።
5. ዮሐ 7:37-39	የሕይወት ውሃ	ተጥረናርፎ እስኪፈስ ድረስ መንፈስ ቅዱስ በእዲያ ሕይወት ይሞላል።
6. 2ቆሮ 1:22 ኤፌ 1:13-14	ማሕተም ወይም መያዣ	ከእግዚአብሔር ጋር ለሚረን የዘላለም ሕይወት መንፈስ ቅዱስ እንደ መያዣ ተሰጥቶናል።
7. ዮሐ 20:22 ሕዝ 37:9፣14	እስትንፋስ ነፋስ	እስትንፋስ መንፈስ ቅዱስ ለእኛ ሕይወትን የሚስጠን የእግዚአብሔር እስትንፋስ ነው።

(10). በማስታወሻ ደብተርህ ምልክቶችን በገርገር ጻፋቸው። ጌታን በተሻለ መንገድ ታገለግል ዘንድ ከሕይወትህ ጋር የሚገናዘበውን እያንዳንዱን ምልክት እንደ ት ተግባራዊ እንደምታደርው ግለጽ። ይህ የምትሰራው ልምምድ መንፈስ ቅዱስ በሕይወትህ ለለሚሰራው ሥራና በእርሱም እማካይነት ለለሚመጣው ደስታ እንዳንድ እውነቶችን እንድትገነዘብ ይረዳሃል።

ቤተ ክርስቲያንን በሚመለክት

ዓላማ 7 መንፈስ ቅዱስ ለአገልግሎት የሚለጠውን ችሎታ አማኞች ለዚህ ማስቻል ከሚስጡት ምላሽ ጋር ማቀናጀት

መንፈስ ቅዱስ አማኝ ላልሆነው ዓለምና ለአማኞች እግልግሎት ለለ ሚለጥበት መንገድ የተመለከትነው በተደጋጋፊነት ወይም በእንድ ወጥነት ለክርስቶስ እካል የሚለጠውን እገልግሎት ለመመልከት መሰረት ይሆናል።

መንፈስ ቅዱስ የተለዩ ለዎችን ለተለየ አገልግሎት ይቀባ በነበረበት በብሉይ ኪዳን ዘመን የእግዚአብሔር ለዎች ከመንፈስ ቅዱስ እገልግሎት በከፍተኛ ደረጃ በረኩት እግኙተዋል። ይሁን እንጂ በአዲስ ኪዳን ዘመን ይህ እገልግሎት የማያቋርጥና በተለይ በእገልጋዮች ቡድን ዙሪያ ብቻ የተወሰነ ባለመሆኑ በይበልጥ ይፋ ሆኗል። በእዲስ ኪዳን ዘመን ያለው የመንፈስ ቅዱስ እገልግሎት በብሉይ ኪዳን ወቅት ካከናወነው ሥራ ጋር እንዴትና ለምን እንደሚለይ እስኪ እንመልከት።

በኢየሱስ ጥምቀት ወቅት ዮሐንስ መጥምቁ በመንፈስ ቅዱስ እጥማቂው ኢየሱስ እንደሆነ እወጀ (ዮሐ 1:33)። በፈጸመው የቤዛነት ሥራ ኢየሱስ ተከታዮቹ በመንፈስ ቅዱስ የሚጠመቁበትንና እጽናኙን የሚቀበሉበትን መንገድ ከፈተላቸው። መንፈስ ቅዱስ ከእነርሱ ጋር ለዘላለም የሚኖር የኢየሱስ የራሱ ወኪል ነበር (ዮሐ 14:16)። ከትንሣኤው በኋላ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ በጥቂት ቀን ጊዜ ውስጥ በመንፈስ ቅዱስ እንደሚጠመቁና በውጤቱም ኃይልን እንደሚቀበሉ (የሐዋ 1:5፤8) እለታወቃቸው።

በብሉይ ኪዳን ዘመን ለእንድ ለተወሰነ ሥራ ልዩ ችሎታን እንዲያስገኝ የሚለጥ የተለየ ቅባት የነበረ ቢሆንም በእዲስ ኪዳን ግን ይህ እዲስ ልምምድ ማለትም የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለእማኞች ፍሬያማ መንፈሳዊ ሕይወትና አገልግሎት እንዲኖራቸው የሚለጥ ነው። በብሉይ ኪዳን እንደሚታየው መንፈስ ቅዱስ በእዲስ ኪዳን የሚገኘው እንድ የተወሰነ ውጤት ላይ ለማድረስ ወይም ሥራ ለማሠራት ለተወሰነ ጊዜ ብቻ እይደለም። ከዚህ ይልቅ ክርስቶስን በተቀበሉት ውስጥ በቋሚነት ይኖራል (ዮሐ. 7:38-39፤ 14:17)። መንፈስ ቅዱስ በዚህ መልክ ሲያድር በእማኙ ውስጥ ትልቅ መንፈሳዊ ዕድገት ከመታየቱም በላይ ዕምነታቸ ውንና ልምምዳቸውንም ለሌሎች ለማካፈል ኃይልን ያገኛሉ።

በለሆነም በእዲስ ኪዳን ልምምድ የተቀደለ ሕይወት መኖር እንዲያስችላቸውና ተቀባይነት ባለው መንገድ እግዚአብሔርን እንዲያገለግሉ አማኞች በውስጣቸው የሚያድር መንፈለ ቅዱስ ሊኖራቸው ይችላል። በብሉይ ኪዳን ዘመን ይደረግ እንደነበረው ሁሉ የራሳቸውን መልካም ምኞት ለመፈጸም ካላቸው ፍላጎት በለተቀር ራሱ የሚጠይቀውን እኗኗር ለመኖር ብርታት የማይለጥ ውጫዊ ብቻ የሆነ መመሪያ ወይም ሕግ ከእንግዲህ ወዲህ የላቸውም። በቤተ ክርስቲያን አባላት ውስጥ መንፈለ ቅዱስ ሲያድርና የጋራ እገልግሎታቸውንም ሲመራ በምድር ላይ የእግዚአብሔርን ሥራና ፈቃዱን ለመፈጸም ብርታት ይኖራቸዋል።

(11). ከዚህ በታች ከ1-2 የለፈረውን ዘመን መንፈለ ቅዱስ በለዎች ሕይወት ውስጥ ስለሚያከናውናቸው ተግባሮች ከሀ-ረ ከተለጡት መልሶች ጋር እቀናጃቸው። ይህ ልምምድ መንፈለ ቅዱስ በብሉይና በእዲስ ኪዳን ዘመናት ያከናውናቸው በነበሩት ተግባራት መካከል ያለውን ልዩነት እንድትመለከት ይረዳሃል።

1. ብሉይ ኪዳን
2. አዲስ ኪዳን

ሀ. የተለዩ እገልግሎቶችን እንዲያከናውኑ በለዎች ውስጥ ካደረ በኋላ ይለያቸዋል።
ለ. ክርስቶስን በተቀበሉት ሁሉ ዘንድ ያድራል።
ሐ. በለዎች ውስጣዊ ሕይወት በግል ያድርባቸዋል።
መ. ውጫዊ በሆነና ከግል ሕይወታቸው ጋር ባልተገናዘበ መንገድ በለዎች ዘንድ ይገኛል።
ሠ. እርሱን በመቀበላቸው ብቻ ለዎች በመንፈስ ቅዱስ ይጠመቃሉ።
ረ. ለተለየ ዓላማ እንዳንድ ለዎች እልፎ እልፎ ይቀባሉ።

የኢየሱስ ተከታዮች ውጤታማ ምለክሮች እንዲሆኑ ያለቻላቸውን ብርታት ማግኘት ብቻ ሳይሆን ወንጌልንም በሚገባ ለመመከት ይችሉ ዘንድ ኃይልን ተቀብለው ነበር። ይህም በማር 13:9-11 የተገለጸው ቃል ቀጥተኛ ፍጻሜ ነበር። ቀደም ባለ እንድ ወቅት ጴጥሮስ ከኢየሱስ ጋር ለለነበረው ግንኙነት ለቀረበበት ሙግት ምላሽ ለመለጠት ኃይል እልነበረውም (ማቴ 26:69-75)። ይሁን እንጂ ለትንሣኤው ምበክር መሆንና በበዓለ ኀምሳ ዕለት በመንፈስ ቅዱስ መሞላትን ከሚያካትቱ አያሌ ጉልህ ልምምዶች በኋላ ለመለበክ (የሐዋ 2) ደግሞም እምነቱን አለተማማኝ በሆነ መንገድ ለመግለጽ (የሐዋ 4:8-20) ድፍረት አገኘ።

ከዚህ በተጨማሪ መንፈለ ቅዱስ እጋልጋዮቹን ወዴት መሄድ እንዳለባቸውና ወዴት ደግሞ መሄድ እንደሌለባቸው በመምራት (የሐዋ 13:2፤ 16:6-7) የቤተ ክርስቲያንን የወንጌል ተልዕኮ ይቆጣጠራል። በእርሱ ምሪት እማካይነት የጥንቶቹ ክርስቲያኖች ለቀጣዩ የቤተክርስቲያን ተልዕኮ ማለትም ለፍጥረት ሁሉ ወንጌልን ለመስበክ (ማር 16:15) ቁልፍ ወደ ሆኑ እበፈላጊ ማዕከሎች ደርለዋል። በመጀመሪያው የቤተ ክርስቲያን የወንጌል

ተልእኮ ጥረት ጳውሎስንና በርናባስን ለአገልግሎት የለያቸውና ለዚሁም አገለግሎት የሾማቸው (የሐዋ 13:2) መንፈስ ቅዱስ ነበር።

መንፈስ ቅዱስ ተገቢ የቤተ ክርስቲያን እመራር እንዲኖርም ምሪት ሰጥቷል። ቤተክርስቲያን ባደገችና ብሔራዊ፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ድንበሮችን እያቋረጠች በሄደች መጠን ከእግዚአብሔር ቃልና ከክርስቲያናዊ ፍቅር ጋር የሚጣጣሙ መልሶችን የሚሹ ጥያቄዎች ተነሱ። ተፈጥሮአዊ የሆኑ ሰብአዊ የትምክህት አዝማሚያዎች የክርስቶስን አካል የመከፋፈል ሥጋት ፈጠሩ። ሆኖም የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ያዕቆብና ሐዋርያት ለችግሮቹ መፍትሔ እንዲያስገኙና ጥበብ የተሞላው ምክር እንዲሰጡ አስችሏቸዋል። ይህም ቤተክርስቲያን ከመቸውም ጊዜ ይልቅ በፍጥነት እንድታደግና የእንደኑትንም መንፈስ እንድታዳብር አብቅቷታል።

ላያቋርጥ በቀጠለው ምሪቱ በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነትና ቁጥጥር በተጻፉት መልእክቶች አማካይነት መበርታት፣ መጽናናት፣ መሠረታዊ የክርስትና ትምህርት ማስጠንቀቂያ እንዲሁም ለቤተክርስቲያን ይታዩ በነበሩት የተለዩ የባሕርይ ጥያቄዎች ላይ (1ቆሮ 7:40) ምላሽ ተሰጥቷል። የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊም ቅጣት እግዚአብሔር አማኞችን ወደ መንፈሳዊ ዕድገት የሚመራበት የማሳደጊያ ሂደት እንደሆነ ገልጿል (ዕብ 12:4-11)።

ሁሉን እዋቂ አስተዳዳሪ እንደመሆኑ መጠን በማሳደጉ ሂደት መንፈስ ቅዱስ የእነርሱን ተግባር በዓለምና በክርስቶስ አካል በቤተክርስቲያን ዙሪያ ለማከናወን አስፈላጊ የሆኑትን ስጦታዎች ለእያንዳንዱ አማኝ ያበታተታል። ሮሜ 12:4-8፣ 1ቆሮ 12:1-28፣ ኤፌ 4:11-16 ጋር አነጻጽር። ጳውሎስ ". . . መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ለጥቅም ይሰጠዋል" (1ቆሮ 12:6-7) ብሏል። ስለሆነም መንፈስ ቅዱስ የሚከተሉትን ብርታቶች ለቤተክርስቲያን ያድላል፦

1. ወንጌልን ለመስበክ የሚያስፈልገውን ኃይል
2. የእምነት ተቃዋሚዎችን ለመመከት አስፈላጊ የሆነውን ጥበብንና ድፍረትን
3. ለመላው የክርስቶስ አካል እንዲሁም ለእያንዳንዱ ብልት ለአገልግሎት የሚያስፈልጉ ተገቢ ስጦታዎችን።
4. ሥራውን ለመምራት የሚያስፈልጉ የሚመሩ ሰዎችን
5. ታላቁን ተልዕኮ ለመፈጸም አስፈላጊ የሆኑትን ራዕይና መንፈሳዊ መነቃቃት

(12). ከዚህ በታች ከሀ-ሠ የቀረቡትን የመንፈስ ቅዱስ እገልግሎት መግለጫዎች ከዚህ ቀጥሎ ከ1-5 ተስማሚ ከሆኑ የአማኞች ምላሾች ጋር አቀናጃቸው።

1. ስሕይወትና ለአገልግሎት መሠረታዊ ኃይልን ያነፍላል።
2. ስጦታዎችን ይሰጣል።
3. ራዕይንና ምሪትን ይሰጣል።
4. ለችግሮች መፍትሔ ይሰጣል።
5. ጥበብንና ድፍረትን ይሰጣል።

ሀ. አማኞች እማኝ ስላልሆኑ ሰዎች ግንዛቤ አገኙ፣ እነርሱንም ለማገልገል ምኞት እደረባቸው።
ለ. እያንዳንዳቸው የተሰጣቸውን ልዩ አገልግሎት እያከናወኑ አማኞች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንደተባበረ አካል ያገለግላሉ።
ሐ. አማኞች በመንፈስ ቅዱስ ይጠመቃሉ።
መ. አማኞች የወንጌል ተቃዋሚዎችን የመመከት ብርታት ያገኛሉ።
ሠ. ችግሮች ሲያጋጥሟቸውና ውሳኔ መወሰን ሲያስፈልጋቸው አማኞች በእግዚአብሔር ቃልና በጸሎት ላይ ይደገፋሉ።

ለመንፈሳዊ ሕይወታችን፣ ለብርታት፣ ለራዕይ፣ ለተዋጣ አገልግሎት፣ በፈተና ወቅት ረድኤት ለማግኘት፣ በግል ሕይወታችንም ድል እንድናገኝና ዕድገትም እንዲኖረን ምን ያህል በመንፈስ ቅዱስ ላይ መደገፍ እንዳለብን ተመለከትክ? መንፈስ ቅዱስን አምልከው። በሕይወትህ ያለውን የእርሱን ሕልውና ውደደው። እርሱ እንድትሆን የሚፈልግብህን ዓይነት መንፈሳዊ ሰው ለመሆን የማደግና የመጎልመስ ፍላጎት ይኑርህ። በእንተ ውስጥ ሊኖር የመጣው የመንፈስ ቅዱስ አሳብ ምን ጊዜም ከእንተ ጋር ይሁን። ለድምፁ፣ ለምልጃው፣ ለተግሳጹና ለምክሮቹ ንቁ ልቦና ይኑርህ። አስተሳሰብህ፣ ንግግርህና ምግባርህ በሙሉ መንፈስ ቅዱስ በሕይወትህ ያለውን መሪነት የሚያንፀባርቅ ይሁን። የዚያን ጊዜ መንፈሳዊ ሕይወትህ የበለፀገ ኑሮህም በእርግጥ የተሳካ ይሆናል።

የመከራ ፈተና

እውነት ወይም ሐሰት። መግለጫው እውነት ከሆነ እውነት ሐሰት ከሆነ ደግሞ ሐሰት በል።

1. የመለኮት ማንነት መታወቂያዎች የሆኑት ዘላለማዊነት፣ ሁሉን ቻይነት፣ በሁሉ ሥፍራ መገኘትና ሁሉን አዋቂነት ለመንፈስ ቅዱስም ሊጠቀሱ ይችላሉ።

2. በሐዋርያው ጳውሎስ መልእክቶች ለመለኮት ብቻ የሚጠቀስው "ጌታ" የሚለው ቃል ለመንፈስ ቅዱስም ሊጠቀስ ይችላል።

3. የሐዋርያዊው የበንብት ቃልና በውሃ ጥምቀት ሥርዓት የሚነገረው ቃል በሥላሴ ውስጥ ባሉት እካላት መካከል ያለውን ጉልህ አኩልነት ያሳያል።

4. በማንነቱ መንፈስ ቅዱስ አካል የሌለው ከንፋስ ምንነት ጋር ተመሳሳይ የሆነ ማንነት ያለው ነው።

5. በአካል ደረጃ የሚከናወኑ ተግባሮች፣ ግላዊ ስሞች፣ ግላዊ ግንኙነቶች፣ ግላዊ ተውላጠ ስሞች በግል እርምጃ ሊወሰዱ ወይም ሊወሰድባቸው መቻል መንፈስ ቅዱስ አካላዊነት አንዳለው አጠንክረው የሚያመለክቱ ናቸው።

6. እኛ ውሱን በለሆንና መንፈስ ቅዱስ ደግሞ ወሰን የሌለው በመሆኑ ስለ አካላዊነቱም ሆነ ስለ ሥራው ምንም ነገር መረዳት አንችልም።

7. መንፈስ ቅዱስ ባልተቀደሱና ኃጢአተኛ በሆኑ ሰዎች ሕይወት አይሰራም።

8. በአማኞች ምትክ በሚያቀርበው ምልጃ አማካይነት አማኞች የመንፈስ ቅዱስን ልዩ ረድኤት ይቀበላሉ።

9. ከእግዚአብሔር ቃል ይልቅ የእንድ ሰው የግል ልምምድ በእምነትና በተግባር መመሪያነት የበለጠ አስተማማኝ እንደሆነ ጴጥሮስ አስተምሯል።

10. የመንፈስ ቅዱስ አሠራር ልዩነቱ የሚታየው በብሉይ ኪዳን ለእስራኤል በነበረው የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎትና በአዲስ ኪዳን አማኞች ሕይወት ውስጥ ማደሩ ነው።

11. የመንፈስ ቅዱስ አገልግሎት ወንጌልን ወንጌል ወዳልደረሳቸው ማድረስና በመንግሥት ባለሥልጣኖች ፊት የወንጌል ተቃዋሚዎችን በመመከት ላይ የተወሰነ ነው።

12. ችግር በሚያጋጥሙን ጊዜ መንፈስ ቅዱስ የታመነ አስተዳዳሪ ነው።

13. አማኙ በኃጢአተኛ ሕይወቱ ልዩ ድል እያገኘ እንዲቀጥል መንፈስ ቅዱስ ሥፍራ ከተሰጠው አማኙ በይበልጥ ጌታውን እየመሰለ ይሄዳል።

14. በመንፈስ ቅዱስ የሚመራ ሕይወት የሚጀምረው በመንፈስ ቅዱስ በምንሞላበት ጊዜ ነው።

15. አማኙ የመንፈስ ቅዱስን ጥምቀት ከተቀበለ ከሙሉ መንፈሳዊ ብስለት ደረጃ ላይ ደርሷል።

16. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ለመንፈሳዊ ሕይወት ዕድገት መሠረት ነው።

17. መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር አብ ጋር ስሚኖረን የዘላለም ሕይወት መያዣ ሆኖ ተሰጥቶናል።

18. በዘይት መቀባት የመንፈስ ቅዱስን ንጹህነት ይወክላል።

19. የመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ከሕይወት ውሃ ጋር ተነፃፅሯል።

20. በአማኙ ውስጥ የሚያድረው መንፈስ ቅዱስ አማኙ ሁልጊዜ በቅድስና እንዲኖርና ውጤታማም እንዲሆን ዋስትና ነው።

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስ

1. ሀ. 4 ለ. 3 ሐ. 1 መ. 2

7. "ሀ"፣ "ሐ" እና "መ" መልሶች እውነት ናቸው። መልስ "ለ" ሐሰት ነው። (በሞቱና በትንሳኤው ኢየሱስ በሰይጣን ላይ ድል ተቀዳጅቷል።

2. በ "ሀ"፣ "ሐ" እና "መ" የቀረቡት መልሶች ለመንፈስ ቅዱስ መለኮትነት ማስረጃ ናቸው። መልስ "ለ" የመለኮትነት ማበረጃ አይደለም፣ "እጽናኝ" የሚለው ቃል የመንፈስ ቅዱስን ብዙ ተግባራት ከሚገልጹት አንዱ ነው።

8. መልስህ ከዚህ በታች ካለው ጋር ሊመሳሰል ይገባል፦

ሀ. በዳግም ልደት መንፈስ ቅዱስ ወደ እግዚአብሔር ቤተሰብ ያመጣናል።
ለ. ለመመስከር ኃይል ይሰጠናል።
ሐ. ያስተምረናል።

መ. በእኛ ሥፍራ ወደ እግዚአብሔር አብ ይግልድልናል።
ሠ. በፈቀድንለት መጠን ወደ ድልና ክርስቶስን ወደሚመስል ሕይወት ይመራናል።
ረ. መንፈሳዊ ፍሬን (ክርስቶስን የመስለ ባህርይ) ያስገኝልናል። ይህንን የሚያደርገው ሕይወታችንን እንዲቆጣጠር ስንፈቅድለት ነው።

3. ሀ. 2 ለ. 3 ሐ. 4 መ. 1 ሠ. 4

9. ሀ. መፍሰስ ለ. ጥምቀት ሐ. መሳት

4. ሀ. 3 ለ. 1 ሐ. 2

10. የእንተ መልስ ከሚከተለው የእኔ መልስ ጋር ይስማማ ይሆናል።
እሳት፡- መንፈስ ቅዱስ ያጠራኛል።
ርግብ፡- በእርጋታ ይመራኛል።
የቅባት ዘይት፡- የተዋጣ አገልግሎት እንድሰጥ መንፈስ ቅዱስ ይቀባኛል
ስጦታ፡- መንፈስ ቅዱስ አብ የሰጠኝ መልካም ስጦታ ነው።
ሕያው ውሃ፡- ሕይወትን እየሰጠኝ እስክትረፈረፍ ይሞላኛል።
ማሕተም ወይም መያዣ፡- መንፈስ ቅዱስ በእግዚአብሔር መንግሥት ሥፍራ እንደሚኖረኝ የሚያረጋግጥልኝ ዋስትናዬ ነው።
እስትንፋስ፣ ነፋስ፡- መንፈስ ቅዱስ በእኔ ውስጥ የዘላለም ሕይወት እስትንፋስ ይተነፍስልኛል (ይሰጠኛል)።

5. እካል ባለው ሕልውና ብቻ ሊከናወኑ የሚችሉ ሆኖም እካል በሌለው ኃይል ሊሰሩ የማይችሉ ተግባራትን እንደሚያከናውን ይገልጻለ።

11. ሀ. 1 ሐ. 2 ሠ. 2
ለ. 2 መ. 1 ረ. 1

6. ከ"ሐ" እና ከ"ሰ" በስተቀር ሁሉንም መክበብ ይኖርብሃል።
ሁለቱ ለመንፈስ ቅዱስ ሊጠቀሱ አይችሉም።

12. ሀ. 3 ሐ. 1 ሠ. 4
ለ. 2 መ. 5

5 መላእክት
የብርሃንና የጨለማ ሠራዊት

ትምህርት


የሰይጣን የጥፋት መንፈሳዊ ኃይሎች የመከላከል አቅማችንን በማዳከም መንፈሳዊ ሕይወታችንን መግደል ይፈልጋሉ። በእግዚአብሔር ላይ እስከታመንን ድረስ ከጥቃት የተጠበቅን እንሆናለን። ከፍተኛ የሆኑት የእግዚአብሔር መንፈሳዊ ኃይላት ጠላታችንን ሰይጣንን መቃወም እንድንችል ረድኤት ያቀርቡልናል። ስለሆነም መንፈሳዊ ውጊያ ስለ መላእክት ለምናደረገው ጥናት መሠረት ይሆንልናል።

በከፍል እንድ ስለ እግዚአብሔርና በፍጥረቱ ላይ ስላለው ሉአላዊ አገዛዝ ተምረናል። እሁን ደግሞ በመለኮታዊ አገዛዙ ሥር ወዳሉት ወደ መላእክትና የስዎች ኃጢአት ወዳስከተለው ችግር መለስ ብለን እንመለከታለን። በሚከተሉት ሦስት ክፍለ ትምህርቶች የኃጢአትን መነሻ ምክንያት ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር ግዛት ሥር ባሉት ሁሉ ላይ ያስከተላቸውን ዘለቄታዊ ውጤቶች ጭምር እብረን እንመለከታለን።

ስለ ንጉሣችንና በእርሱ አመራር ሥር ስላሉት የመላእክት ኃይላት በዚህ ትምህርት አማካይነት ስናጠና በደሙ የተዋጁ አያሌ ሰዎችን ወደ ፍጻሜው ድል እንደሚመራ በመገንዘብ ጌታን በይበልጥ እንድታከብረው ጸሎቴ ነው።

የክፍለ ትምህርቱ እከፋፈል

- የመላእክት ባሕርይ
- የመላእክት ምግባራዊ ባህርያት
- የመላእክት ብዛት
- የመላእክት እደረጃጀትና አሰራር



የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

- የእግዚአብሔር ቃል ላይ በተመሠረቱ ጥቅሶች የመላእክትን የማንነት መታወቂያ፣ ባህርይ፣ ብዛትና፣ አደረጃጀት፣ መግለጽ።
- የለይጣንንና የክፉ መላእክትን እንላለና ባሕርይ መግለጽ።
- አማኙ በክፋት ኃይላት ላይ የመጨረሻውን ድል ለመቀዳጀቱ የእግዚአብሔር ሁሉን ቻይነት ዋስትናው እንደሚሆን መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ መስጠት።
- መላእክት ለለሚሰጡት ረድኤትና አገልግሎት በይበልጥ ማመስገን

የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. ለዚህ ትምህርት መሠረት ይሆንህ ዘንድ ኤፌ 6:10-18፣ 2ጴጥ 2:1-22 የይሁዳን መልእክት አንብብ።

2. በክፍለ ትምህርት አንድ በተለጠው መመሪያ መሠረት ይህንን ትምህርት አጥና። ይህንን ትምህርት በመረዳት በኩል አለፈላጊ የሆኑ ብዙ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶቹ አሉ። ጥቅሶችን ሁሉ ማንበብህን እርግጠኛ ሁን፣ የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎችንም በሙሉ መልሳቸው። ከዚህ በኋላም እንደተለመደው የመመዘኛ ፈተናዎችን ስራ።

የትምህርቱ ዋና ክፍል

የመላእክት ባሕርይ

የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ የሚከተለውን ምክር ይሰጣል። "እንግዶችን መቀበል አትርሱ፣ በዚህ እንዳንዶች ሳያውቁ መላእክትን እንግደነት ተቀብለዋል" (ዕብ 13:2)።

መላእክትን በሚመለከተው በዚህ ጥቅስ ልዩ ለለሆነው ባሕርያቸው እንዳንድ ነገሮችን እንመለከታለን። ያልተለመዱ በመሆናቸው በመላእክት ዙሪያ ሚለጥራዊነት ሰፍኗል። ይህ እውነት በብሉይም ሆነ በአዲሰ ኪዳን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ተደጋግሞ ተገልጸአል።

እያንዳንዱን የመላእክትን መኖር የሚመለክሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሰናነብ መላእክትን በሚመለከት ምን ልንማር እንችላለን? ጅማሬያቸው ምን ይመለል ነበር? ባህሪዎቻቸውስ ምንና ምን ናቸው? ለእነዚህ ጥያቄዎች መልሶችን ማግኘታችን ለለ መላእክት የመፈጠር ዓላማና በእኛም ሕይወት ለሳላቸው እስፈላጊነት የበለጠ እንድንረዳ ይረዳናል። ለለ መላእክት እነሳስና ለለ ባህሪዎቻቸው መጽሐፍ ቅዱስ የሚያቀርብልንን እንዳንድ እውነቶች እስቲ እንመርምር።

ጅማሬያቸው

ዓላማ 1 የመላእክትን ጅማሬና ባህሪዎቻቸውን የሚመለከቱ መግለጫዎ ችን ማጠናቀቅና መምረጥ

መላእክት ምንድን ናቸው? መላእክት የእግዚአብሔር መልእክተኞች ወይም አገልጋዮች የሆኑ ውሱን መደቦች ወይም ፍጡራን ናቸው። ክለው የላቀ እውቀትና ኃይል አላቸው። እንዳንድ መላእክት በቅድሰናቸው ና በፈቃደኛነት የእግዚአብሔርን ሃሳብ በመፈጸማቸው የእግዚአብሔርን እቅድ አዎንታዊ በሆነ መንገድ ያገለግላሉ። በእግዚአብሔር ላይ ያመጹ ሌሎች መላእክት ደግሞ በፈጸሙት በደል ምክንያት ለዘላለም ከእግዚአብሔር ተለይተዋል። ይህ ዘላለማዊ የሆነ ከእግዚአብሔር መለየት በክርስቶስ በኩል ደህንነት ለቀረበለት ኃጢአተኛው የሰው ልጅ እግዚአብሔር ያሳየውን የተለየ ጸጋ በግልጥ ያሳያል።

መጽሐፍ ቅዱስ በተጸፈባቸው የጥንት ቋንቋዎች መላእክት የሚለው ቃል መልእክተኛ የሚል ትርጉም ነበረው። እንዳንድ ጊዜ መልእክተኛ የሚለው ቃል ለዎችን ያመለክታል (ዘሚል 2:7 ካህን ማለት ነው)። ቃሉ በተለያየ መንገድ ጥቅም ላይ በመዋሉ ትክክለኛውን ትርጉም መወሰን ይቻል ዘንድ ቃሉ የገባበትን እያንዳንዱን አውድ መመርመር ይኖርብናል። ይሁን እንጂ በአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱስ ለለ መላእክት ዘሚናገርበት ጊዜ

የሚያመሰክተው ለእግዚአብሔር ልዩ መልእክተኞች እንደሆኑ ስለተገለጹት መንፈሳዊና ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃልዋንን ነው።

መላእክት ከየት መጡ? መዝሙረኛው ስማያዊ አካላት ከሆኑት ከፀሐይ፣ ከጨረቃና ከከዋክብት *ጋር* መላእክትና የስማይ ሠራዊት ሁሉ በእግዚአብሔር እንደተፈጠሩ ይናገራል (*መዝ* 148:2-5)። የክርስቶስን የአፈጣጠር ተግባር ስተመለከተ ዮሐንስ ከማንኛውም የላቀ መግለጫ ይሰጣል። "ሁሉ በርሱ ሆነ ከሆነውም እንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም" (ዮሐ 1:3)። መጽሐፍ ቅዱስ የማንኛውንም ነገር ሕላዌ ከእግዚአብሔር ሕልውና *ጋር* በግልጽ ስለሚያያይዘው መላእክትም ፍጡራን *መሆናቸውን* እናውቃለን።

(1). የሚከተሉትን መግለጫዎች አጠናቅቃቸው፡-

ሀ. ቆላ 1:16፡- ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ. . .(መላእክትን ጨምሮ) እንደፈጠረ ይገልጸል።
ለ. ፩1ጢሞ 6:13-16፡- እግዚአብሔር ብቻ ለሁሉም (*መላእክትን* ጨምሮ) . . . እንደሚሰጥ እናነባለን።

መጽሐፍ ቅዱስ ጊዜውን ስላልገለጸልን *መላእክት መቼ* እንደተፈጠሩ በትክክል እናውቅም። በፍጥረቱ መልእክ የሆነው ስይጣን ከሰው ልጆች *ጋር* ባለው ግንኙነት ትኩረትን ያገኘው ከዚህ ወቅት ጀምሮ *በመሆኑ መላእክት* በዘፍጥረት 3 ከተዘገቡት ሁኔታዎች ቀደም ብለው እንደተፈጠሩ እናውቃለን። እንደማንኛቸውም የሚያመዛዝኑ ፍጡራን ሁሉ *መላእክትም* አስመሞት ማለትም ፍጹም የማይቋረጥ ሕላዌ (ሉቃ 20:36) ተሰጥቷቸዋል።

(2). ስለ ጅማሬያቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ በምናገኘው መረጃ መሠረት *መላእክት* ናቸው ብለን መደምደም እንችላለን።

ሀ. ምን ጊዜም የነበሩ የማይሞቱ ፍጡራን
ለ. የማይቋረጥ ሕልውና ያላቸው የማይሞቱ ፍጡራን
ሐ. ከሰው የላቀ ኃይልና ጥበብ ያላቸው ሆኖም እንደሰው ሟች የሆኑ ፈጡራን
መ. ከመለኮት *ጋር* አንድ ዓይነት የሆኑ ዝርያዎች

ባሕርያቶቻቸው

የመላእክትን ጅማሬ በጠቀስንበት ጊዜ ከባሕርያቸው አንዱ የሆነውን ፍጡር *የመሆናቸውን* ነገር *ተመ*ልክተናል። የእግዚአብሔርን ቃል በምንመረምረበት ጊዜ ትኩረት የሚያገኙ ብዙ ሌሎች የማንነት *መታወቂ*ያዎች ይከስታሉ።

መላእክት መንፈሳዊ ፍጡራን ናቸው። ዕብ 1:14 እንደዚህ ይላል፡- "ሁሉ *መዳንን* ይወርሱ ዘንድ ስላላቸው ለማገዝ የሚላኩ፣ የሚያገለግሉም *መናፍስት* አይደሉምን?" ስዎችን *መናፍስት* ናቸው ማለት አንችልም። ምክንያቱም ተዳሳሽ አካል (*ሥጋ*) እንዲሁም ተዳሳሽ ያልሆነ አካል (መንፈስ) በእንድነት የያዘ ማንነት አላቸው። መላእክት *መናፍስት* በመሆናቸው ቁሳዊ አካል እንዳላቸው እድርገን ልንቆጥራቸው እንችልም። በኤፌ 6:12 ላይ የተንፀባረቀው ሃሳብም ይሄው ነው። "*መጋደ*ላችን ከደምና ከ*ሥጋ ጋር* አይደለምና፣ በስማያዊ ሥፍራ ካሉ ከክፋት *መንፈሳዊ*ያን ሠራዊት *ጋር* ነው እንጂ።" (ይህ ጥቅስ የሚናገረው የስይጣንን ሥራ ስሰሚያከናውኑት ስለ ርኩሳን *መላእክት* ነው።)

መላእክት አዘውትረው ራሳቸውን በሰው እምሳል እንደገለጹ (*መሳ* 6:11-24፣ ዮሐ 20:12) የእግዚአብሔር ቃል *ያመ*ለክታል፣ ይሁን እንጂ እነዚህ ያልተለመዱ *መላእክት* በመደበኛ የሕልውና ገጽታቸው ግዙፍ አካላት አላቸው ማለት እይደለም። ይልቁኑም ተዳሳሽ አካል እንደለበሱ ሆነው ራሳቸውን የሚገልጹት ሁኔታውን ከሰው ልጆች *ጋር* ግንኙነት ስማደረግ ሲጠቀሙበት ነው። ቁሳዊ አካል እንደለበሱ ሆኖ መገለጥ የመደበኛ ሕልውናቸው እንዱ ክፍል ስላልሆነ *መላእክት* ማደግ ማርጀት ወይም መሞት የተባሉ ነገሮችን እያውቁም።

መላእክት አካል ያላቸው ፍጡራን ናቸው። *መላእክት* መሠረታዊ የሆኑ የአካልነት ገጽታዎችን ማለትም እውቀት፣ ስሜትና ፍቃድ እንዳላቸው ያሳያሉ። በብሉይ ኪዳን ይኖሩ በነበሩ ስዎች እ*መለ*ካከት *መላእክት* እውቀትን የማገናዘብ ችሎታ እንደነበራቸው የሚጠቁም ሃሳብ በ2ኛ ሣሙ 14:20 ላይ ቀርቧል። እርኩሳን *መላእክት* እንኳ ከሰው ልጆች የላቀ የእውቀት ደረጃ እንዳላቸው በሉቃ 4:34 ተገልጿል። ራእ 12:12 ርኩሳን *መላእክት* ስሜትን (ብስጭትን ወይም ቁጣን) *የመግ*ለጽ ችሎታ እንዳላቸው ይጠቁመናል። በጣም አ*ዎ*ንታዊ በሆነ *መ*ንገድ ቅዱሳን *መላእክት* ስሜቶቻቸውን ሐሴት በማድረግ እንደሚገልጹ ጌታ ኢየሱስ በሉቃ 15:10 ላይ ተናግሯል። ስያጣን ፈቃዱን እንዲያደርጉ ስዎችን የማጥመድ ችሎታ እንዳለው ጳውሎስ በ2ጢሞ 2:26 ጠቅሷል። እነዚህ እንግዲህ *መላእክት* የእካልነት *የመ*ታወቂያ ባህርያት እንዳላቸው ከሚገልጹት ብዙ የእግዚአብሔር ቃል ክፍሎች ጥቂቶቹ ምሳሌዎች ናቸው።

መላእክት ፆታ የላቸውም። ምንም እንኳን እንዳንዶቹ *መላእክት* (እንደ ገብርኤልና ሚካኤል) ለወንድ (ተባዕታይ) የሚሰጥ ስም ቢሰጣቸውም *የመላእክት* አ*መዳ*ደብ በፆታ ላይ *የተመ*ሠረተ እይደለም። *መጽሐፍ* ቅዱስ *መላእክት* እንደማያገቡና ስጋብቻም እንደኖቸው ለሌላው እንደማይሰጡ (ማቴ 22:30) ይነግረናል። *መላእክት* እርስ በርሳቸው ስለማይራቡ በትክክል የምንገልጻቸው እንደ አንድ ማህበር (ሠራዊት) ነው እንጂ እንደ ዝርያ አይደለም። በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ቃል *መላእክትን* እንደ እግዚአብሔር ልጆች እንደጠቀሳቸው የምናስታውስ ቢሆንም *የመላእክት* ልጆች የሚል ግን ፈጽሞ እልተጠቀስም (ኢዮብ 1:6 12:1138:7)።

ቀደም ሲል እንደተገነዘብነው መላእክት ከሰው ልጆች የላቀ እውቀት አላቸው። የኢየሱስ እንጋገር ጥበባቸው ሰፊ እንደሆነ የሚያመለክት ነው። "ስለዚያች ቀንና ሰለዚያች ሰዓት ግን. . . የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ . . . የሚያውቅ የለም" (ማቴ 24:36)። እውቀታቸው ከሰው የላቀ ይሁን እንጂ ውሱን ነው። ሰለሚመጣው ክብር ሲናገር ጴጥሮስ "ይህንንም ነገር መላእክቱ ሊመለከቱ ይመኛሉ" (1ጴጥ 1:12) ብሎአል።

የመላእክትን ባሕርይ ቀረብ ብለን ስንመረምር ከሌሎቹ ባሕርያቶቻቸው ሁሉ የበለጠ ትኩረት የተሰጠው ኃይላቸው ነው ብለን እንድንደመድም እንደሳፈራሰን። መላእክት ከሰዎች ይልቅ ብርቱ እንደሆኑ ጴጥሮስ አሰታውቋል (2ጴጥ 2:11)። መዝሙረኛው ስለ መላእክት ሲገልጽ እንዲህ ብሏል። "ቃሉን የምትፈጽሙ፣ ብርቱዎችና ኃያላን የቃሉንም ድምጽ የምትሰሙ መላእክቱ ሁሉ. . ." (መዝ 103:20)። ጳውሎስም ስለ እነርሱ ሲጠቅስ "ጌታ ኢየሱስ ከሥልጣኑ መላእክት ጋር . . ." (2ተሰ 1:7) ብሏል።

ርኩሳን መላእክትን በተመለከተ ሰድጋሚ ትኩረት የተሰጠው ባሕርይ የኃይላቸው ጉዳይ ነው። "የዚህ ዓለም ገዢ" (ዮሐ 12:31)፣ "ኃይለኛ ሰው" (ሉቃ 11:21)፣ "የጨለማው ሥልጣን" (ሉቃ 22:53)፣ "ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዢዎች . . ." (ኤፌ 6:12)፣ "ብጠላትም ኃይል ሁሉ . . ." (ሉቃ 10:19)። ሠይጣን ኢየሱስን በፈተነው ጊዜ የዓለም መንግሥታት ክብራቸውም ለእኔ ተሰጥቶአል ለምወደውም ለማንም እሰጠዋለሁና ለእንተ እሰጥሃለሁ" (ሉቃ 4:6)።

ይሁን እንጂ ጥበባቸውና ኃይላቸው ከሰው የላቀ ቢሆንም አነዚህ የመላእክት ባሕርያት ውሱን ናቸው። ስዚህ ዘመን መጨረሻ ሰይጣንን ለማሰርና ወደ ጥልቁ ለመጣል የሚያበፈልገው አንድ መልእክ ብቻ ነው (ራእ 20:2-3)። ሆኖም ይህ አሰራት ከመከናወኑ ሰፊት ሰይጣንና መላእክቱ ከመላእክት አለቃ ከሚካኤልና ከመላእክቱ ጋር ይዋጋሉ። በሰማያት በሚደረገው ጦርነት ሰይጣን ይሸነፋል። ከዚያም ወደ ውጭ ይጣላል (ራእ 12:7-9)። በዳን 10 እንደምንመለከተው የሰዎችንና የመንግሥታትን ጉዳይ በሚመለከት ቅዱሳንና ርኩሳን መላእክት በውጊያ ላይ ናቸው። የመላእክት አለቃ ሚካኤልም ሆነ (ይሁዳ 9) ሰይጣን (ኢዮብ 1:2) ገደብ የሌለው ኃይል የላቸውም።

መላእክት በአንድ ጊዜ በሁሉም ሥፍራ መገኘት አይችሉም። ስለ ሚያከናውነው ሥራ ለእግዚአብሔር መልስ በሚሰጥበት ጊዜ "ምድርን ሁሉ ዞርኋት፣ በርሷም ተመላለስሁ" (ኢዮ 1:7፣ 1ጴጥ 5:8) ብሎ ነበር። የጌታ መላእክትም ዘገባ በሚያቀርቡበት ጊዜ "በምድር ላይ ተመላለስን" (ዘካ 1:11) ብለው ነበር። ይህ ከቦታ ወደ ቦታ መንቀሳቀስ ጊዜ የሚፈጅ እልፎ እልፎም መዘግየትን የሚጠይቅ ይሆናል (ዳን 10:5፣12-14)፣ ይህ የውሱንነት መረጃ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚሳተፋቸው መንፈሳዊ ውጊያዎች ለምን ለተራዘመ ጊዜ እንደሚቀጥል መግለጫ ይሰጠናል።

በመጨረሻም መላእክት የከበሩ ሰዎች እለመሆናቸውን ልንረዳ ይገባናል። መጽሐፍ ቅዱስ በስማያዊቱ ኢየሩሳሌም በሚገኙት "አእላፋት መላእክት" እና "ፍጹማን በሆኑት የጻድቃን መንፈሶች" (ዕብ 12:22-23) መካከል ልዩነት እንዳለ ያስገነዝባል። ይህን የመስለው ልዩነት በዕብ 2:16 ላይም ይታያል። "የአብርሃምን ዘር" ይዞአል እንጂ የያዘው የመላእክትን አይደለም።

ሰአርግጥ የሰው ልጅ በአንድ ወቅት "ከመላእክት እጅግ ጥቂት. . . " አንስ ነበር (መዝ 8:4-5)። ሆኖም ወደ ፊት ሰው ከመላእክትም የላቀ ይሆናል (ዕብ 2:7)። ጳውሎስ "በመላእክት እንኳ እንድንፈርድ አታውቁምን?" ብሏል (1ቆሮ 6:3)። እንግዲህ በዚህ የፍርድ አሰራር ዝቅተኞቹ ወይም ባነስ ደረጃ ላይ የሚገኙት ከአነርሱ በበለጡት ላይ እንደማይፈርዱ እንረዳለን።

(3). መላእክት በባሕርያቸው ውሱንነት አንዳላቸው የሚያሳዩ ሦስት መንገዶችን ግለጽ።

(4). ከዚህ ቀጥሎ ከተራ ቁጥር 1-8 ያሉትን የመላእክት ባሕርያት ከሀ-ሸ ካሉት ትክክለኛ መግለጫዎች ጋር አቀናጃቸው።

1. ፍጡራን ናቸው	5. እውቀት አላቸው
2. መንፈስ ናቸው	6. ኃይለኞች ናቸው
3. አካል አላቸው	7. በሁሉም ሥፍራ አይገኙም
4. ዖታ የላቸውም	8. የከበሩ ሰዎች አይደሉም

ሀ. አርሰ በርሳቸው አይዋለዱም ወይም ቁጥራቸው አይጨምርም።
ለ. በአንድ ጊዜ በሁሉም ሥፍራ ሊገኙ አይችሉም።
ሐ. የመሪያቸውን ፈቃድና ዓላማውን መፈጸም ይችላሉ።
መ. ከሰዎች የላቀ እውቀት አላቸው።
ሠ. ተዳሳሽ አካላዊ ሕልውና የላቸውም።
ረ. ሕልውና ያገኙት ሰጊዜ ውሰጥ በአንድ ወቅት ነው።
ሰ. በእግዚአብሔር ቃል ውሰጥ ከሰው ልጆች ጋር ያላቸው ልዩነት ጥርት ብሎ ተገልጿል።
ሸ. እውቀት፣ ስሜትና ፈቃድ አላቸው።

የመላእክት ምግባራዊ ባሕርያት

መላእክት በቅድስና የተፈጠሩ ናቸው

ዓላማ 2 የእግዚአብሔርን ቃል መሠረት በማድረግ የመላእክትን ምግባራዊ ባህርይ በሚመለከት እውነተኛ የሆኑትን መግለጫዎች መምረጥ

ቀደም ባሉት ገጾች ስለ ቅዱሳንና አርኩሳን መላእክት ተመልክተናል። ስዚህ ክፍል የምናጠናው ጥናት መላእክት ሁሉ ቅዱሳን ሆነው

እንደተፈጠሩ ሆኖም አንዳንዶቹ ከተቀደሰ ሥፍራቸው እንደወደቁ የሚያመለክት ይሆናል። ውድቀታቸውም በአጠቃላይ በዓለም ላይ ትልቅ ውጤት አስከትሏል።

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መላእክት ጅማሬ የሚናገረው በጣም ጥቂት ነው። ይሁን እንጂ በመፍጠር ተግባሩ መጨረሻ ላይ "እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ፣ እነሆም እጅግ መልካም ነበር" የሚል ቃል እናነባለን (ዘፍ 1:31)። በእርግጥ ይህ አባባል መላእክት በተፈጠሩ ጊዜ የነበራቸውን በቅድስና ፍጹም መሆንን የሚያጠቃልል ነበር። ሆኖም የእግዚአብሔር ቃል አሳዛኝ ስለሆነው ውድቀታቸውም ይናገራል። መላእክት ትክክለኛና የተላላተ ተግባርን ለመፈጸም እንዲሁም ትክክለኛ የምግባር መመሪያን ለይቶ ለማወቅና ለመከተል ያላቸውን ችሎታ አለኪ እንመልከት።

(5). ከዚህ በታች ያለውን እያንዳንዱን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ አንብበህ የቀረቡትን መግለጫዎች አጠናቃቸው።

ሀ. ዮሐ 8:44 የለይጣንን ውድቀት ካለከተሉት ኃጢአቶች አንዱ
ለ. 2ጴጥ 2:4 መላእክት እግዚአብሔር አልራራላቸውም።
ሐ. ይሁ ቁ. 6 አንዳንድ መላእክት አልጠበቁም ይልቁንም
መ. 1ጢሞ 3:6 ለሰይጣን ውድቀት ዋነኛ ምክንያቶች ከሆኑት አንዱ ኃጢአት ነበር።

መላእክት የራሳቸውን ምርጫ አደረጉ

እንደተመለከትነው መላእክት ሁሉ ሲፈጠሩ ፍጹማን ነበሩ። በመጀመሪያ ምኞታቸው ወይም ፍቅራቸው ወደ ፈጣሪያቸው ያዘነበለና የአርሱንም ፈቃድ ለመፈጸም የቀና ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ዝርዝር ነገር ባይነግረንም በዚያን ወቅት ኃጢአትን ለማድረግ ወይም ላለማድረግ ችሎታ ነበራቸው ብለን እናምናለን። ከፈጣሪያቸው ጋር ስለ ነበራቸው አቋምና የግንኙነት ሁኔታ መረዳት ወይም ግንዛቤ እንደሚኖራቸው ግልጽ ነው። መታዘዛቸው ወይም አለመታዘዛቸው የወደፊቱን እጣቸውን እንደሚወስንም ሳያውቁ አይቀሩም።

ኃጢአት ለማድረግ ወይም ላለማድረግ የመምረጥ ኃይል በነበራቸው ጊዜ መላእክት እግዚአብሔርን እንዲታዘዙና ባቋማቸውም እንዲጸኑ አልተገደዱም። ምርጫቸው ፍጹም በፈቃዳቸው ላይ የተመሰረተ ነበር። ከመላእክቱ ሠራዊት ከፊሉ በወደቁ ጊዜ በዚያን አካባቢ ስለ ተፈጸሙት ዝርዝር ክንውኖች ምንም መረጃ የለም። ይሁን እንጂ ለይጣን ውድቀት የደረሰበት በትዕቢት ምክንያት እንደሆነ ጳውሎስ በመለኮታዊ መገለጥ አመልክቷል (1ጢሞ 3:6)።

በመሠረታዊ አቀራረባቸው ስለ ምድራዊ ነገሥታት የሚናገሩ አያሌ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ስለ ሰይጣንም በምሳሌ የሚናገሩ ይመስላሉ።

ለምሳሌ ያህል በሕዝ 28:12-19 የጢሮስ ንጉስ በውበቱ ከመጠን በላይ ለለታበየ እንደወደቀ ተነግሯል። ይህም ትዕቢት ራሱን በትክክል የመምራት ወይም ሚዛናዊ ፍርድ የመስጠት ችሎታውን አጠፋበት።

በኢሳ 14:12-15 የባቢሎን ንጉሥም ከመጠን ባለፈ ትዕቢትና ምኞች የተነሳ ለጥፋት ተዳርጎ ነበር። እነዚህ ምሳሌዎች በምሳሌያዊ አነጋገር ስለ ሰይጣን ውድቀት ቢናገሩም ባይናገሩም የራሳቸውን ፈቃድ ለመለማመድ በወሰዱት እርምጃ ከመላእክት ሠራዊት አንዳንዶቹ የሥልጣን ሰፍራቸውንና መኖሪያቸውን ለመተው እንደመረጡ እናውቃለን (ይሁዳ 6)።

ሰይጣንን ኃጢአት እንዲፈጽም ያደረገው ዝንባሌ ከመላእክት በቁጥር ብዙዎቹን የበከለ ይመስላል። ራእ 12:4 ከመላእክት ሲሶው ለይጣን በእግዚአብሔር ላይ ባደረገው ዓመፅ ስለተከተሉበት አጋጣሚ የሚጠቅሰ ሊሆን ይችላል። ያም ሆነ ይህ ለይጣን የውሸት መንፈሳዊ ቁንጮ እንደሆነ እናውቃለን (ዮሐ 8:44)። ለሰይጣንና ላመጹት ለሌሎች መላእክት በሙሉ ምርጫው ከእግዚአብሔርና ከፍላጎቶቹ ይልቅ ራሰንና የግል ፍላጎትን የመምረጥ ጉዳይ ነበር። ውጤቱ ጥፋትን ያመጣ ነበር፣ የተከተለውም ፍርድ፣ "እግዚአብሔር ኃጢአትን ላደረጉ መላእክት ሳይራራላቸው . . . አሳልፎ . . ." ሰጣቸው (2ጴጥ 2:4)።

ለሰዎች መንፈሳዊ ፍላጎት መልስ እንዲሆን የታቀደውን ደኅንነት የወደቁት መላእክት ሊያገኙት አይችሉም። ያልተቀደሱት መላእክት በክፉው ክልል ውስጥ ምንጊዜም መኖራቸውን ይቀጥላሉ (ማቴ 6:13፣13:9፣ 1ዮሐ 5:18-19)። ይህም ለእኛ እግዚአብሔርን እንዳንቃወመውና የሰጠንን ጸጋ በቸልተኝነት እንዳናክፋ የዘወትር ማስጠንቀቂያ ይሆንልናል።

ኃጢአት ያደረጉ አንዳንድ መላእክት ተፈረደባቸው፣ ከዚያም "የሰይጣን መላእክት" አካል ሆኑ (ማቴ 25:41)። ሌሎች ኃጢአት አላደረጉም፣ የእግዚአብሔር ቅዱሳን መላእክት ሆነው ከአብ ጋር ይቆያሉ (ማር 8:38)። የእግዚአብሔር ቃል ከዚያ በኋላ ስለተፈጸመ የመላእክት አመፅና ስለተከተለው ፍርድ አይነግረንም። ስለሆነም መላእክት በውሳኔያቸው መሠረት የጸኑ ይመስላል፣ ማለትም የአብን ፈቃድ ለማድረግ የመረጡት ለዘላለም ቅዱሳን ይሆናሉ፣ የራሳቸውን ፈቃድ ሊያደርጉ የመረጡት ደግሞ ለዘላለም የተረገሙ ናቸው።

ቅዱሳን መላእክት ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለማጽናት፣ በሰማይ አብን ለመመልከት (ማቴ 18:10)፣ እንዲሁም ፍቃዱን ለማድረግ የተመረጡ ናቸው (ማቴ 6:10)። እነርሱ የብርሃን መላእክት ተደርገው ይቆጠራሉ (2ቆሮ 11:14)።

(6). የሚከተሉት መግለጫዎች በእግዚአብሔር ቃል በግልጽ ተደግፈው በአውደ ምንባቡ ወይም በተምሳሌታዊ ቋንቋ አለዚያም በተዘዋዋሪ መንገድ መልእክቱ ተላልፎ እንደሆነ ወይም አልተላለፈ እንደሆነ መርጠህ መልስ በጥ።

1. በግልጽ ተደግፏል
2. በተዘዋዋሪ መንገድ መልእክቱ ተላልፏል
3. በጭራሽ አልተደገፈም

ሀ. ሰይጣን የወደቀው በእብሪቱ ወይም ከመጠን ባለፈ ትዕቢቱ ነው።
ለ. መላእክት ፍጹማን ሆነው ተፈጥረዋል።
ሐ. ከመላእክት ሲሶው (እንድ ሦስተኛው) ሰይጣንን ለመከተል ወሰነዋል።
መ. የወደቁ መላእክት ሁሉ ንስሐ የመግባት ዕድል ይኖራቸዋል።
ሠ. መላእክት በሙሉ ኃጢአትን ለማድረግ ወይም ላለማድረግ በፈቃዳቸው መርጠዋል።
ረ. ኃጢአትን ባደረጉት መላእክት ላይ እግዚአብሔር አፋጣኝ ፍርድ አስተላልፏል።
ሰ. ኃጢአትን ለማድረግ ወይም ላለማድረግ በወሰኑት ውሳኔ መላእክት ሁሉ ተጠያቂ እንደሚሆኑ ተነግሯቸዋል።
ሸ. ሰይጣን እንደ ብርሃን መልአክ ተደርጎ ተቆጥሯል።
ቀ. ቅዱሳን መላእክት የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንደሚፈጽሙ ሁሉ ክፉ መላእክትም የሰይጣንን ፈቃድ ይፈጽማሉ።
በ. ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ ሰይጣን ክፉ ነበር።

የመላእክት ብዛት

ዓላማ 3 የመላእክትን ቁጥር በሚመለከት መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ትምህርት ጠቅለል አድርጎ የሚያቀርበውን መግለጫ መምረጥ

ለለ ቅዱሳንም ሆነ ስለ ርኩሳን መላእክት ብዛት በትክክል በእግዚአብሔር ቃል ባይገለጽልንም እጅግ ብዙ እንደሆኑ የሚገልጹ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶችን እናገኛለን።

1. ነቢዩ ኤልሳዕና ሎሌው በዶታይን ከተማ በኃይለኞቹ የአራም ሠራዊት በተከበቡ ጊዜ እግዚአብሔር ከእነርሱ የበለጡ የመላእክት ሠራዊት ባሪያዎቹን እንዲጠብቁ ልኪዋል (2ነገ 6:14-17)።

2. መዝሙረኛው እንደተናገረው "የእግዚአብሔር ሰረገላዎች የብዙ ብዙ ሺህ ናቸው" (መዝ 68:17)።

3. ሙሴ የእሥራኤልን ሕዝብ በመረቀ ጊዜ "እግዚአብሔር ... ከአእላፋት ቅዱሳኑ" ጋር እንደመጣ ጠቅሷል (ዘዳ 33:2)።

4. ዳንኤል ትንቢታዊ መግለጫውን በሚሰጥበት ጊዜ በዘመናት የሸመገለው (እግዚአብሔር) በፍርድ ዙፋኑ ላይ ቢቀመጥ ተመልክቶአል። የነበረውን ሁኔታ ዳንኤል ሲገልጽ "ሺህ ጊዜ ሺህ ያገለግሉት ነበር፣ እልፍ አእላፋትም በፊቱ ቆመው ነበር (ዳን 7:10) ብሏል።

5. የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ ለመልእክቱ ተቀባዮች "አእላፋት መላእክት" (ዕብ 12:22) በሚሰበሰቡበት ሕያው እግዚአብሔር ፊት በመቅረብ ስላለው የከበረ እድል ይናገራል።

6. በመጨረሻም ለተወዳጁ ደቀ መዝሙር ለዮሐንስ በግርማ ለለተሞላው በማያዊ ዐለቱ መገለጥ በሰጠው ጊዜ፥ ዮሐንስ "እየኑም በዙፋኑም እንስሶቹም በሽማግሌዎቹም ዙሪያ የብዙ መላእክትን ድምፅ ሰማሁ፤ ቁጥራቸውም አእላፋት ጊዜ አእላፋትና ሺህ ጊዜ ሺህ ነበረ፣" (ራእ 5:11) በማለት ተናገረ።

ከእነዚህ መረጃዎች እንደምንረዳው የመላእክት ሠራዊት ወይም የቅዱሳን መላእክት ቁጥር በርግጥም ከፍተኛ ነው። ከእነዚህ በተጨማሪ የሰይጣን ወይም የክፉ መላእክት ሠራዊት እንዳሉና ቁጥራቸውም ብዙ እንደሆነ እናውቃለን (ራእ 12:7-12)።

ለሚከተለው ጥያቄ ትክክለኛ የሆነውን መልስ ብቻ መርጠህ መልስ።

(7). የመላእክትን ብዛት በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን

ሀ. ለእግዚአብሔር ታማኝ ሆነው ከቀሩት ይልቅ ብልጫ ቁጥር ያላቸው መላእክት እንደወደቁ ነው።
ለ. መልካምም ክፉም የሆኑ ሊቆጠሩ የማይችሉ መላእክት እንዳሉ ነው።
ሐ. ብዙ መላእክት እግዚአብሔርን ሲያገለግሉ ክፉ የሆኑት ጥቂቶቹ ደግሞ ሰይጣንን እንደሚያገለግሉ ነው።
መ. የመላእክት ብዛት እየቀነሰ እንደሚሄድ ነው።

የመላእክት አደረጃጀትና አሰራር

መደራጀታቸውን የሚገልጹ መረጃዎች

ዓላማ 4 ቅዱሳን መላእክት በተደራጀ ሁኔታ አገልግሎታቸውን እንደ ሚፈጽሙ የሚያሰረዱ መግለጫዎችን መምረጥ

የተሰጣቸውን የተወሰኑ ተግባራት መወጣት ይችሉ ዘንድ መንፈሳዊ ኃይላት የተዋጣ አመዳደብ እንዳላቸው የሚገልጹ ብዙ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃዎች አሉ። ከእነዚህም ክፍሎች እንዳንዶቹ

1. 1ነገ 22:19 ነቢዩ ሚክያስ ስለ መላእክት አመዳደብ የገለጸው ነገር አለ። "እግዚአብሔር በዙፋኑ ተቀምጦ የሰማይም ሠራዊት ሁሉ በቀኙና በግራው ቆመው አየሁ"። የሰማይ ሠራዊት (መላእክት) በሙሉ ከሰውት እግዚአብሔር በዙፋኑ ተቀምጧል።

2. ማቴ 26:53 ኢየሱስ ለጴጥሮስ እንዲህ ብሎት ነበር። "ወይስ አባቴን እንድለምን እርሱም አሁን ከአሥራ ሁለት ጭፍሮች የሚበዙ መላእክት እንዲሰድልኝ የማይቻል ይመስልሃልን?" ይህ የሮም ወታደሮች የነበራቸውን ተመላላይ ዓይነት አደረጃጀት ያስታውሰናል። መላእክት የሰማዩን አባት መመሪያ ለመፈጸም ዝግጁዎች ሆነው በንቃት የሚጠባበቁ መሆናቸውንም ይህ ጥቅስ ያሳስበናል።

3. ሉቃ 2:8-14 ለእረኞቹ ተገልጾ የኢየሱስን መወለድ መልእኩ ካበሰረ በኋላ በድንገት "ብዙ የሰማይ ሠራዊት . . ." አብረው ተገልጸው ታዩ። ልዩ መልእክተኛውና ልዩ የመላእክት መዘምራን ባንድነት ሆነው ለእግዚአብሔር በምሥጋና ዜማ አዜሙ። በግሉ የተላከው መልእክተና መዘምራኑ መላእክት ለአብ ፈቃድ ምላሽ በመስጠት በየበኩላቸው የተሰጣቸውን ተግባር እንዳከናወኑ ግልጽ ነው።

4. ራእ 19:10-14 በጌታ ምጽአት ወቅት ስለሚገለጸው ድል አድራጊ የመላእክት ሠራዊት ዮሐንስ ባየው ራእይ መላእክቱ ትክክለኛነት፣ ሥርዓት ድርጅት፣ ሥልጣንና ዓላማ እንዳላቸው ተገልጿል። "በሰማይም ያሉት ጭፍራዎች ነጭና ጥሩ ቀጭን የተልባ እግር ልብስ ለብሰው በእምባ ላይ ፈረሶች ተቀምጠው ይከተሉት ነበር።

የቅዱሳን መላእክት የተደራጀ አሠራር

ሁለት ራሳቸውን ስለቻሉ የመላእክት ቡድን ማለትም ስለ ቅዱሳንና ስለ ርኩሳን መላእክት የምንመለከት በመሆናችን በቅድሚያ የቅዱሳን መላእክትን ሥራ እናጠናለን። ስለ ሥራቸው በምናውቅበት ጊዜ ይህንኑ ሥራ ለመሥራት እንዴት እንደተደራጁ በይበልጥ እንረዳለን።

መላእክት እግዚአብሔርን ያመልካሉ። በእግዚአብሔር ቃል ምበላቸው ተገልጾ ከቀረቡት ቅዱሳን መላእክት መካከል በእግዚአብሔር ፊት ቆመው እርሱን የሚያመልኩት መላእክት ይገኛሉ (መዝ 103:20፣ 148:2፣ ኢሳ 6:1-7)። ከፍጥረቱ ምሥጋና ሊቀበል የተገባው በመሆኑ እነዚህ መላእክት በከፍተኛ ድምጽ የምሥጋና ዜማ አሰምተዋል። ስለ ማንነቱ፣ ስለ ስጠን ስመታና ሰምችን ለመቤዠት ስላዘጋጀው መንገድ እግዚአብሔርን ያመልኩታል (ራእ 5:9-12 ላይ የቀረበውን ከራእ 5:13 -14 ጋር አነፃፅር)።

ቅዱሳን መላእክት እግዚአብሔር በተፈጥሮ ውስጥ በሰራው ድንቅ ሥራና (ኢዮብ 38:7) ኃጢአተኞችን በመለወጥና ወደራሱ ቤተሰብ በማምጣት በሚፈጽመው የታምራት ሥራ ሐሴት ያደርጋሉ (ሉቃ 15:10)። መንግሥተ

ሰማያት መላእክት ስማያዊ ጉባኤ ሆነው የሚታዩበት የከበረች ቤተ መቅደስ ሆና ተገልጣለች። በዚያም ሥፍራ እግዚአብሔርን በማምለክና በማመስገን መላእክት ምንጊዜም ይኖራሉ (ማቴ 18:10)።

መላእክት የሚያገለግሉ መናፍስት ናቸው። መላእክት እግዚአብሔርን ማምለክና በማንነቱ፣ እንዲሁም በሥራው ደስ መሰኘት ብቻ ላይሆን፣ የእርሱንም ፈቃድ ያበፈጽማሉ (መዝ 103:20)። እንደሚያገለግሉ መናፍስት መላእክት ደኅንነትን ሊወርሱ ያላቸውን ሊያገለግሉ ተልከዋል (ዕብ 1:14)። በብሉይና በአዲስ ኪዳን ዘመናት ይህ የመላእክት አገልግሎት እንዴት ይፈጸም እንደነበረ እስኪ እስተውል።

1. በጣም አደገኛ በሆነ ሁኔታ ውስጥ በነበረበት ጊዜ መላእክት ጳውሎስን አበረታትተውታል (የሐዋ 27:23-24)።
2. ፊሊጶስ በሚያገለግልበት ወቅት መላእክት መርተውት ነበር (ሐዋ 8:26)።
3. ከእግዚአብሔር ጋር የበለጠ የሚያረካ ግንኙነት እንዲኖረው ባደረገው መሻት መልአክ ቆርነሌዎስን ረድቶት ነበር (የሐዋ 10:3-7)።
4. ጴጥሮስ በመልአክ አማካይነት በታምራታዊ ሁኔታ ከእሥራት ነጻ ወጥቶአል (የሐዋ 12:7-10)።
5. በመጽሐፍ ቅዱስ በተጠቀሱ ቢያንስ ሁለት ወቅቶች መላእክት ኢየሱስን አበረታተውታል (ማቴ 4:11፣ ሉቃ 22:43)።
6. ኤልሳዕ ከኃይለኛው የሶሪያ ሠራዊት በቅዱሳን የመላእክት ጭፍሮች ተጠብቆ ነበር (2ነገ 6:8-23)።
7. ዳዊት ከአቤሜሌክ ዘንድ ካመለጠ በኋላ (1ሳሙ 21:10-22:1) በመላእክት እንደተጠበቀና ነፃ እንደወጣ ተናግሯል (መዝ 34:7 ተመልከት)።

መላእክት ፍርድ አስፈጻሚዎች ናቸው። መላእክት የእግዚአብሔርን ጠላቶች በመቅጣት ፍርድ አስፈጻሚ ወኪሎች ሆነዋል። ለዚህ ምሳሌ ሊሆንልን የሚችል ሁኔታ በ2ነገ 19:31 ላይ እናገኛለን። "በዚያችም ሌሊት የእግዚአብሔር መልአክ ወጣ፣ ከአሦራውያንም በፈር መቶ ሰማንያ አምስት ሺህ ገደለ"። በሐዋ 12:23 ላይም "ለእግዚአብሔርም ክብር በላልሰጠ ያን ጊዜ የጌታ መልአክ መታው፣ በትልም ተበልቶ ሞተ" ይላል።

ብዙ ሌሎች ክፍሎች መላእክት የእግዚአብሔርን ችሮታ እንዲሁም ባለፈው ዘመን የተከናወኑትንና ወደፊትም የሚከናወኑትን ፍርዶች በማስፈጸም፣ ከዚህም በስተቀር በምዕእቱ ወቅት ልዩ ኃይላት ሆነው ጌታን በማጀብ ስለ ሚሰሩት ሥራ ይጠቅሳሉ።

(8). ከሚከተሉት ተግባራት ቅዱሳን መላእክት የተሳተፉት በየትኞቹ ነው?

ሀ. እግዚአብሔርን ያመልኩታል፣ ያመሰግኑታል፣ ፈቃዱንም ያደርጋሉ።
ለ. የሚያገለግሉ መናፍስት እንደመሆናቸው በምድር የተዋጁትን ያገለግላሉ።

ሐ. ስምችን ስለ ኃጢአታቸው በመውቀስ ወደ ንስሐ ይመራሉ።
መ. የእግዚአብሔርን ሕዝብ ይጠብቃሉ፣ ከመከራ ያወጣሉ፣ ይመራሉ፣ ያደፋፍራሉ፣ ያበረታታሉ።
ሠ. የእግዚአብሔርን ጠላቶች በመቅጣት የፍርድ አስፈጻሚ ወኪሎች ይሆናሉ።

መላእክት በመንግሥታት ጉዳይ ላይ ተጽእኖ ያሳድራሉ። ዳን 10:13፣ 20 በመንግሥታት ላይ የሰለጠኑ የክፉ መናፍስት ግዛቶች እንዳሉና ቅዱሳን መላእክቱም እንደሚቋቋሟቸው ይገልጻል። ከእነዚህና ከዳን 10:21-11:1 ከምናገኘው መረጃ መላእክት የመንግሥታት ጉዳይ በአደራ የተሰጣቸው ይመስላል። በትንቢተ ዳንኤል ያሉትን መረጃዎች ከኤፌ 1:21፣ 6:12፣ እንዲሁም ከቆላ 1:16፣2:15 ጋር ስናነጻጽር በስማያዊው ግዛት በማንኛውም ጊዜ መንፈሳዊ ውጊያዎች እንደሚያካሂዱ እንመለከታለን። እነዚህ ጦርነቶች የሰዎችን አእምሮና ፍላጎት በማጥመድና ውጤቱም የነፍሳቸውን ዘላለማዊ ጥፋት በማስከተል በክፉ ኃይላት የሚካሄድ ነው።

የመላእክት አለቃ ራሱ እስከሚሳተፍ ድረስ ውጊያው እጅግ የከረረ ደረጃ ሊደርስ የሚችል ይመስላል። በይሁ 9 የመላእክት አለቃ የተባለው ሚካኤል የቅዱሳን መላእክት መሪ ነው። የእሥራኤል ሕዝብ አለቃ እንደሆነም ተነግሯል፣ ሥራውም የእሥራኤልን መንግሥት መጠበቅና ማበልጸግ የሚያጠቃልል ይመስላል (ዳን 10:13፣ 21፣ 12:1)። ወደ ጌታ ምዕአት የሚያመሩ ሁኔታዎች መፈጸም ሲጀምሩ ድምፁን ከፍ አድርጎ ያመስግናል (1ተሰ 4:16)።

በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ በስም የተገለጹት ሁለት መላእክት ብቻ ናቸው። የመላእክት አለቃ ሚካኤልና ልዩ መልእክተኛ እንደሆነ የተገለጸው ገብርኤል (ዳን 8:16፣ 9:21፣ ሉቃ 1:19፣ 26)። ስማቸው ያልተጠቀሱ ብዙ ሌሎች መላእክትም ጌታን በዚህ ደረጃ ያገለግሉታል።

የሌሎች ቅዱሳን መላእክት እርከንን በሚመለከት መጽሐፍ ቅዱስ የተወሰኑ መረጃዎች ይሰጠናል፦

1. ኪሩቤል (ዘፍ 3:24፣ 2ነገ 19:15፣ ሕዝ 10:1-22፣ 28:14-16)። ኪሩቤል የእግዚአብሔር ዙፋን ጠባቂዎች ናቸው። የኤደን ገነትን መግቢያም ይጠብቃሉ።

2. ሱራፌል (ኢሳ 6:2፣6)። ሱራፌል በእግዚአሔር ዘንድ አምልኮ መሪዎች ሳይሆኑ አይቀሩም። የአነርሱ ዋና ትኩረት በእግዚብሔር የተዋጁት ተቀባይነት ያለው አምልኮና አገልግሎት ያቀርቡ ዘንድ ነው።

3. ጠባቂዎች (ዳን 4:13፣ 17)። የተወሰኑ ተግባሮችን እንዲከታተሉ መመደባቸው ግልጽ ነው። በሚያከናውኗቸው ተግባሮች ታማኞች ናቸው፣ በዚህም ጥቅስ የእግዚአብሔርን መልእክት ለሰዎች ሲያቀርቡ ይታያሉ።

4. ሕያዋን እንስሶች (ራእ 4:6-9፣ 6:1-7፣ 15:7)። እነዚህ መላእክት ከሱራፌል፣ ከኪሩቤልና ከተለመዱት ዓይነት መላእክት የተለዩ ይመስላሉ። እግዚአብሔርን የሚያመልኩ፣ ፍርዱን የሚያስፈጽሙና በዙፋኑም ዙሪያ የሚንቀሳቀሱ ይመስላል።

በአጠቃላይ የቅዱሳን መላእክት አካል የሆኑት፣ እግዚአብሔርን በሚገባ ከማገልገላቸውም በላይ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያሉትን ዓላማዎች ለማስፈጸም ምንጊዜም ዝግጁዎች ናቸው።

(9). ከዚህ ቀጥሎ ከተራ ቁጥር 1-7 ያሉትን እያንዳንዳቸውን ስሞችና ምድቦች ከሀ-ስ ድረስ ከተሰጡት መግለጫዎች ጋር አዛምዳቸው።

1. ሚካኤል
2. ገብርኤል
3. ቅዱሳን መላእክት
4. ኪሩቤል
5. ሱራፌል
6. ጠባቂዎች
7. ሕያዋን እንስሳት

ሀ. የተለዩ ተግባሮችን እንዲከታተሉ የተመደቡ ልዩ መልእክተኞች።
ለ. ልዩ መልእክተኛ የሆነ መልእክ።
ሐ. የእግዚአብሔርን ዙፋን የሚጠብቁ መላእክት።
መ. በእግዚአብሔር ዙፋን ዙሪያ የሚንቀሳቀሱና አንዳንድ ፍርዶችን የሚያስፈጽሙ።
ሠ. የእግዚአብሔርን ፊት የሚመለከቱ፣የሚያመልኩና ትዕዛዙን ለመፈጸም ዝግጁ ሆነው የሚጠባበቁ ጠቅላላ ሠራዊት።
ረ. በእግዚአብሔር ሕልውና ዘንድ ቅድስና በመጠበቁና ተቀባይነት ያለው አምልኮ በማቅረቡ ላይ ትኩረት የሚያደርጉ መላእክት።
ሰ. የእሥራኤል መንግሥት ልዩ አለቃ።

የቅዱሳን መላእክት የተግባራቸው ስፋት

ስለ ቅዱሳን መላእክት ተግባሮች የሚናገረውን ርዕስ ከማለፋችን በፊት የተግባራቸውን ደረጃ ወይም መጠን በሚመለከት ከእግዚአብሔር ቃል አንጻር ልንደርስባቸው የምንችላቸውን በርከት ያሉ ድምዳሜዎች መጥቀስ አለብን።

በቅድሚያ ቅዱሳን መላዕእክት የእግዚአብሔር ሕዝብና ቤተክርስቲያን የእግዚአብሔር ልዩ ችሮታ በሚያስፈልጓቸው ጉዳዩች የሚያገለግሉ ናቸው። ዕብ 1:7 "መላእክቱን መናፍስት አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል የሚያደርግ" ይላል (መዝ 104:4)። በሌላ አነጋገር እግዚአብሔር መላእክቱን መልክተኞች አድርጎ የሚጠቀምባቸው ለተለመደው ዓይነት አሰራር ሳይሆን ከሕጉ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ልዩ ኃይሉን መግለጽ በሚፈልግበት ጊዜ ነው (ዘዳ 33:2፣ የሐዋ 7:53፣ ገላ 3:19 እና ዕብ 2:2)።

በሰዎች ልጆች ጉዳዮች ላይ የመላእክት ጣልቃ የመግባት ሁኔታ እልፎ እልፎ የሚፈጸምና ብዙውን ጊዜ ያልተለመደ ነው። መላእክትም ጣልቃ ሲገቡ በራሳቸው ፈቃድ ሳይሆን እግዚአብሔር ሲያዛቸው ብቻ ነው።

በሁለተኛ ደረጃ ከእግዚአብሔር የሚገኘውና በእርሱም ላይ የሚደገፈው የመላእክት ኃይል የመንፈሳዊውንና የተፈጥሮአዊውን ሕግ በመከተል ተግባራዊ የሚሆን ይመስላል። እግዚአብሔር እንደሚያደርገው ሁሉ መላእክት መፍጠር፣ ያለ እግዚአብሔር ሥልጣን ድርጊትን ማከናወን፣ ልብን መመርመር ወይም የተፈጥሮን ሕግ መለወጥ አይችሉም። በሰዎች አእምሮ ላይ በቀጥታ ተፅእኖ ማሳደር አይችሉም። ምክንያቱም ይህን ማድረግ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው። ግልጽ በሆነ ሁኔታ መላእክት የሚሰሩት ውሱን በሆነ መንገድ ነው።

በሦስተኛ ደረጃ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚገልጸው በአጠቃላይ የመላእክት መገለጽ የሚከሰተው እስፈላጊና አዲስ የእግዚአብሔር እቅድ ከመጀመሩ በፊት ወይም የአቅዱን መገለጽ በማጀብ ነው። ለምሳሌ በሚከተሉት ሁኔታዎች የመላእክትን እንቅስቃሴ እንመለከታለን።

- በመፍጠር ወቅት (ኢዮብ 38:7)
- የአሪት ሕግ በተሰጠበት ጊዜ (ገላ 3:19)
- በክርስቶስ ልደት ወቅትና ከዚያ ትንሽ ቀደም ብሎ (ሉቃ 1:11፣ 26፣ 2:13)
- ኢየሱስ በምድረ በዳ በተፈተነበት ጊዜና በጌቴሰማኒ (ማቴ 4:11፣ ሉቃ 22:43)
- በኢየሱስ ትንሣኤ ወቅት (ማቴ 28:2)
- በኢየሱስ ዕርገት ወቅት (የሐዋ 1:10-11)
- ከክርስቶስ ዳግም ምጽአት በፊት በሚፈጸመው የመጨረሻው ዘመን ክንውኖች (ስለ መላእክት አሰራር በዮሐንስ ራዕይ የቀረቡትን ብዙ ጥቅሶችና ማቴ 25:31 ተመልከት)።

(10). የቅዱሳን መላእክትን ተግባር በመግለጽ ዓረፍተ ነገሩን የተሟላ ሊያደርጉ ከሚችሉት መግለጫዎች አንዣር ያሉትን ፊደላት ክበቡቸው። መላእክት

ሀ. በእግዚአብሔርና በሕዝቡ መካከል ጣልቃ ይገባሉ።
ለ. የእግዚአብሔር ችሮታ ልዩ አገልጋዮች ናቸው።
ሐ. የአሪት ሕግ በተሰጠ ጊዜ ልዩ ኃይላቸውን ገልጸዋል።
መ. በመፍጠር ተግባር ወቅት ነበሩ።
ሠ. የሰዎችን እእምሮ በመለወጥ ተግባር በመሳሪያነት አገልግለዋል።
ረ. ሰውን በቀጥታ በመፈተናቸው ተጠያቂ ናቸው።
ሰ. የእግዚብሔር የማዳን ዕቅድ እስፈላጊ አቅጣጫ በሚይዝበት ጊዜ የተለየ ተሳትፎ እላቸው።
ሸ. የመንፈሳዊውንና የተፈጥሮአዊውን ዓለም ሕግጋት ይሽራሉ።

የእርኩሳን መላእክት አደረጃጀትና ተግባር

ዓላማ 5 ቅዱሳን ያልሆኑ ወይም የጨለማ መላእክት የሚያከናውኑትን ተግባርና የመጨረሻ ዕጣቸውን በተመለከተ የሚናገሩትን ትክክለኛ መግለጫዎችን መምረጥ

መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ዙፋን እንዳለውና የሚያገለግሉ ጭፍሮች በዙሪያው እንዳሉ እንደሚናገር ሁሉ ጨለማ በሆነው መንፈሳዊ ክልልም ዲያቢሎስ የራሱ ድርጅት እንዳለው ይገልጻል። ሰይጣን ዙፋን እለው (ራእ 2:13) በእግዚአብሔር ቃል "የዚህ ዓለም ገዢ" ተብሎ ተጠቅሷል (ዮሐ 14:30፣ 16:11)። እንዲሁም "በአየር ላይ ሥልጣን ያለው አለቃ" (ኤፌ 2:2) ተብሏል። እርሱ የክፉው ድርጅት አለቃ ነው። ሰይጣን መላእክት እንዳሉትና (ማቴ 25:41) እነዚህም መላእክት እግዚአብሔርን እንደሚቃወሙ (ራእ 12:7-9) መጽሐፍ ቅዱስ ይነግረናል።

ስለእነዚህ የክፉ ኃይላት ድርጅት ተጨማሪ መረጃዎች በጳውሎስ መልእክቶች ውስጥ ተጠቅሶአል። በቆላ 1:16 ላይ ስለ ". . .ጌትነት ወይም አለቅነት ወይም ሥልጣናት. . ."፣ ኤፌ 6:12 ስለ ". . . አለቆች. . . ሥልጣናት. . . የጨለማ ዓለም ገዦች. . .በሰማያዊ ሥፍራ ስላሉ የክፋት መንፈሳዊያን ሠራዊት" ይናገራል። እነዚህንም ሠራዊት በመበቀሉ ድል አድርጓቸዋል (ቆላ 2:15)። በእነዚህ ጥቅሶች ስያንዳንዳቸው ውስጥ በሥልጣን እርከን ላይ የተመሠረተ የሹመት አደረጃጀት እንዳለ መረጃዎችን እንመለከታለን። ይህ የክፋት እደረጃጀት በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ለዓመፅ የተነሣጠረ ነው። በመሆኑም እነዚህ ልዩ ልዩ የሰይጣን ኃይላት ከእግዚአብሔርና ከሕዝቡ ጋር የሚቃረኑ ናቸው። የመሪያቸውን ማንነት በመመርመር ስላልተቀደሱት ወይም እርኩሳን መላእክት ብዙ እንማራለን።

መሪያቸው

ርኩሳን መላእክት እግዚአብሔርን ይቃወማሉ፣ ፍቃዱንም ለማስናከል ጥረት ያደርጋሉ። ይህንንም ለመሪያቸው ከተሰጡት በሞች በመነሳት እንደማስረጃ እንመለከታለን።

1. *ሰይጣን* ተብሏል፦ ይህም ጠላት ወይም ተቃዋሚ መሆኑን ያመለክታል። ከሁሉም በፊት እርሱ የእግዚአብሔር ጠላት ነው። የሰውም ደግሞ ጠላት ነው (ዘካ 3:1፣ ማቴ 13:39፣ 1ጴጥ 5:8)።

2. *ዲያብሎስ* ተብሏል፦ ይህም ክሳሽ መሆኑን ያመለክታል። ስዎችን በእግዚአብሔር ፊት (ዘፍ 3:1-4) እግዚአብሔርንም በሰዎች ፊት (ኢዮ 1: 9፣ 16፣ ራእ 12:10) ይከሳል።

3. *ፈታኝ* ተብሏል፦ ሰዎችን ኃጢአት እንዲያደርጉ ስለሚያባብላቸው፣ ፈታኝ ተብሎ ተጠርቶአል። ይህንንም ለማድረግ የሚጠቀምባቸው ዘዴዎች

ኃጢአትን ሰመፈጸም ምክንያታዊ የሚመስሉ ማስተባበያዎችን እንደዚሁም ኃጢአትን ሰማድረግ ሊገኙ ይችላሉ የሚባሉ ታላላቅ ትርፎችን ማመልከት ናቸው (ማቴ 4:3፤ 1ተስ 3:5)።

ውሱን በመሆኑና ሁሱን ቻይ፣ ሁሱን አዋቂ ወይም በሁሉም ሥፍራ የሚገኝ ባለመሆኑ ሰይጣን እግዚአብሔርን ሰመቃወም የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማል። እግዚአብሔርን በቀጥታ ሊዋጋው እንደማይችል ግልጽ ነው፤ ስለሆነም የእግዚአብሔር ፍጥረት ቁንጮ የሆነውን ሰው ሰልዩ ልዩ መንገድ ያጠቃዋል፦

1. ይዋሻል (ዮሐ 8:44፤ 2ቆሮ 11:3)
2. ይፈትናል (ማቴ 4:1)
3. ይሰርቃል (ማቴ 13:19)
4. ያስቃያል (2ቆሮ 12:7)
5. ያዘገያል (1ተስ 2:18)
6. ሕይወትን ሰማንገላታት ያበጥራል (ሉቃ 22:31)
7. ለማታለል እንዲመቸው ራሱን ይሰውጣል (2ቆሮ 11:14) (ያልሆነውን ለመሆን ይሞክራል)
8. ያከሳል (ራእ 12:10)
9. በሕመም ያጎሳቁላል (ሉቃ 13:16)
10. በሰዎች መንፈስ ያድራል (ዮሐ 13:27)
11. ይገድላል ደግሞም ያጠፋል (ዮሐ 8:44፤ 1ጴጥ 5:8)

እንደ*መሰከትነው ሰይጣን በእግዚአብሔር ላይ ባመጸ ጊዜ እርሱን የተከተሱትን ብዙ ሌሎች የክፉት መላእክትን ይቆጣጠራል። ቦተፈጠረበት ወቅት የተሰጠውን ሥልጣኑን እንዲጠብቅ የተፈቀደለት ይመስላል። እግዚአብሔር የሰጣቸውን የሥልጣን ሥፍራና መኖሪያቸውን (ይሁዳ 6) እንዲሁም ለፈጣሪያቸው ያላቸውን ታማኝነት ከመጠበቅ ይልቅ ሰይጣንን ለመከተል የመረጡት ርኩሳን መናፍስት በዓመጻቸው ጸንተዋል። ላታሰላቸው ለመሪያቸው ራሳቸውን ሙሱ በሙሱ ሰጥተዋል፤ የሰይጣን የክፉት ዓላማዎቹም ከግብ እንዲደርሱ በፈቃደኛነት አገልግሎታቸውን አበርክተዋል።

(11). ከዚህ ቀጥሎ ከ1-5 ያሉትን ስሞች ወይም መጠሪያዎች ከሀ-ሠ ካሉት መግለጫዎች ጋር አዛምዳቸው።

1. ለይጣን
2. ዲያብሎስ
3 ፈታኝ
4. ሰው
5. የጨለማ መልአክ

ሀ. የዲያብሎስ የጥቃት ዓላማ እግዚአብሔርን የሚያሳዝንበት መንገድ።
ለ. በእግዚአብሔር ላይ በተከፈተው ዘመቻ ከዲያብሎስ ረዳት ሠራተኞች መካከል የሆኑት።
ሐ. የጠላትነትን ወይም የተቃዋማነትን ሃሳብ ያዘለ።
መ. አንድን ሰው ኃጢአት እንዲያደርግ ስለሚያባብል የተሰጠ ስም።
ሠ. በሐሰት ስለሚከስ የተሰጠ ስም።

ተግባሮቻቸው

የሰይጣን የጨለማ መንግሥት ተዋጊ ሞፍራ የሆኑ ርኩሳን መላእክት እግዚአብሔርን፣ ሕዝቡን፣ እንደዚሁም ቅዱሳንን ይቃወማሉ (ማቴ 25:41፤ ኤፌ 6:12፤ ራእ 12:7-12)። በርኩሳን መላእክትና በአጋንንት መካከል ያለውን ልዩነት ሰማወቅ አንዳንድ ሙከራዎች ቢደረጉም ሁለቱም የማይነጣጠሉና ወይንም እንድ አለመሆናቸውን የሚያረጋግጥ መረጃ ግን አልተገኘም።

እነዚህ ርኩሳን መላእክት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ከአምላካቸው ለመሰየት ሙከራ ያደርጋሉ (ሮሜ 8:38)። ቅዱሳን መላእክትን ይቃወማሉ (ዳን 10:12-11:1)፤ ሰዎችን በሥጋዊና አእምሯዊ በሽታ ያጎሳቁላሉ (ማቴ 9:33፤ 12:22፤ ማር 5:1-16፤ ሉቃ 9:37-42) በሰዎችና በእንስሳት ሳይቀር ያድራሉ (ማቴ 4:24፤ ማር 5:8-14፤ ሉቃ 8:2፤ የሐዋ 8:7፤16:16)።

ከራሳቸው ውጪ በሆነ መንገድ እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ እመጸኛ ሰዎችን ለመቅጣትና (መዝ 78:49፤ 1ነገ 22:23) ጻድቃንን ወይም መልካም ሰዎችን ለመገሰጽና ለማስተካከል ዓላማው እርኩሳን መላእክትን ይጠቀምባቸዋል (ኢዮብ 1 እና 2፤ 1ቆሮ 5:5)።

የመጨረሻ ዕጣቸው

ርኩሳን መላእክት የከፋ የሕይወት አቋም ያላቸው ምን እንደሚደር ሰባቸው ለማስረዳት በምሳሌነት ያገለግላሉ። የሚከተሉት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃዎች የመጨረሻ ዕጣቸውን ይገልጻሉ።

- በሁለት ሰዎች ውስጥ ያደሩ አጋንንት ኢየሱስ በመጣባቸው ጊዜ እንዲህ ብለው ጮኸዋል፦ "... ጊዜው ሳይደርስ ልታሰቃየን ወደዚህ መጣህን?" (ማቴ 8:29)

- ኢየሱስ "ለሰይጣንና ለመላእክቱ ... ስለ ተዘጋጀ የዘላለም እሳት" (ማቴ 25:41) ተናግሯል።

- ጳውሎስ "ጌታ ኢየሱስ በእሱ መንፈስ የሚያጠፋው ሲመጣም በመገለጡ የሚሰራው ዓመጸኛ... " እንደሚመጣ (2ተስ 2:8) ተናግሮአል።

- ያዕቆብ "...እጋንንት ደግሞ ያምናሉ ይንቀጠቀጡማል" ብሏል (ያዕ 2:19)

- ዮሐንስ "... ዲያቢሎስ ጥቂት ዘመን እንዳለው እውቆ በታላቅ ቁጣ ወደ እናንተ ወርዷልና" ብሏል (ራእ 12፤12)።

- ዮሐንስ "... ለዘላለምም እስከ ዘላለም ቀንና ሌሊት ይሰቃያሉ" ብሏል (ራእ 20:10)።

(12). ጥቅሶቹን አንብበህ መግለጫዎቹን የተማሉ አድርጋቸው።

ሀ. 2ጴጥ 2:4 "እግዚአብሔር ኃጢአትን ላደረጉ መላእክት ሳይራራላቸው ወደ ጥሎ ለ ሊጠበቁ
ለ. ይሁዳ 6 "መኖሪያቸውን የተውትን እንጂ የራሳቸውን አለቅነት ያልጠበቁትን መላእክት በዘላለም እሥራት
ሐ. መዝ 78:49 "የመዓቱን መቅሰፍት በላያቸው ሰደደ፣ መቅሰፍትን መዓትንም መከራንም
መ. ማቴ 8:16፣ ማር 9:25-26 ያደረባቸውን ብዙዎችን ወደ አርሱ አመጡ።
ሠ. ሉቃ 13:10-16 ርኩሳን መናፍስት ሰዎችን ይችላሉ።
ረ. ራእ 12:7-12፣ ኤፌ 6:12 ሰይጣንና ርኩሳን መላእክት ሥራቸውን የሚያከናውኑባቸው ሥፍራዎች እና ናቸው።

ሰለ ርኩሳን መላእክት አሰራርና የመጨረሻ ዕጣቸው አሰካሁን ካደረግነው ጥናት አንዳንድ አሰፈላጊ ግንዛቤዎችን ማውጣት አንችላለን።

1. የዲያብሎሰን ዘዴዎች በሚመለከት ልንሳሳትና ከአኛም ይልቅ ብልሀ ሆኖ እንዲያሞኘን መፍቀድ አይገባንም (2ቆሮ 2:11)። በሕይወታችን ድርሻ አንዲኖረው ፈቃድ መስጠት አይገባንም (ኤፌ 4:27)። ከዚያ ይልቅ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ በመጠቀም ልንቃወመው መዘጋጀት አለብን (ያዕ 4:7፣ ኤፌ 6:10-18)።

2. የዲያብሎስን ነገር እንደዋዛ አንሰተን መናገር (ይሁዳ 8፣9) ወይም የአማኙን መንፈሳዊ ሕይወት ሰማጥፋት የሚያሳየውን የቆራጥነት መጠን አቅልሰን ልንመለከተው አይገባንም። በሌላ በኩል ኢየሱሰ ሰይጣንን በመሰቀሉ ላይ ድል እንዳደረገው (ዕብ 2:14) እኛም በዚያ ድል መሰረት ላይ ቆመን በአምነት መኖር እንደሚገባን መዘንጋት የለብንም።

3. የሰይጣንና የርኩሳን መላእክቱ ኃይል በጊዜና በሰፋት የሚሰሩበት መጠን በእግዚአብሔር ፈቃድ የተወሰ ነው። አነርሱ ሁሉን ቻይ፣ ሁሉን አዋቂ ወይም በማንኛውም ሥፍራ የሚገኙ አይደሉም።

4. በትክክል ካልተገለጸ በስተቀር ሕመምንና ተፈጥሮአዊ ጥፋቶችን ከዲያብሎሰና ከርኩሳን መላእክቱ ጋር ልናዛምዳቸው አይገባንም። ክፋትን ለመሥራት ያላቸው ብርታት አርግጠኛ ቢሆንም ውሱን ነው።

5. እግዚአብሔርን የሚቃወሙ ቢሆኑም ዓላማዎቹን እንዲፈጽሙ ያሰገድዳቸዋል። የራሱን ዓላማዎች ሰማሰፈጸም አግዚአብሔር ክፉ አቅዳቸውን ቢጠቀምበትም በተቀጠረው ወቅት ፍርዱንና ቅጣቱን ይፈጽምባቸዋል።

6. በሰዎች ላይ የሚሠራው የርኩሳን መናፍሰት ኃይል ከሰዎች ፈቃድ ውጪ አይደለም። ሥራቸውን ለመጀመር የሚያሰችላቸውን የሰዎችን የሰምምነት ፈቃድ ሳያገኙ ክፉ መናፍሰት ኃይላቸውን ተግባራዊ ማድረግ አይችሉም። ይህም ማለት በጸሎትና በእግዚአብሔር ላይ ባለው አምነት አማኙ ኃይላቸውን ሊቃወም ይችላል። ይህ የተረጋገጠ የእግዚአብሔር የተሰፋ ቃል አለን። "ልጆች ሆይ፣ አናንተ ከእግዚአብሔር ናችሁ አሸንፋችኋቸሁማል፣ በዓለም ካለው ይልቅ በአናንተ ያለው ታላቅ ነውና!" (1ዮሐ 4:4)።

(13). አውነተኞቹን መግለጫዎች የሚያሳዩትን ፊደሎች ክበባቸው።

ሀ. የሰይጣንን ዓላማ ከተሰጡት ሰሞች አንጻር መገንዘብ አንችላለን።
ለ. ሰይጣን አግዚአብሔርን በቀጥታ ማጥቃት ሰለማይችል አግዚአብሔርን ለመበቀል ሰውን ያጠቃል።
ሐ. ዲያብሎሰ የተፈጠረው በእግዚአብሔር ላይ ባመጹት አርኩሳን መላእክት ላይ መሪ አንዲሆን ነው።
መ. አርኩሳን መላእክት ክፉዎች ሆነው የተፈጠሩት በራሱ በእግዚአብሔር ሥራ ነው።
ሠ. አርኩሳን መላእክት ውሱን ሰላልሆኑ በማንኛውም ሰው ላይ በማንኛውም ጊዜ ሥራቸውን ሊሰሩ ይችላሉ።
ረ. ኃጢአተኞችን ለመቅጣት ወይም ጻድቃንን ሰመገሰጽ ዓላማው እግዚአብሔር ከራሳቸው ውጪ በሆነ መንገድ ርኩሳን መላእክትን ይጠቀምባቸዋል።
ሰ. አንዳንድ አርኩሳን መላእክት ፍርዳቸውን አሰኪቀበሉ ድረስ በአሰራት ላይ ሊገኙ ሌሎቹ ደግሞ የዲያብሎሰን ፈቃድ ለማሰፈጸም በነፃነት ይመላለሳሉ።
ሸ. ሰይጣንና አርኩሳን መላእክቱ በጊዜና በሰፋት የሚሰሩበት መጠን በእግዚአብሔር ችሮታዊ ፈቃድ የተወሰነ ነው።
ቀ. አማኙ ዲያብሎሰንና የአርሱንም ኃይሎች መቃወም ይችል ዘንድ በሚገባ ታጥቋል።
በ. ዲያቢሎሰ ያለ ፈቃዳቸው በአማኞች ውሰጥ ሊያድር አይችልም።

የመከራ ፈተና

እውነት ወይም ሐሰት። ሐሰት በሆኑ መግለጫዎች አንባር "ሐ"፣ እውነት በሆኑት መግለጫዎች አንባር ደግሞ "እ" ብለሀ ጻፍ።

1. መላእክት መንፈሳዊ ሕላዌ ያላቸው ፍጡራን ናቸው።

2. መላእክት በሙሉ ቅዱሳን ሆነው ተፈጥረው ነበር።

3. መላእክት ጭፍራዎች ወይም ዝርያዎች ተብለው ሊጠሩ ይችላሉ።

4. የመላእክት ጭፍራዎች በተግባራቸው ወይም በሥራ ድርሻቸው ላይ የተመሰረተ የሚመስል የመደራጀት መረጃ ይታይበቸዋል።

5. የሥልጣን ሥፍራቸውን የተውትና የራሳቸውን መኖሪያ የለቀቁ መላእክት ያንን ያደረጉት በገዛ ፈቃዳቸው ነው።

6. መላእክት አካላዊነት እንዲሁም ከሰዎች ይልቅ እውቀትና ኃይል አላቸው።

7. መላእክት ሁሉን እዋቂ፣ በሁሉም ሥፍራ የሚገኙና ሁሉን ቻይ ናቸው።

8. የሰይጣን ውድቀት ራሱን የማታለሉና የትዕቢቱ ውጤት መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያስገነዝባል።

9. የመላእክት አሰቃ፣ ኪሩቤል፣ ሱራፌልና የተሰየ መጠሪያ የሌላቸው ብዙ መላእክት መኖራቸውን የሚደግፍ መረጃ ቀርቧል።

10. የሰይጣን ኃይል በጊዜና በስፍራ የሚሰራበት መጠን በእግዚአብሔር ችሮታዊ ፈቃድ የተወሰነ ነው።

11. ቢያንስ ቢያንስ ከመላእክት ግማሹ ሰይጣንን ለመከተል እንደመረጡና በዚያም ምክንያት ከእርሱ ጋር እንደወደቁ መጽሐፍ ቅዱስ ያስገነዝባል።

12. ዲያብሎስ እንድንወድቅ ሊፈትነን ይችላል እንጂ እንድንወድቅ ሊያደርገን አይችልም።

13. ሰዎች እየተቃወሙት እንኳን ያሰ ፈቃዳቸው ጋኔን ሊያድርባቸው ይችላል።

14. አጅግ በጣም ብዙ መላእክት እንዳሉና ከብዛታቸውም የተነሳ ሊቆጠሩ የማይችሉ ጭፍሮች እንደሆኑ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጽልናል።

15. "መላእክት" የሚለው ቃል ትርጉም "መልእክተኛ" ማለት ሲሆን ይህም የመላእክትን ዋና ተግባር ይገልጻል።

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስ

7. ለ

1. ሀ. ሁሉንም ነገሮች፣ የሚታዩትንና የማይታዩትን
   ለ. ሕይወት

8. ሀ፣ ሰ፣ መ፣ እና ሠ የቅዱሳን መላእክት ተግባሮች ናቸው።

2. ለ

9. ሀ. 6 ሐ. 4 ሠ. 3 ሰ. 1
   ለ. 2 መ. 7 ረ. 5

3. ሁሉን አዋቂ፣ ሁሉን ቻይና በማንኛውም ሥፍራ የሚገኙ አይደሉም።

10. ለ፣ ሐ፣ መ፣ እና ሰ የቅዱሳን መላእክት ተግባሮች ናቸው።

4. ሀ. 4 ሐ. 6 ሠ. 2 ሰ. 8
   ለ. 7 መ. 5 ረ. 1 ቸ. 3

11. ሀ. 4 ሐ. 1 ሠ. 2
   ለ. 5 መ. 3

5. ሀ. በእውነት ጸንቶ አለመቆም ነው
   ለ. ኃጢአትን ሲያደርጉ
   ሐ. የሥልጣን ስፍራቸውን፣ የራሳቸውን የመኖሪያ ስፍራ ለቀቁ
   መ. የእብሪት (ከመጠን ያለፈ ትዕቢት)

12. ሀ. ገሃነም፣ በጨለማ ጉድጓድ፣ ለፍርድ፣ አሳልፎ ከሰጣቸው
   ለ. ከጨለማ በታች፣ እስከ ታላቁ ቀን ፍርድ ድረስ ጠብቆእቸዋል።
   ሐ. በክፉዎች መላእክት ሰደደ።
   መ. አጋንንት
   ሠ. ሽባ ሊያደርጉ (ሊያጎብጡ)
   ረ. በሰማያዊ ስፍራዎችና በምድር

6. ሀ. 2 ሐ. 2 ሠ. 2 ሰ. 1 ቀ. 1
   ለ. 1 መ. 3 ረ. 1 ቸ. 3 በ. 3

13. "ሐ"፣ "መ" እንዲሁም "ሠ" ሐሰት ናቸው። የተቀሩት እውነት ናቸው።

6 ትምህርት

ሰው
ለፈጣሪው ተገዢ

የሰውን አፈጣጠር በተመለከተ ሰዎች በጣም የተለያዩ መልሶች አላቸው። ፈላስፋዎች ምክንያታዊ መግለጫቸውን ያቀርባሉ፣ የአገሪጋሚ ለውጥ ምሑራን የራሳቸውን አቋም ያንጸባርቃሉ፣ የሕብረተሰብ ሳይንስ አዋቂዎች ግምታቸውን ይገልጻሉ። የማያምኑ ሰዎች ጅማሬያቸውና ዕድገታቸውን ለመግለጽ የሚያደርጉት ጥረት ያደናግረናል፣ ምክንያቱም አነርሱ የሰው ልጅ ያለ ትርጉምና ያለ ዓላማ እንዲሁ በአጋጣሚ የተገኘ ነው ብለው ያምናሉ። በአንጻሩ መዝሙረኛው በለ አፈጣጠሩ በማስላስል ለእግዚአብሔር እንዲህ ይለዋል "ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና አመሰግንሃለሁ፣ ሥራህ ድንቅ ነው፣ ነፍሴም እጅግ ታውቀዋለች. . .ያልተሰራ አካሌን ዓይኖችህ አዩኝ፣ የተፈጠሩ ቀኖቼ ሁሉ. . ." (መዝ 139:14፣ 16)።

ምድርን በጽድቅ፣ በጥበብና በኃላፊነት ስሜት እንድናስተዳድራት በእግዚአብሔር ተፈጥረናል። እውቀትን፣ ስሜትንና ምግባራዊ ምርጫዎችን ማድረግ የሚያስችሉ ችሎታዎችን ስጥቶናል። ከፍተኛ ሥራዎች የማከናወን አቅም አለን ሆኖም ተፈጥሮአዊ በጠታችንን የማባከንና ስጦታዎቻችንን ሁሉ የስጠንን የመካድም ችሎታው አለን። እግዚአብሔር የለጠንን ታላቅ እምቅ ችሎታ መገንዘብ የምንችልበት መንገድ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ነው። አለመታዘዛችን ከሙሉ ችሎታችን ላይ አሁንም ሆነ ለዘላለም የመድረስ ዕድላችንን ይገፋብናል።

ተደም ባለው ትምህርታችን በመናፍስት ዓለም ዙሪያ ያለውን በቅርብ ተመ ልክተናል። አሁን ደግሞ በእግዚአብሔር ግባት ሥር ካሉት ፍጥረቶች ሌላ ውን ወገን ማለትም ሰውን እንመለከታለን። በዚህ ትምህርት "ሰው" ወይም "የሰው ዘር" የሚለው አነጋገር የሚያመለክተው ሁለቱን የያታ አባላት ማለት ወንዶችንና ሴቶችን ነው። ትምህርቱን በምታጠናበት ጊዜ ራስህን የተሻለ መረዳት እንደዚሁም የእግዚአብሔርን ሉአላዊነት የተቀበሉ ያለባቸ ውን ግዴታና መብቶቻቸውን በበለጠ ግልጽነት ማወቅ መቻል አለብህ።

የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል
- የሰው ጅማሬ
- የሰው ተፈጥሮ
- የሰው ኢ - ሙዋቲነት

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህንን ትምህርት ስታጠናቅቅ የሚከተሉትን ማድረግ መቻል አለብህ፦



- ስለ ሰው አፈጣጠር፣ ስለ ማንነት መታወቂያውና ስለ ነፍሱ ዘላለማዊነት መጽሐፍ ቅዱሳዊውን አመለካከት መግለጽ።
- ለሰው ልጅ ማንነት አስተዋጽኦ የሚያደርጉትን ባህርያት ለይቶ ማወቅ።
- አንድ ሰው ምግባራዊ ተጠያቂ የሚያደርገውን ውሳኔ የሚወስንበትን መንገድ መግለጽ።
- በራስህ ሕይወት የእግዚአብሔርን አምላል የማንጸባረቅ ፍላጎት እንዲያድርብህ ማድረግ።

የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. ለዚህ ትምህርት እንደ መሠረት እንዲያገለግልህ ዘፍ 1-3 ያለውን አንብብ። በተጨማሪ በደረስክበት ሥፍራ ያጋጠሙህን ጥቅሶች አንድ በአንድ አውጥተህ ማንበብህን አርግጠኛ ሁን።
2. ትምህርቱን እንደተለመደው አጥናው። ትምህርቱን ስታጠናቅቅ የሙከራ ፈተናዎቹን ሥራ፣ በትክክል መመለስህንም አረጋግጥ።

የሰው ፍጥረት

የሰው አፈጣጠር ልዩ ነው

ዓላማ 1 ሰው የእግዚአብሔር ልዩ ፍጡር ስለመሆኑ መረጃ የሚያቀርቡ መግለጫዎችን መምረጥ

"ሰው እንዴት በሕይወት ሊኖር ቻለ?" ለሚለው ጥያቄ መጽሐፍ ቅዱስ ምክንያታዊና ቀጥተኛ የሆነ መልስ ይሰጣል። ስለሰው አፈጣጠር፣ ስለተፈጠረበት ዓላማና ስለመጨረሻ ዕጣ ፈንታው መረጃዎችን ይሰጣል። ሰው የእግዚአብሔር ልዩ ፍጡር እንደሆነ ይገልጽልናል።

የሰው ልጅ ልዩ ነው። የእግዚአብሔር ቃል ሰው የመለኮታዊ ሥራ ልዩ ውጤት መሆኑን ያውጃል። እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፦ "... እኔ ምድርን ሰርቻለሁ፣ ሰውንም በእርሷ ላይ ፈጥሬአለሁ" (ኢሳ 45:11-12) ሌሎች ክፍሎች ተመሳሳይ ምስክርነት ያቀርቡልናል።

(1). ጥቅሶቹን እንብብና እያንዳንዱ ጥቅስ ስለ አፈጣጠር የሚነግረንን ጻፍ።

ሀ. ዘፍ 1:27	ሐ. ዘፍ 6:7	ሠ. ዘዳ 4:32	ሰ. ያዕ 3:9
ለ. ዘፍ 5:1-2	መ. ዘፍ 9:6	ረ. መዝ 100:3	

የሌሎች ፍጥረታት አፈጣጠር የተፈፀመው ወዲያውኑ ተግባራዊ የሚሆን ትዕዛዝ በተላለፉ በማሰተላለፍ ብቻ ነው (ዘፍ 1:20፣ 24)፤ ሰውን በመፍጠር ወቅት ግን እግዚአብሔር ልዩ ድርጊት አከናውኗል። በቅድሚያ ከምድር አፈር ሰውን እበጀው ከዚያ በኋላ የሕይወትን እስትንፋስ ባፍንጫው እፍ አሰበት (ዘፍ 2:7)፤ ሰውም ሕያው ነፍስ ያለው ሆነ። ይህ መለኮታዊ እስትንፋስ ሰውን በዘፍ 1 ከተጠቀሱት ሌሎች እንስሶች ሁሉ በላይ ከፍ ያደረገውን መንፈሳዊ ባህርይ እንዲኖረው አስችሎታል። ከዚህም በላይ ምድርን እንዲገዛና እንዲቆጣጠር እግዚአብሔር የሰጠው ትዕዛዝ በሰውና በፍጡር ሥርዓት በተፈጠሩት ሌሎች ፍጥረታት (ዘፍ 1:28) ሁሉ መካከል ያለውን ታላቅ ርቀት ያመለክታል።

ምድርን በሰው ልጆች ዘር እንዲሞላ፣ በምድር ላይ በሚገኙ ፍጥረታት ሁሉና ፍሬን በሚያፈሩ ዕፅዋት ሁሉ ላይ የገዢነት ሥልጣን ይኖረው ዘንድ፣ ሰውን እንዲዋሰድ በማድረጉ እግዚአብሔር በሰው ላይ ያሰውን ልዩ ትኩረት መመልከት እንችላለን (ዘፍ 1:28፤5:2)።

በሰውና በሌሎች ፍጥረታት ሁሉ መካከል ያለው ዋና ልዩነት ሰው በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠሩ ነው (ዘፍ 1:26)። ማንኛውም ሌላ

ፍጥረት በእግዚአብሔር አምሳል አልተፈጠረም፣ የፈጣሪው አምሳል የተሰጠው ሰው ብቻ ነው።

በሰዎችና ሰሌሎች እንስሳት መካከል ባሉት ታላላቅ ልዩነቶች የሰውን ልዩ ባህርይ ተጨማሪ መረጃዎችን እናገኛለን። ከእነዚህ ልዩነቶች አንዳንዶቹን ቀጥለን እንመልከት፦

❶. *ሰው የንግግር ኃይል አለው*፦ በዚህም ድንቅ ችሎታ አማካይነት ተለዋዋጭና ጥበባዊ በሆነ መንገድ ተጨባጭ፣ እውንና ረቂቅ የሆኑ እስተሳሰቦችን ያስተላልፋል። ማንኛውም እንስሳ ይህንን ማድረግ አይችልም፡

❷. *ሰው ሰውበት ደሰ የመሰኘት ችሎታ አለው*፦ እንስሳት ውብ የሆነ የአትክልት ስፍራን ከአስቀያሚ (ረግረግ ስፍራ) አስበልጠው ወይም መርጠው የሚመለክቱ አይመስልም።

❸. *ሰው ትክክል በሆነ ነገርና ስህተት በሆነ መካከል ያለውን ልዩነት የመለየት ችሎታ አለው*፦ እንስሳት ይህ ችሎታ የላቸውም። ለምሳሌ ያህል እንድ ውሻ እመጻኛ ስለሆነ የደረሰበትን ቅጣት ይጠላው ይሆናል፤ በተደጋጋሚ ቅጣት ምናልባት መታዘዝን እንዲያውቅ ሊሰማመድ ወይም ሊስለጥን ይችል ይሆናል። ያሁን እንጂ የዶሮዋን እንቁላል መስረቅ ወይም ጫጩቶቹዋን መብላት ከሥነ-ምግባር አንፃር ስህተት መሆኑን በፍጹም ሊማር አይችልም።

5. *ሰው በቅድሚያ ማቀድ፣ ወደ ፊት የሚያስፈልጉትን መጠበቅ እንዲሁም በሁኔታዎች ላይ ለውጥ ማምጣት ይችላል*። አዳዲስ የቤት እቅዶችን በማዘጋጀት እንደዚሁም አዳዲስ የሥነ ጥበብ ፈሊጦችን በማውጣት ሐሴት ያደርጋል። አካባቢውን ለመስወጥ፣ ኑሮንም ቀላልና የተሻለ ስማድረግ የማያቋርጥ ጥረት ያደርጋል። እንስሳት ግን የፈጠራ ወይም አርቆ የማሰብ ችሎታ የላቸውም። ወደ ፊት ስሚገጥሟቸው ነገሮች የሚያደርጉት ዝግጅት በተፈጥሮ በደመ-ነፍስ ብቻ የሚያደርጓቸው ምላሾች ናቸው። ለምሳሌ ያህል አእዋፍ ስጫጩቶቻቸው ጎጆ የመሥራት ደመ-ነፍሳዊ ፍላጎት ቢኖራቸውም በዘመናት ሁሉ ቅደመ እያቶቻቸው ሲሰሯቸው የኖሩትን እነዚያኑ ዓይነት ጎጆዎችን መሥራት ይቀጥላሉ።

ስለሆነም ሰው የእግዚአብሔር ልዩ ፍጡር መሆኑ ግልጽ ነው። ሰው የአጋጣሚ ውጤት እይደለም። ከዝቅተኛው የእንስሳት ሕይወት በዝግመተ ለውጥ አልተገኘም። ዓለምን የፈጠረው እግዚአብሔር እርሱ ራሱ ደግፎና እጽንቶ እንደሚጠብቃት ቀደም ባለው ትምህርት ተመልክተናል። ተፈጥሮ ተመልካች ወይም ተንከባካቢ ካጣ ከመሻሻል ይልቅ ጥራቱን እያጣ ይሄዳል። ነገሮች እያረጁ ይሄዳሉ። በሥርዓት ሊካሄድ የነበረው የመዘባረቅ ምልክት ማሳየት ይጀምራል። አንድን ሥርዓት ባለበት ሁኔታ ለማቆየትና እየተሻሻለም እንዲሄድ ስማድረግ ከሥርዓቱ ውጪ የላቀ እውቀትና

ኃይልም ያለው ሊሆን ይገባል። ይህ እጅግ ድንቅ የሆነው ፍጡር ማለትም ሰው፥ የተፈጠረው በልዑል እግዚአብሔር ልዩ እሰራር ነው (ቆላ 1:16-17)።

(2). ከሚከተሉት መግለጫዎች ሰው የእግዚአብሔር ልዩ ፍጡር ለመሆኑ መረጃ የሚያቀርቡት የትኞቹ ናቸው?

ሀ. የሰው አፈጣጠር የእፅዋትንና የእንሰሳትን ሕይወት የአፈጣጠር ሥርዓት የተከተለ ነው።
ለ. ከእግዚአብሔር አስትንፋስ የተነሳ ሕይወትን የተቀበለው ሰው ብቻ ነው።
ሐ. ሰው ለእፅዋትና ለእንሰሳት ሕይወት ላይ ገዢ እንዲሆን ተሰጥቶታል።
መ. ሰው በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ነው።
ሠ. ሰው በምድር ካሉት ሌሎች ፍጥረታት ሁሉ የተለየና የላቀም ነው።
ረ. ሰው ብቻ ከሌሎች ከፍተኛ ኃይላት ተፅዕኖ ነፃ ነው።

በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠር

ዓላማ 2 በተሰጡት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች የሰውን በእግዚአብሔር አምሳል መፈጠር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ የሚገልጹትን ማግኘት

ሰው በእግዚአብሔር ምሳሌ ወይም አምሳል እንደተፈጠረ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምራል (ዘፍ 1:26፣ 5:1፣ 9:6፣ 1ቆሮ 11:7፣ ያዕ 3:9) እንደ እግዚአብሔር ሁሉ ሰው ከአቅድና ከዓላማ አንጻር ማሰብ ይችላል። እያንዳንዳችን በራሳችን በሆነ መንገድ ጠቃሚና ውብ የሆነ ነገር ማበጀት እንችላለን። ራሳችን በምናደርጋቸው ጥናቶች ለእግዚአብሔር ጥበባዊ ሥራዎች መረጃዎችን ሊሰጡን የሚችሉ የተፈጥሮ መርሆዎችን መርምረን ማግኘትም እንችላለን። ይህ "የእግዚአብሔር አምሳል" ምን ሌላ የሚያካትተው ነገር አለ? የማያካትተውስ ምንና ምንን ነው?

"በእግዚአብሔር አምሳል" የሚለው አገላለጽ ሰው የእግዚአብሔር ትክክለኛ ግልባጭ ነው ማለት አይደለም። ሃሳቡ የሚያስተላልፈው በአንዳንድ መንገድ እግዚአብሔርን እንደሚመስል ነው። በክፍለ ትምህርት 1 እግዚአብሔር እንደማይታይና መንፈስም እንደሆነ ተመልክተናል። ስለሆነም በሰው ዘንድ ያለው የእግዚአብሔር አምሳል አካላዊ መመሳሰል እንዳልሆነ እናውቃለን። ከእግዚአብሔር ጋር ያለው መመሳሰል አካላዊ መመሳሰል ካልሆነ ምን ማለት ይሆናል?

❶. *አካላዊነት*። እግዚአብሔር መንፈስ ቢሆንም እንኳ የኛ ሰብአዊ መንፈስ ከመለኮታዊው መንፈሱ ጋር ግንኙነት ማድረግ ይችላል፤ ምክንያቱም እኛም እንደ እግዚአብሔር የአካላዊነት ሕልውና አለን። ግላዊ በሆነ

ግንኙነት ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት የማድረግ ችሎታ አለን። እርሱ እንደ ሚያደርገውም ከሌሎች ፍጥረታት ጋር ግንኙነት የማድረግ ችሎታም አለን።

❷ *ምግባራዊ መመሳሰል*። ሰው እንደ እግዚአብሔር በክፉና በደግ መካከል የመለየት ችሎታ አለው። በመጀመሪያ የሰው ሁለንተናው፥ ማለትም እውቀቱ ስሜቱና ፈቃዱ ወደ እግዚአብሔር ያዘነበለ ነበር። የሰው ውስጡን ምግባራዊነት ውስንነት የሌለበት የእግዚአብሔር ፍጹማዊ ምግባር ግልባጭ ነበር። ሰው የመምረጥና ተግባሩን በኃላፊነት የማከናወን ነፃነት አለው። ይህንንም ተግበር ላይ በሚያውልበት ወቅት፥ ሰው በሕይወቱ ሊፈተን፣ በሚዘናዊ ፍርድ ሊያድግና ቡሮው እርምጃ ሊያሳይ ይችላል። በዚህ በኩል ያለው ሐቅ የሚያመለክተው ሰው በክፉና በደግ መካከል መለየት አስፈላጊ መሆኑን እንደተገነዘበ ነው።

❸. *የማሰብ ችሎታ*። እግዚአብሔርንና ሌሎችንም ነገሮች የማወቅና የማመዛዘን ችሎታ ማለትም የምክንያዊነት ባሕርይ ወይም እውቀት ስላለው ሰው ከእግዚአብሔር "ምክንያዊነት" ጋር ምስል አለው። ይህ ችሎታ ሰው ከፈጣሪው ጋር ያለው የአስተሳሰብ መመሳሰል ተብሎም ይጠቀሳል።

❹ *የማስተዳደር ችሎታ*። መግዛትን ወይም መቆጣጠርን ተግባራዊ በማድረግ ችሎታው ሰው እግዚአብሔርን ይመስላል። ሰው ከእርሱ ይልቅ ብርቱ የሆኑትን እንሰሳት ማለማመድ ይችላል። የኤሌክትሪክን ኃይል ለማመንጨት ግድቦችን በመሥራት ወንዞችን ይገራል። ሥፍራዎች በተፈጥሮ ለምለም እንደሆኑ፣ በረሃዎችን እንዲለመልሙ ያደርጋል። በቀላል እንጋገር ይህ በእግዚአብሔር የተሰጠው ችሎታው እግዚአብሔር በመላው ዓለም ላይ ያለውን የገዢነት ሥልጣን ያንፀባርቃል።

❺. *ራስን ማወቅ*። በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ እኔነት ያለው ሕላዌ እንደመሆኑ መጠን ሰለ ራሱ ግንዛቤ አለው። አንድ ሕፃን ገና በትንሽነቱ ከተቀረው የቤተሰቡ አባል ሁሉ እርሱ የተለየ እንደሆነ ይረዳል። ያ ሕፃን አንድ ግለሰብ ነው። ከቤተሰቡ ወይም ከአካባቢው ባሕል የሚፈለግበት ምንም ነገር ቢሆን ይህ ግለሰብ የተለየ ሰው እንደ ሆነ ያውቃል። በመሆኑም ይህ ሰው የራሱ የሆኑ ሕልሞች፣ ፍላጎቶች፣ ተስፋዎች፣ ሥጋቶች እንዲሁም ቀልቃሽ ምክንያቶች አሉት። እርሱ ከሌሎቹ ግለሰቦች ሁሉ የተለየ ነው። ሌሎች ፍጥረታት ሰለ ራሳቸው ግንዛቤ የላቸውም።

❻. *ማሕበራዊ ባሕርይ*። ሰው ከመለኮት ላገኘው የማህበራዊነት ባህርይ መሠረቱ የእግዚአብሔር መውደድ ወይም ፍቅሩ ነው። እግዚአብሔር በዘላለም ውስጥ የፍቅሩን ትኩረት በሥላሴ መካከል ባሉት የመለኮት ሕላዌዎች ላይ አድርጓል። "አብ እንደ ወደደኝ እኔ ደግሞ ወደድኋችሁ፣ በፍቅሬ ኑሩ . . . እኔ እንደ ወደድኋችሁ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ ትእዛዜ ይህች ናት" (ዮሐ 15:9፣12)። ማሕበራዊ ባሕርይን ሰለተቀበልን

ከእግዚአብሔርና ከሌሎች ሰዎች ጋር ሕብረት ማድረግ እንሻለን። ሕይወታችንንም በማሕበራዊው መሠረታዊ እርከን ማለትም በቤተሰባችን ጉሪያ እናደራጃለን። ፍቅራችንና ለለሌሎች ሰዎች መገደዳችን በቀጥታ የሚመነጨው ማሕበራዊ ገጽታ ካለው ባሕርያችን ነው።

(3). የሚከተሉትን ጥቅሶች እውጣና በያንዳንዱ ጥቅስ ውስጥ ሰው እግዚአብሔርን ለመምሰሉ የተጠቀሰውን ግለጽ።

ሀ. ዘፍ፡ 2፡18	መ. መዝ 139፡13-16	ሰ. 1ጴጥ 1፡15
ለ. ኤፌ. 4:24	ሠ. ሮሜ 10፡8-11	
ሐ. ቆላ 3፡10	ረ. ዘፍ፡ 1፡26፣ 28	

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሰው እፈጣጠር ተጨባጭ ዘገባ ያቀርብልናል። ዘገባው ስለ ሰው ማንነትና በውስጡ ስላለው እምቅ ችሎታ ይናገራል። ሰው ከፈጣሪው ጋር ስለ መመሳሰሉ ያለውን ሐቅ ይገልጸል። ይህ ሰው ምን ያህል በጣም ልዩ እንደሆነና ከሌሎች ፍጥረታትም ምን ያህል የላቀ እንደሆነ እንድንመለከት ይረዳናል። በምግባሩ ካለው ከፍተኛ ደረጃ ጋር ሰው አንዳንድ እጅግ በጣም አስፈላጊ የሆኑ ኃላፊነቶች እንዳሉበት መጽሐፍ ቅዱስ በተጨማሪ ያስተምረናል። በሚቀጥለው ትምህርታችን እንደምንመለከተው እነዚህ ለሰው ያለበት ኃላፊነቶች ዘላለማዊ ዕጣውን የሚወስኑ ናቸው።

የሰው ተፈጥሮ

ዓላማ 3 የለውን ቁሳዊና ረቂቅ ገጽታዎች የሚመለከቱ መግለጫዎችን ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ማዛመድና የተሟሉ ማደረግ

ስለ ሰው ባህርይ በጣም የተሟላ መረዳት ካለን ለችግሮቻችን መፍትሔ ለማግኘት ቀላል ይሆንልናል። የሰው ልጅ በጣም ረቂቅ ፍጡር መሆኑ እርግጥ ነው፣ ድንቅ እካል፣ ንቁ አእምሮና በነፃና በደግ መካከል የመለየት ችሎታ አለው። እነዚህ በጣም ጉልህ ከሆኑት መታወቂያ ባህርያቱ ጥቂቶች ናቸው። ይህ እገላለጽ ሰው የሚታይ ቁሳዊ ወይም የሚዳሰስ እካል እንዲሁም የማይታይ፣ በቤተ ሙከራ ሊመዘንና ሊተነትን የማይችል ገጽታ እንዳለው ይገልጸልናል። እስኪ እሁን እነዚህን የሰውን ማንነት ልዩ ልዩ ገጽታዎች ወይም የማንነቱን መታወቂያዎች እንመልከት።

የሰው ተዳሳሽ ወይም ቁሳዊ ገጽታ

የለውን ቁሳዊ ወይም የሚዳሰሰውን ገጽታ ለይቶ ማወቅ ቀላል ነው። ይህ ማለት ሰለ ሌላው ለው የምናየው ነገር ነው። ሊመዘን፣ ሊለካ ትንታኔ ሊደረግበት የሚችል ነው። ይህ የሰው እካል ነው።

የእግዚአብሔር ቃል ስለ እካላችን እዘውትሮ ይናገራል። የተቤዠንበትም እንዱ ክፍል እድርጎ ይጨምረዋል (ሮሜ 8፡23፣ 1ቆሮ 6፡12-20)። መጽሐፍ ቅዱስ ለሰው እካል ምን ያህል ዋጋ ይሰጣል? ረቂቅ የሆነው የሰው ገጽታ ከቁሳዊው እካል ይልቅ እጅግ እስፈላጊ እንደሆነ (ማቴ 10፡ 28) ብንማርም፣ እካላችን ሊጠላ የሚገባው ወይም በፍጥረቱ ክፉ እንደሆነ እንድንቆጥር የሚያላስብ ነገር እላገኘንም። እንዲያውም ከዚህ ተቃራኒ በሆነ ሁኔታ ሐዋርያው ጳውሎስ እካላችን ከሞት በኋላ የሚበሰብስ ቢሆንም እንድ ቀን በታምራዊ መንገድ ትንሣኤ እንደሚያገኝ እስተምሯል። "ኢየሱስ ክርስቶስ. . . ክቡር ሥጋውን እንዲመስል የተዋረደውን ሥጋችንን ይለውጣል" (ፊልጵ 3:20-21)።

ሐዋርያው ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ የአማኞች እካል የክርስቶስ እካል ብልቶች እንደሆኑ ገልጿል። እሱ እንደተናገረው የአማኞች እካሎች የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደሶች ናቸው። በዚህም ምክንያት ክርስቲያኖች በሥጋቸው እግዚአብሔርን እንዲያከብሩ ያላስባቸዋል (1ቆሮ 6፡15፣ 19-20)።

ጌታ ኢየሱስ ራሱ፣ የለውን ሥጋ በለበስ ጊዜ ለሰው ሥጋ እጅግ ከፍተኛውን ክብር ሰጥቶአል። እካለ መጠን በደረሰበት ጊዜ ኢየሱስ በቁመት ያድግ እንደነበረ ሉቃስ ዘግቧል (ሉቃ 2:40)። እንዲያውም የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ ለእኛ የሚራራ ሊቀ ካህንና ኃጢአታችንን የሚያስተሰርይ እዳኝ ይሆን ዘንድ (ዕብ 2:14-15፣ 17-18) ጌታችን የእኛን ሥጋ መልበሱ እስፈላጊ እንደሆነ ገልጸልናል።

(4). ከዚህ ቀጥሎ ከ1-9 ያሉትን የእግዚአብሔር ቃል ጥቅሶች ከሀ-ሰ ካሉት ተገቢ መግለጫዎቻቸው ጋር እቀናጃቸው።

1. ዘፍ 1፡27፣31	4. መዝ 139፡13-16	7. ፊልጵ 3:20-21
2. ሮሜ 12፡1	5. ዕብ 2:14-15፣ 17-18	8. ሮሜ 8:23
3. 1ቆሮ 6:15፣19-20	6. 1ቆሮ 6:14	9. 1ቆሮ 12:12-27

ሀ. የሰው እካል እግዚአብሔር እጅግ መልካም ነው ብሎ የመለከረለት ድንቅ የእግዚአብሔር ፍጥረት ነው።
ለ. ኢየሱስ የለውን ሥጋ ስለለበሰ የሚራራ ሊቀ ካህናችን ሊሆን ይችላል።
ሐ. ለብዓዊ እካላችንና መላው ብልቶቻችን የክርስቶስን እካል ሥርዓት በመወከል የገለግላል።
መ. እካላችን እንደ መንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ ሊቆጠር ይገባዋል።
ሠ. ለብዓዊ እካሎቻችን በኢየሱስ ከርስቶስ ባገኘነው መቤገት ተካተዋል።
ረ. እካላችን በተቀደሰና ተቀባይነት ባለው መንገድ ለእግዚአብሔር እገልግሎት ሊውል ይገባል።
ሰ. ለብዓዊ እካላችን ከሙታን ይነሳል፣ የኢየሱስንም የከበረ ሰውነት ይመስል ዘንድ ይለወጣል።

የማይዳሰሰው ወይም ረቂቁ የሰው ገጽታ

የሚዳሰስውን የሰውን ገጽታ ለይቶ ማወቅ ቀላል ሲሆን ረቂቁን ወይም የማይዳሰሰውን የሰውን እቋም መግለጡ ግን እጅግ አስቸጋሪ ነው። ለምሳሌ ያህል በ1ተስ 5፡23 መጽሐፍ ቅዱስ ከሰው ሥጋ ጋር በመሆን የሰውን ሁለንተና ስለሚወክሉት ስለ ነፍስና መንፈስ ይናገራል። ይሁን እንጂ በማቴ 10፡28 መሰረት ነፍስ በአጠቃላይ ግዙፍ ያልሆነውን ገጽታችንን የምትወክል ይመስላል። ሁለታዋነት ወይስ ሦስታዊነት ያለን ፍጥረቶች ነን? ነፍስና መንፈስ አንድ ዓይነት ነገሮች ናቸው ወይስ ይለያያሉ?

ነፍስና መንፈስ የሰው ሁለንተና ሕላዌ ሁለት የተለያዩ ገጽታዎች መሆናቸውን ወይም አንድ የማይነጣጠሉ መሆናቸውን ለይቶ መናገር አስቸጋሪ ነው። ኢ-ተዳሳሽ ገጽታዎቻችንን በጥልቀት ስምንመረምርበት ጊዜ ይህንን አመለካከታችንን እጽንተን እንጠብቅ።

እንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሑራን እግዚአብሔር ሰውን በፈጠረ ጊዜ ስለው ላይ እፍ ያለው እንደ ሥርዓት ይሄውም ሕያው ነፍስ እንደሆነ ያምናሉ። ሌሎቹ ደግሞ ኢ-ተዳሳሽ የሆነው የሰው ሕልውና ሁለት አንዳሮች አሉት ብለው ያምናሉ። ከእነዚህም አንዱ ለሥጋዊ ሕይወታችን መሠረታዊ ሥርዓት የሚያስይዘው ወይም አስትንፋስ የሚስጠንና ሕያዋን ፍጥረታት የሚያደርገን ነፍስ ነው። ሌላኛው ደግሞ ስምክንያታዊ ሕይወታችን መሠረት የሆነው ወይም ከማመዛዘን አስዚያም ከመረዳት ጋር የተያያዘው መንፈስ ነው ይላሉ።

(5). የሚከተሉትን ጥቅሶች ካነበብክ በኋላ ኢ-ተዳሳሽ ስለሆነው የሰው ገጽታ የሚያመለክቱት ነጠላነቱን ወይም ጥንድነቱን መሆኑን ግለጽ።

ሀ. ዘፍ 2፡7 ሐ. 1ቆሮ 5፡3 ሠ. 1ተስ 5፡23
ለ. መዝ 42፡6 መ. ዕብ 4፡12

የምክኑያዊው ሕይወት አስፈላጊ ገጽታዎች አሉት። ከእነዚህም የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ የሰብእና ገጽታዎች ናቸው። እነርሱም፦

1. *እውቀታዊ ገጽታ*- የመረዳት፣ የማመዛዘንና የማስታወስ ችሎታ።

2. *ስሜታዊ ገጽታ*- በስሜት የመነካት፣ ስምናውቀው ወይም በምንለማ መደው የመለወጥ ችሎታ።

3. *ፈቃዳዊ ገጽታ*- የመምረጥ የመወስንና ተግባራዊ የማድረግ ችሎታ።

4. *ኅሊናዊ ገጽታ*- ከታወቀ የትክክለኛነትና የስህተት መመዘኛ አንፃር ራስን የማወቅ ችሎታ።

ስለ እግዚአብሔር ማንነት በተማርነው ትምህርታችን (ክፍለ ትምህርት 1) የአካላዊነት መሠረታዊ ክፍሎች ከሆኑት ከእውቀት ከስሜትና ከፈቃድ ጋር እንደተፈጠርን ተምረናል። እነዚህ ልዩ መታወቂያዎች ከእግዚአብሔርና ከሌሎች ስዎችም ጋር ኃላፊነት በሚስማውና ትርጉም ባለው መንገድ ግንኙነት እንድናደርግ ያስችሉናል። እነዚህ ኢ-ተዳሳሽ የሆኑት ገጽታዎቻችን ተዳሳሽ ከሆነው ሕልውናችን ጋር በመሆን ሙሉና ፍጹም የሆነ ሕይወት እንድንኖር ያስችሉናል። አካባቢያችንን እንቆጣጠራለን፣ ለኑሮአችን የሚያስፈልገንንም ከዚያ እንወስዳለን። መተባበር ስስፈነባቸው ማህበራዊ ክልሎች ከሌሎች ስዎች ጋር እብረን መሥራት እንማራለን። ከሁሉም ይልቅ ትርጉም ላለው ሕይወትና ለዘላለም ደኅንነት የሚያስፈልገንን ሁሉ ያቀረበልንን ፈጣሪያችንን ደስ ለማስኘት እንጥራለን። በሚቀጥለው የጥናታችን ክፍል እንደምንመለከተው ፈቃዳችንና ሕሊናችን የረቂቅ የኢ-ተዳሳሽ ማንነታችን አስፈላጊ ክፍሎች ናቸው።

(6). ቀደም ብለን የተመለከትናቸውን እውነቶች መሠረት ስማድረግ ከሚከተሉት ሐሳቦች ውስጥ እርግጠኝነት መሆን የምንችለው

ሀ. ስው ከሦስት ማለትም ከሥጋ፣ ከነፍስና ከመንፈስ የተፈጠረ መሆኑን ነው።
ለ. ስው ሦስት ገጽታዎች ያሉት ሕላዌ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስተምራል።
ሐ. ስው ከሁለት ማለትም ከሥጋና ከነፍስ የተፈጠረ ነው።
መ. ስው ሁለት ገጽታዎች ያሉት ሕላዌ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ስግልጽ ያስተምራል።
ሠ. የእግዚአብሔር ቃል ስለ ሥጋ፣ ነፍስ፣ መንፈስ፣ የሕይወት አስትንፋስ እንዲሁም ስለ ስው ማንነት ለሚገልጹ ሌሎች አባባሎች ይናገራል እንጂ ሰው ሁለታዊ ወይም ሦስታዊ ማንነት ይኑረው አይኑረው በትክክል አይገልጽም።

(7). የሰው ምክኑያዊ ሕይወት አራት ገጽታዎች።

1. 3.
2. 4. ናቸው።

ምግባራዊ ገጽታዎች

ዓላማ 4 ሥነ-ምግባራዊ ምርጫዎች ማድረግን ስተመለከተ ስለ ሕሊናና ስለ ፈቃድ ተግባር የተጠቀሱ እውነተኛ መግለጫዎችን መገንዘብ

ቀደም ሲል ባጠናነው በኢ-ተዳሳሽ ሕላዌያችን የሚገኙት የምክኑያዊነት ልዩ መታወቂያዎች ትክክለኛ ወይም የተሳሳተ ተግባራዊ እርምጃ እንድንወስድ ያዘጋጁናል። እውቀታችን የትኛው ትክክል የትኛው ደግሞ ስህተት እንደሆነ ለመለየት ያስችለናል። ስሜታችን ስዚህ ወይም በዚያ

በአንደኛው አቅጣጫ እንቅስቃሴ እንድናደርግ ያሳበበናል፣ ፍቃዳችንም በዚህ ጉዳይ ውሳኔውን ያደርጋል። ይሁን እንጂ አራተኛው ገጽታ ማለትም ሕሊናችን ተሳትፎ የማያደርግ ከሆነም ምንም ሥነ-ምግባራዊ እርምጃ መውሰድ አይቻልም።

ሕሊናችን የተወሰኑ ተግባራዊ እርምጃዎችን በተመለከተ የእግዚአብሔር ሥነ-ምግባራዊ ሕግ በእኛ ላይ ተፈጻሚ እንዲሆን የሚናገረን እንዲሁም እንድንታዘዘውም የሚያበረታታን "ውስጣዊ ድምጽ" ተደርጎ ሊገለጽ ይችላል። የዚህን ሥነ ምግባራዊ ኃይል ባህርይ በበለጠ ግልጽነት መረዳት እንችል ዘንድ ከተግባራችን ጋር ካላቸው ግንኙነት አንፃር ሕሊናንና ፈቃድን አሁን መመልከት እንጀምራለን።

ሕሊና

ሕሊናችን ከአመለካከታችንና ከተግባራችን ጋር የተያያዘ መሆኑን በመጠኑ ተመልክተናል። ይህ ከፍል እግዚአብሔርን ደስ ሊያሰኙ ወይም ሊያሳዝኑ የሚችሉ ተግባራዊ እርምጃዎችን ወይም የአመለካከት አዝማሚያዎችን አመዛዝነን ተገቢ ውሳኔ መስጠት የሚያስችለን ነው። እግዚአብሔር በቃሉ ተቀባይነት ያለውን የኑሮ መስፈርት አስቀምጧል። የምንቀበለውን መለኮታዊ እውነት መማራችንና ተግባራዊ ማድረጋችን እንዴት መኖር እንደሚገባን መረዳት እንድናገኝ ይረዳናል። ስለሆነም በቃሉ አማካይነት ስለ እግዚአብሔር ፍቃድ የምናውቀውና በዕለታዊ ኑሮአችን ይህንን እውነት ተግባራዊ ለማድረግ የተማርነው ሁለቱ ነገሮች ሕሊናችን መሥራት የሚችልበትን መሠረት ያዘጋጃሉ።

ሕሊና የምናስላስላቸውን አመለካከቶች ወይም ተግባራዊ ልናደጋቸው በመዘጋጀት ላይ የምንገኝባቸውን እርምጃዎች ትክክለኛነት ወይም ስህተተኛነት ይቆጣጠራል (ያበጠነቅቃል ወይም ጥቆማ ያቀርባል)። "እነርሱም ሕሊናቸው ሲመስክርላቸው አሳባቸውም እርስ በርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ" (ሮሜ 2:15) በማለት ሐዋርያው ጳውሎስ የዚህን ምሳሌ አቅርበልናል።

ለምሳሌ ያህል ውሳኔ መወሰን ያለበት ታደሰ የተባለ ክርስቲያን ነጋዴ አስ ብለህ አስብ። "ከአንድ አስፈላጊ ነጋዴ ጋር እራት ለመብላት ርኩሰት የተሞላበት መዝናኛ ከሚቀርብበት ሥፍራ ልሂድ ይሆን? ወይስ ግብዣውን ባለመቀበሌ የንግድ ግንኙነት የማጣ ብሆን እንኳ ይህንን እርምጃ መውሰድ ስህተት ነው ብዬ በአቋሜ ጸንቼ ልቁምን?" ብሎ ራሱን ይጠይቃል።

የታደሰ ቋሚ መመሪያ የእግዚአብሔር ቃል ነው። በማይመች ሁኔታ ከማያምኑ ጋር ስለ መጠመድ እግዚአብሔር ምን እንደሚል ያውቃል (2ቆሮ 7:1፣ 1ቆሮ 15:33)። የቀረበለትን ግብዣ መቀበል ስህተት እንደሆነ ሕሊናው ይመስክርለታል፣ ምክንያቱም ከእግዚአብሔር መመሪያ ጋር ይቃረናል። እግዚአብሔር እንደሚፈልግበት የመኖር ግዴታ እንዳለበትም

ያሳስበዋል። ስለሆነም የእግዚአብሔርን ቃል መስረት በማድረግ የታደስ ሕሊና በትክክለኛውና በተሳሳተው መካከል ይለያል። እንግዲህ ታደስ ክርስቲያን በመሆኑ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር ያለው ሕሊናው ይናገረዋል።

ታደስ የሕሊናውን ምስክርነትና ምግባራዊ ኃላፊነቶቹን የሚዘነጋ ከሆነ ኃፍረትና ጸጸት ይሰማዋል፣ ደግሞም በወሰደው እርምጃ ምክንያት ሥጋት ይይዘዋል። ስፈተና እጁን መስጠት የውድቀት ስሜትን ያስከትላል፣ ይህም የውድቀት ስሜት እንደ እግዚአብሔር *መመሪያ መሠረት* መኖር ያለመቻል ስሜት ነው። ከውድቀት ጋር የተያያዙት ስሜቶች ኃፍረት፣ ጸጸትና ፍርሃት የሕሊና ሳይሆን የስሜት ገጽታዎች ናቸው። እንግዲህ ሕሊና ለአእምሮአዊ ዝንባሌያችንና ለባህሪያችን እንደ ዳኛ ሆኖ ያገለግላል።

(8). ሕሊናን አለመታዘዝ ለክርስቲያን ስሜቶች ያስከትልበታል። የተባሉትን ሦስት

እግዚአብሔር ከዚህ ውስጣዊ ተቆጣጣሪ ወይም "ድምጽ" ጋር በስ ፈጠረን ሕሊናችንን እንዴት መጠቀም እንዳለብንና ስላለበትም ውሱንነት መረዳት ይገባናል። በመጀመሪያ እንደ ማወቅ ችሎታችን ሁሉ ሕሊናችንም ባደግንና በበሰልን መጠን እየዳበረ ይሄዳል። ኃላፊነታችንን በምንረዳበት ጊዜ የተግባራችንን ውጤት እየተገነዘብን እንመጣለን። በሁለተኛ ደረጃ መጽሐፍ ቅዱስ ሕሊና ሊጎድፍ ሊበላሽና ሊደነዝዝ እንደሚችልም ያስተምረናል።

1. "እንዳንዶች ግን ጣዖትን እስከአሁን ድረስ በለ ለመዱ ስጣዖት የተሰዋ ነው ብለው ይበላሉና ሕሊናቸው ደካማ ስለ ሆነ ይረክሳል" (1ቆሮ 8:7)

2. "ሁሉ ለንጹሆች ንጹሕ ነው፣ ስርኩሳን ለማያምኑ ግን ንጹሕ የሆነ ምንም ነገር የለም፣ አእምሮቸውም ሕሊናቸውም ረክሶአል" (ቲቶ 1:15)

3. ". . .በውሸተኞች ግብዝነት የተሰጠውን የአጋንንትን ትምህርት እያዳ መጡ... በገዛ ሕሊናቸው እንደሚቃጠሉ ደንዝዘው . . . " (1ጢሞ 4:2)

በክርስትና ሕይወት ግድየለሽ መሆን፣ የሕሊናን ድምጽ ችላ ማለትና እምነትን መጣል በእግዚአብሔር የተሰጠን ሕሊና እንደሚገባ ሥራውን እንዳያከናውን ሊያደርግ እንደሚችል እነዚህ የእግዚአብሔር ቃል ክፍሎች ያመልክታሉ። ይሁን እንጂ መጽሐፍ ቅዱስ ሕሊና ሊደመስስ እንደሚችል እያመለከተንም።

በሦስተኛ ደረጃ ሕሊና ስህተት አልባ አይደለም። ይህም አንድ ሰው የተሳሳተ *መመሪያ* ከቀረበለት ሊሳሳት ይችላል ማለት ነው። በደማስቆ መንገድ ከተስማመደው ገጠመኝ ቀደም ብሎ ሐዋርያው ጳውሎስ በተሳሳተ ባህሪው በጣም እልከኛ ነበር። ትክክለኛውን ነገር የሚያደርግ ይመስለው ነበር። የነበረው ቀናተኛ መንፈስ እንዲሁም ነቀፋ የሌለው ባህርይ

የሚመለጡ ነበሩ፣ ይሁን እንጂ ተግባሮቹ አስደንጋጭ ነበሩ፤ የማመዛዘን ችሎታው የተሳሳተውን የብሉይ ኪዳን ፍቺ ስለተለማመደ ሐሊናው በዚያ ፍቺ ላይ የተመሰረተ ምስክርነት እየሰጠው አሳተው (የሐዋ 9ን ተመልከት)። እንግዲህ ሕሊናችን በምግባራችንና በአመለካከታችን ላይ ብያኔውን (ፍርዱን) የሚያስተላልፈው የሚከተሉትን ሁኔታዎች መሰረት በማድረግ ነው።

1. ስለ እግዚአብሔር ሕልውና ያለን እውቀት
2. የተገለጠው የእግዚአብሔር ፈቃድ
3. እግዚአብሔር የሰጠን ሥነ-ምግባራዊ ግንዛቤ
4. በትምህርት ያገኘናቸው ነገሮች (በሕሊናችን እንዲቀመጥ የተደረገው)
5. የተቀበልናቸው የማሕበራዊ ኑሮ መስፈርቶች

በእግዚአብሔር ዘንድ ተጠያቂነት እንዳለብን እናውቃለን። ይሁን እንጂ ከኃጢአትና የእግዚአብሔርን መመሪያ ከመጣስ የተነሳ የማሕበራዊ ኑሮ መስፈርቶች ሁልጊዜ አንድ ዓይነት አይደሉም። ስለዚህም ምክንያት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለው ብቸኛው የሕሊና መመሪያ መንፈስ ቅዱስ የሚተረጉምልንና በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሰረተው መመሪያ ነው።

(9). አውነተኛ ከሆነው ከአያንዳንዱ መግለጫ አንፃር ያለውን ፊደል ክበበው።

ሀ. ሕሊና ተቀባይነት ካለው መመሪያ አንጻር ኃላፊነት የሚሰማው እኗኗር መኖር አለመኖራችንን ይነግረናል።
ለ. ትክክለኛና ስህተት የሆነውን በመለየት ረገድ ክርስቲያኖች ብዙውን ጊዜ በማሕበራዊ መስፈርቶች ሊመሩ ይችላሉ።
ሐ. ሕሊና ምንጊዜም የተመሰረተበትን መመሪያ ጠብቆ ይሄዳል።
መ. በእግዚአብሔር ቃል መመሪያ ላይ የተመሰረተ ከሆነ ሕሊና ሊበላሽ፣ ሊጎድፍ ወይም ሊደነዝዝ አይችልም።
ሠ. የክርስቲያንን ሕሊና በዋናነት የሚቀርጸው ለትክክለኛና ለተሳሳተ ተግባር የሚሰጠው ትርጉም ነው።
ረ. ሕሊና ያለማቋረጥ አልሰማህም ከተባለ ሊበላሽ፣ ሊጎድፍና ሊደነዝዝ ይችላል።
ሰ. አንድ ሰው ሕሊናው ከሚነግረው ተቃራኒ በሆነ መንገድ ድርጊቱን የሚቀጥል ከሆነ ሕሊናው ሊደመሰስ ይችላል።

ፈቃድ

ልንወስድ የሚገባንን እርምጃ አንድንመርጥ ወይም አንድንወስን የሚያስችሰን ፈቃዳችን ነው። ስለምንወስደው ማንኛውም እርምጃ ስሜታችንን ከመግለጻችን በፊት ልናውቀው ይገባናል። ከዚያም በኋላ አውቀታችንና ስሜታችንን መሰረት አድርገን ፈቃዳችንን ተግባር ላይ በማዋል

የምንወስደውን እርምጃ እንመርጣለን። ከብሀሪያችን ጋር ሊሄድ የሚችለውን ማንኛውንም ነገር በነፃነት መምረጥ እንችላለን። ለመሮጥ መፍቀድ እንችላለን፣ ሆኖም እንደ ዓሣ በውሃ ውስጥ ለመኖር መፍቀድ አንችልም። መሮጥ ከሰው ባሕርይ ጋር የሚሄድ ነው። በውሃ ውስጥ መኖር ግን አይደለም። በሚቀጥለው ትምህርታችን እንደምንመለከተው ሰው ጻድቅ ለመሆን በመፍቀድ ምግባራዊ አቋሙን መለወጥ እንዳይችል በኃጢአት ምክንያት ውሱን ሆኗል።

እንግዲያውስ በፈቃድ ላይ ተጽእኖ የሚያሳድረው ምንድነው? ፈቃድ ሙሉ በሙሉ በሰው ቁጥጥር ሥር ነው ወይስ በእግዚአብሔር? በውሳኔ አሰጣጣችን ሂደት ላይ ሚና ያለው ምንድነው? የሰውን ባሕርይ በሙላት በምናጠናበት ወቅት እስኪ እነዚህን ነገሮች እንመርምር።

እግዚአብሔር ሰውን በፈጠረ ጊዜ ለሰው የመምረጥን ኃይል ማለትም ኃጢአት የማድረግን ኃይልና ኃጢአት ያለማድረግን ኃይል በጥቆታል። እግዚአብሔር በኤደን ገነት ክስቀመጠው በኋላ ከርሱ ጋር ሕብረት በማድረግ መቀጠል የሚችልበትን ሁኔታ ገልጾለታል።

> "እግዚአብሔር እምላክም ሰውን እንዲህ ብሎ አዘዘው። ከገነት ዛፍ ሁሉ ትበላለህ፣ ነገር ግን መልካምንና ክፉን ከሚያስታውቀው ዛፍ እትብላ ከእርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ" • (ዘፍ 2:16-17)።

ከእግዚአብሔር ስተሰጠው ስዚህ መመሪያ አዳም የሰጠው ምላሽ ምን ነበር? የውሳኔ አሰጣጡ ሂደት ምናልባት ይህንን ስልት የተከተለ ሳይሆን አይቀርም፦

1. አዳም *በማወቅ ችሎታው* የእግዚአብሔርን መመሪያ ተቀብሎ እግዚአብሔር የተናገረውን ነገር ተረድቶ ነበር።
2. *ስሜቶቹ* ስእግዚአብሔር ቃል ትክክለኛነት ማረጋጫቸውን ሰጥተዋል። ፈጣሪውና ሉአላዊ ጌታው እንደመሆኑ እግዚአሔር ይህንን መመሪያ የመስጠት መብት አለው።
3. በአባቢቱ የቀረበለትን ፈተና በመቀበልና ባስመቀበል መካከል እንዲወስን ፍቃዱ ዝግጁ ነበር (ዘፍ 3:4-6)።
4. በዚህ ወሳኝ ወቅት የአዳም ሕሊና ከእግዚአብሔር መመሪያ ተቃራኒ የሆነ እርምጃ የመውሰድን ውጤት መዘነ።
5. *ፈቃዱን በመተግበር* አዳም በፈተናው ተማረከ።

ስለሆነም አዳም ሆነ ብሎ የእግዚአብሔርን ቃል ተላለፈ፣ ያስከተለበትንም ቅጣት ወዲያው ተቀበለ። የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ እንዳልጠበቀ እንዲገነዘብ በማድረግ ሕሊናው ወቀሰው። ትዕዛዝን በመተላለፍ የፈጸመው ተግባር ቅንነቱን ስለ ገፈፈው (ዘፍ 3:7-10) ሃፍረት፣ ጸጸትና ፍርሃት ተሰማው። አሁን ማንነቱ ተበላሽቷል። ከነበረው የቅንነት ሁኔታ ወደ ብልሹ ሁኔታ

ወድቋል። አዳም የእግዚአብሔርን ሞገስ ካጣበት ጊዜ ጀምሮ የሰው ልጅ በኃጢአተኛ ተፈጥሮው ምክንያት ውሱን ሆኗል። ያለ እግዚአብሔር እርዳታ ለእግዚአብሔር ታዛዥ ለመሆን መፍቀድ አይችልም። ጳውሎስ "በእኔ ማለት በሥጋዬ በጎ ነገር እንዳይኖር እውቃለሁና፣ ፈቃድ አለኝና መልካሙን ግን ማድረግ የለኝም" (ሮሜ 7:18) ብሏል።

ይሁን እንጂ እግዚአብሔር ሰውን በጥፋት ውስጥ መተው ደስ አላሰኘውም። ኃጢአቱን እንዲናዘዝና እርሱም ያዘጋጀለትን ደኅንነት እንዲቀበል በመጋበዝ (ቲቶ 2:11) በጥፋት ባለበት ሁኔታ እግዚአብሔር ፀጋውን ያቀርብለታል። በዚህን አጋጣሚ ነው መንፈስ ቅዱስ የሰውን ፈቃድ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስ በማግባባት እርምጃውን የሚወስደው (ፊልጵ 2:13)። ወደ እግዚአብሔር የሚመለሱ የእግዚአብሔር ልጆች የመሆን ሥልጣን አላቸው (ዮሐ 1:12)።

እግዚአብሔር በኃጢአት ለወደቀው ሰው ጸጋውን በማቅረብ ክርስቶስን እንደ አዳኝ አድርጎ እንዲቀበል ቢያስችለውም ያንን እንዲያደርግ ግን አያስገድደውም። ሰው ፈቃዱን ተግባራዊ በማድረግ ግብዣውን በመቀበል የእግዚአብሔር ልጅ መሆን ይችላል፣ ወይም ግብዣውን በመቃወም ከእግዚአብሔር መርገም (ፍርድ) በታች ሊወድቅ ይችላል። ይህንን ጥያቄ በመወሰን በኩል የሰው ፈቃድ ነፃ ነው። በዚህ ሂደት ውስጥ የእግዚአብሔርም የሰውም ፈቃድ ድርሻ አላቸው (ቲቶ 2:11-12፣ ዮሐ 7:17)።

(10). ከዚህ ቀጥሎ ከተራ ቁጥር 1-4 ያሉትን ጥቅሶች ከሀ-መ ካሉት መግለጫዎች ጋር አቀናጃቸው።-

1. ዮሐ 7:17
2. ፊልጵ 2:13
3. ቲቶ 2:11-12
4. ሮሜ 7:18

ሀ. የእግዚአብሔር ጸጋ እርኩሰትና ዓለማዊ ምኞትን እንድንቃወም ያስተምረናል።
ለ. መፈለግንም ማድረግንም በእናንተ የሚሰራ እግዚአብሔር ነው።
ሐ. ፈቃዱን ሊያደርግ የሚወድ ቢኖር ይህ ትምህርት ከእግዚአብሔር ቢሆን. . .ያውቃል።
መ. ፈቃድ አለኝና መልካሙን ማድረግ ግን የለኝም።

(11). ወደ ተግባር ወይም ውሳኔ አስጣጥ በሚያመራው ሂደት የሰው የማሰብ ክፍሎች ወይም ኃይሎች በሙሉ በሥራ ላይ እንደሚሆኑ እንመለከታለን። ሂደቱን ለመግለጽ የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች አጠናቃቸው።-

ሀ. የማወቅ ችሎታ. . .
ለ. ስሜቶች. . .
ሐ. ሕሊና . . .
መ. ፈቃድ . . .

የማሰብ ክፍሎቻችን ሥነ-ምግባራዊ ውሳኔዎችን በማድረግ እስከተሳተፉና አእምሮአችን በመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ላይ እስካተኮረ ድረስ መንፈስ ቅዱስ መልካም እንድናደርግ በጎ ተጽእኖ ያሳድርብናል (ሮሜ 8:5-9፣ 12-14)። ደግሞም ወደ እርሱ ፍላጎትም እንዲያመጣን በእኛ ውስጥ ይሰራል (ፊልጵ 2:13)። በመንፈስ ቅዱስ ሕልውና ውስጥ መኖርን መማርና ከመንፈስ ቅዱስ ፈቃድ ጋር አብረን መጓዝ ወደ ክርስቲያናዊ ብስለት ደረጃ በደረጃ ይመራል (ገላ 5:16-18፣25)። በእያንዳንዳችን ሕይወት ውስጥ የሚታይ የእድገት ልምምድ ነው።

የሰው ኪ - መሞቲንት

ዓላማ 5 የዘላለማዊነትን ሃሳብና ሰው በሥጋ ከሞተ በኋላ ስለሚሆነው መግለጫ መስጠት

ለው በሚሞትበት ጊዜ ምን ይሆናል? ከሞት በኋላ በለሚሆነው ብዙ የማናውቃቸው ነገሮች አሉ፣ ሆኖም ከሞት በኋላ ሕይወት እንዳለ በመግለጽ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረን አንዳንድ ነገሮች አሉ።

ሥጋዊ ሞት ሰውነታችን ሥራውን ባቆመ ጊዜ የሚሆነው ነገር ነው። ሥጋችን ይበሰብሰና ወደ አፈርነት ይመለሳል (ዘፍ 3:19 ተመልከት) የማይዳሰሰው የሰው ክፍል ግን ማለትም መጽሐፍ ቅዱስ ነፍስ ወይም መንፈስ በማለት የሚጠራው ክፍል ሕያው ሆኖ መኖሩን ይቀጥላል። እያሌ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች ይህንን ያረጋግጣሉ።

ሉቃ 23:43፡- "ኢየሱስም እውነት እልሃለሁ፣ ዛሬ ከእኔ ጋር በገነት ትሆናለህ' አለው"
2ቆሮ 5:8፡- "ከሥጋ ተለይተን በሰዶት መኖር በጌታም ዘንድ ማደር ደስ ይለናል"
ፊልጵ 1:22-23፡- "በሥጋ መኖር ለእኔ የሥራ ፍሬ ቢሆን ምን እንድመርጥ እላለታውቅም... ልሄድ ከክርስቶስም ጋር ልኖር እናፍቃለሁ፣ ከሁሉ ይልቅ እጅግ የሚሻል ነውና፣. . ."
ዮሐ 5:24፡- "...ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፣ ከሞትም ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም"

የሰው ሥጋዊ ሞት አዳም ኃጢአትን ባደረገ ጊዜ ከደረሰበት እርግማን አንዱ ነው፡- ". . .አፈር ነህና ወደ አፈርም ትመለሳለህና" (ዘፍ 3:19)። ክርስቲያን ሲሞት በተሟላ ቁሳዊና ረቂቅ ሕላዌ መኖሩን ቢያበቃም የከበረ ሰውነት በሚቀበልበት የክርስቶስ ዳግም ምፅአት የከበረ ተስፋ ይኖረዋል። ኢየሱስ በሞቱና በትንሣኤው እኛም ከሙታን ተለይተን እንደምንነሳ ማረጋገጫ ሰጥቶናል። በ1ቆሮ 15:42-49 ይህ ሁኔታ ተገልጿል፡-

"የሙታን ትንሣኤ ደግሞ እንዲሁ ነው። በመበስበስ ይዘራል፣ ባለመበስበስ ይነሳል፣ በውርደት ይዘራል፣ በክብር ይነሳል፣ በድካም ይዘራል፣ በኃይል ይነሳል፣ ፍጥረታዊ አካል ይዘራል፣ መንፈሳዊ አካል ይነሳል። ፍጥረታዊ አካል ካለ መንፈሳዊ አካል ደግሞ አለ። እንዲሁም ደግሞ፦ 'ፊተኛው ሰው አዳም ሕያው ነፍስ ሆነ' ተብሎ ተጽፎአል፣ ኋለኛው አዳም ሕይወትን የሚሰጥ መንፈስ ሆነ። . . .የዚያንም የመሬታዊውን መልክ እንደለበስን የሰማያዊውን መልክ ደግሞ እንለብሳለን" ፲፭፡

ከኃጢአቱ ንስሐ ያልገባ ሰው ሲሞት ከፍተኛ ስቃይ ባለበት ገሃነም ወይም ሲያል በተባለው በፍራ ንቁ ሕሳዌ በተባበስ ሁኔታ ይኖራል። ኢየሱስ ስለ ሀብታሙ ሰውና ስለ አልአዛር በተናገረው ታሪክ (ሉቃ 16:19-24) የዚህ ሁኔታ ጭላንጭል ቀርቦልናል። ኢየሱስ በንግግሩ የገለጸው ባለጠጋ በገሃነም ሆኖ ማሰብ፣ ማስታወስ፣ መናገር እንዲሁም ስሜትን ማገናዘብ ይችል ነበር። ራሱን የማወቅ ችሎታውንም እንደያዘ ነበር።

ስለሆነም ሰው የማይሞት ሕሳዌ ሆኖ በእግዚአብሔር እንደተፈጠረ እንመለከታለን። የክርስቶስን የቤዛነት ሥራ ተቀብሰው ለሚያገለግሉትና ለሚታዘዙት ይህ የተባረከ ተስፋ ነው። አማኞች በሚሞቱበት ጊዜ ነፍሳቸው ወዲያውኑ በጌታ ፊት ይቀርባል። በዳግም ምፅአቱ ወቅት የሞቱው ሥጋቸው ትንሣኤ ያገኝና የከበረ ሥጋ ለመሆን ይለወጣል (1ቆሮ 15:50-57)። ያ ቀን ምን ያህል የከበረ ቀን ይሆን! ሆኖም አማኝ ያልሆነው ከእግዚአሔር ፊት በመራቅ ዘላለማዊ ፍርድና ስቃይ ይቀበላል (ራእ 20:7-10 ተመልከት)።

(12). ቀደም ሲል የተመለከትናቸውን ሃሳቦች መሠረት በማድረግ በማስታወሻ ደብተርህ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ።

ሀ. በምንሞትበት ጊዜ ሥጋችን ምን ይሆናል?
ለ. በሞት ወቅት ነፍስ ወይም መንፈስ ምን ይሆናል?
ሐ. በክርስቶስ ዳግም ምጻት ወቅት አማኞች ምን ይሆናሉ?
መ. ክርስቶስን ያልተቀበሉት የዘላለም ዕጣ ምን ይሆናል?
ሠ. "ሰው የማይሞት ሕሳዌ ነው" የሚለውን አበባል ግለጽ?

የሙከራ ፈተና

ከትክክለኛው መልስ አንጻር ያለውን ፈደል ክበበው።

1. ስለ ሰው አፈጣጠር ያለው መጽሐፍ ቅዱሳዊው አመለካከት።

ሀ. በአንድ ወቅት አግዚአብሔር ከፈጠራቸው ብዙ ሕያዋን ፍጡሮች አንዱ ብቻ እንደሆነ ይገልጻል።
ለ. ከሌሎች ፍጥረታት በላይ እንደሆነና በአግዚአብሔርም የተባረከ ልዩ የአግዚአብሔር ፍጡር እንደሆነ ይገልጻል።
ሐ. በመጨረሻ የበላይ ሆኖ እስከሚቆጣጠራቸው ድረስ በጊዜ ብዛት ቀስ በቀስ ከዝቅተኞቹ እንስሳት ዝግመታዊ ለውጥ ያደረገ መሆኑን ይገልጻል።

2. "ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ተፈጠረ" በምንልበት ጊዜ ምን ማለታችን ነው?

ሀ. ስማንኛውም ረገድ ልክ እንደ አግዚአብሔር ነበር።
ለ. የኋላ ኋላ ያልተወሰነ ኃይልና ሥልጣን ኖሮት ልክ እንደ አግዚአብሔር የሚሆን ቢሆንም አሁን ግን ውሱን የአግዚአብሔር ግልባጭ ነው።
ሐ. ስእካላዊነቱ፣ በምግባራዊ ማሕበራዊ ግንዛቤው እንዲሁም በመግዛት ችሎታው ከአግዚአብሔር ጋር ተመሳሳይ እንደሆነ ነው።

3. የሰው ልጆች የተፈጠሩት

ሀ. ቁሳዊና ረቂቅ ከሆኑ ክፍሎች ነው።
ለ. ከሚደክም ከሞት በኋላ ከሚበሰብስ ሥጋና በፍርድ ቀን ሕያው እስከትደረግ ድረስ ከምትሞት ነፍስ ነው።
ሐ. ከፉ ከሆነ ሥጋና መልካም ከሆነ ረቂቅ ከፍል ነው።

4. የሰው ሕይወት ረቂቅ ገጽታ በሥነ ሕይወት ሥርዓት ውስጥ በእንዳንድ ምሁራን ዘንድ እንደ ተደርጎ ይታያል።

ሀ. እካል (ሥጋ)
ለ. ነፍስ
ሐ. መንፈስ
መ. የሕይወት እስትንፋስ

5. ነፍስ፣ መንፈስ፣ የሕይወት እስትንፋስና ሕሊና የተባሉት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የሰውን ለመግለጽ የዋሉ ቃላት ናቸው።

ሀ. ቁሳዊ ሕሳዌ
ለ. ረቂቅ ሕሳዌ
ሐ. እካላዊነት
መ. እካል (ሥጋ)

6. የሰውን ምክኑያዊ ሕላዌ ስሚመለከት ከሚከተሉ መግለጫዎች አውነት የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. የማወቅ ችሎታ ሰውን አንዲገነዘብና አንዲያመዛዝን ያስችለዋል።
ለ. ስሜቶች አንድን ሰው ስሜትን እንዲያገናዝብና በሚያውቀው ነገር እንዲለወጥ ያስችሉታል።
ሐ. ሕሊና የትክክለኛነትንና ያየስህተተኛነትን መስፈርት መሠረት በማድረግ ተግባራዊ እርምጃንና እመለካከትን ይመዝናል።
መ. ፈቃድ እንድ ሰው እንዲመርጥና እርምጃ እንዲወስድ የሚያስችለው ክፍል ነው።

7. አንድን ነገር በትክክል ስንረዳው በመጀመሪያ

ሀ. ፈቃድ ለጉዳዩ ወዲያው ውሳኔውን ይሰጣል።
ለ. ሀሊና ከእንድ ልክታ ወይም መስፈርት ጋር አነፃጽሮ መልካሞቹንና ክፉዎቹን ነጥቦች ይለያቸዋል።
ሐ. ስሜቶች አንድን ሰው ይሀን ወይም ያንን አርምጃ እንዲወስድ ያሳስቡታል።
መ. ኅሊና በደለኝነትና ጸጸት እንዲፈጠር ያደርጋል።

8. ውሳኔ በማድረግ ሂደት እንድ ሰው በቅድሚያ

ሀ. ስለ ጉዳዩ ያለውን ሐቅ መረዳት ይገባዋል።
ለ. የሕብረተሰቡን መመሪያ መስረት በማድረግ ምን እንደሚያደርግ መወሰን እለበት።
ሐ. ስሜቶቹንና የውሳኔውን ውጤት ማገናዘብ እለበት።

9. ሕሊና የሚያደርገው ክፍል ነው።

ሀ. በሰውየው ፍላጎት ላይ ተመሥርቶ ውሳኔ እንዲወስን
ለ. በሰውየው የኑሮ መመሪያ እንዳር የሚወስደውን ተግባራዊ አርምጃ እንዲመገን
ሐ. እንድን ተግባር ለመፈጸም ውሳኔን እንዲወስን
መ. መወሰድ ስላለበት ተግባራዊ እርምጃ ምርጫ

10. የሰው ፈቃድ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚሠራበት ምክንያት

ሀ. መልካም ነገር የማድረግ ፍላጎት ስላለው ነው።
ለ. የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚገልጽበት ሰብእዊ ሕሊና ስላለው ነው።
ሐ. ደኅንነትን ሊያለገኝና እግዚአብሔርን ለመታዘዝ የሚያስችል የእግዚአብሔር ፀጋ ስላለው ነው።
መ. በእግዚአብሔር ፍርድ ሥር እንዳይወድቅ ወይም እንዳይፈረድበት ስለሚፈራ ነው።

11. የሰውን እስመሞት በተመለከተ እውነቱ የትኛው ነው?

ሀ. አሁን ባሉበት ሁኔታ የሰው ስጋና ነፍሱ ሚቾች እይደሉም።
ለ. የሰው ቁሳዊ አካል ይበስብሳል ደግሞም ይሞታል ሆኖም ነፍሱ ፍጹም ሠላም በተሞላው ሁኔታ ስዘላለም ትኖራለች።
ሐ. የሰው አካል ይሞታል፣ የእማኙ ነፍስ/መንፈስ ወዲያውኑ በጌታ ፊት ትቀርብና በክርስቶስ ዳግም ምፅአት ከሙታን ተነስቶ የከበረ ሥጋ ይለብሳል፣ አማኝ ያልሆነው በገሐነም ወይም በሲኦል ለዘለዓለም ይሰቃያል።

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስ

1. ሀ. እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ።
   ለ. ...በእግዚአብሔር ምሳሌ አደረገው ወንድና ሴት እድርጎ ፈጠራቸው።
   ሐ. እግዚአብሔርም፦ "የፈጠርሁትን ሰው. . . " አለ።
   መ. ሰውን በእግዚአብሔር መልክ ፈጥሮታል።
   ሠ. እግዚአብሔርም ሰውን በምድር ላይ ፈጠረው።
   ረ. እግዚአብሔር እርሱ ሠራን።
   ሰ. ሰዎች እንደ እግዚአብሔር ምሳሌ ተፈጥረዋል።

7. 1. የማወቅ ችሎታ ገጽታ
   2. ፈቃድ
   3. የስሜታዊነት ገጽታ
   4. ሕሊና

2. ለ፣ ሐ፣ መ እንዲሁም ሠ መረጃ ያቀርባሉ።

8. ኀፍረት፣ ጸጸትና ፍርሃት

3. ሀ. የማሕበራዊ ኑሮ ባሕርይ
   ለ. ምግባራዊ መመሳሰል
   ሐ. የምክንያታዊነት ባሕርይ
   መ. ራስን ማወቅ
   ሠ. እካላዊነት
   ረ. የመግዛት ችሎታ
   ሰ. ምግባራዊ መመሳሰል

9. ሀ. እውነት
   ለ. ሐሰት
   ሐ. እውነት
   መ. ሐሰት
   ሠ. ሐሰት (መንፈስ ቅዱስ በሚሰጠው ፍቺ መሠረት በእግዚአብሔር ቃል የሚቀረጽ ነው)
   ረ. እውነት
   ሰ. ሐሰት

4. ሀ. 1 እና 4
   ለ. 5
   ሐ. 9
   መ. 3
   ሠ. 8 እና 6
   ረ. 2
   ሰ. 7

10. ሀ. 3 ሐ. 1
ለ. 2 መ. 4

5. ሀ. የሕይወት እስትንፋስ (አንድ ገጽታ)
ለ. ነፍስ (አንድ ገጽታ)
ሐ. መንፈስ (አንድ ገጽታ)
መ. ነፍስና መንፈስ (ሁለት ገጽታዎች)
ሠ ነፍስና መንፈስ (ሁለት ገጽታዎች)

11. መልሰህ ከሚከተለው ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት።
ሀ. ጉዳዩ ምን እንደሆነ ወይም ምን መወሰን እንደሚገባው ይረዳል።
ለ. መወሰድ የሚገባው ተግባራዊ እርምጃ ይኼኛው ወይም ያኛው መሆኑን ያመለክታል።
ሐ. ከሰውየው የሥነ-ምግባር መመሪያ አንፃር ሊወሰድ የታቀደውን ተግባራዊ እርምጃ ይመዝናል።
መ. ለጉዳዩ ውሳኔ ይሰጣል

6. ሠ

12. መልሰህ ከሚከተለው ጋር ተመሳሳይ መሆን አለበት።
ሀ ይበሰብስና ወደ አፈርነት ይመለሳል።
ለ. ክርሰቲያን በጌታ ፊት ለመሆን ወዲውኑ ወደ ገነት ይሄዳል። አማኝ ያልሆነው ግን በገሃነም ወይም በሲኦል ይሰቃያል።
ሐ. ሟች የሆነው ሥጋቸው ትንሳኤን ያገኘና የማይሞት የከበረ ሥጋን ለመልበስ ይለወጣል።
መ. ከጌታ ፊት ርቀው የዘላለም ፍርድና ቅጣት ይደርሰባቸዋል።
ሠ. ሰው ቁሳዊና ረቂቅ ሕላዌ እንዲኖረውና ነፍሱና መንፈሱም የማይሞቱ ሆነው እንዲኖሩ ተደርጎ በእግዚአብሔር ተፈጥሮአል። በጌታ እግዚአብሔር ፊት አለዚያም የዘላለም ቅጣት ባለበት በሲዖል ለዘላለም ይኖራል።

7 ኃጢአትና ደኅንነት
የኃጢአት መዘዙና መፍትሔው

ትምህርት

በዚህ ክፍለ ትምህርት ስለ ኃጢአት አጀማመርና ስለ አስከተለውም ውጤት መጽሐፍ ቅዱስ የሚለንን እንማራለን። በጥናታችን እግዚአብሔር በክርስቶስ ለላሰገኘልን መፍትሔም እንማራለን። እነዚህን አሰፈላጊ ርዕሶች በምናጠናበት ጊዜ መንፈስ ቅዱስ እንዲረዳን እስኪ እንጠይቀው።

የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- የኃጢአት እውንነት
- የኃጢአት አጀማመር
- የኃጢአት ምንነት
- የኃጢአት ውጤት
- የኃጢአተኛ መታደስ

የክፍለ ትምህርቱ ዓላማዎች

ይህንን ትምህርት በምታጠናቅቅበት ጊዜ የሚከተሉትን ማድረግ መቻል ይኖርብሃል፡-

- የኃጢአት እውንነትን መረጃ የሚያቀርቡ ምሳሌዎችን መስጠት።
- የኃጢአትን አጀማመር በሚመለከት ከእግዚአብሔር ቃል ልንማር የምንችለውን መግለጽ።
- የኃጢአትን ምንነትና ውጤቱን መግለጽ።
- ወደ ኃጢአተኛው መለወጥና መታደስ የሚያደርሱ ደረጃዎችን መዘር ዘር።

የክፍለ ትምህርቱ መመሪያዎች

1. ለትምህርቱ መነሻ እንዲሆንህ ኃጢአት ካስከተለው ችግር ጋር ግንኙነት ያለውን ዘፍ 2 እና 3 እንዲሁም ሮሜ 5 እና 6 አንብብ። እግዚአብሔር ለኃጢአት መፍትሔ ስማበገኘት ያደረገውን ማስተዋል እንድትችል ኢሳ 53 አንብብ። ከዚያ በኋላ እንደ ተለመደው የትምህርቱን ዋና ክፍል በማጥናት የማጠናከሪያ ጥያቄዎቹን ሥራ።
2. በትምህርቱ መጨረሻ የሙራውን ፈተና ከሰራህ በኋላ ከክፍለ ትምህርት 5-7 ያሉትን ከልሳቸው።



የትምህርቱ ዋና ክፍል

የኃጢአት እውንነት

ዓላማ 1 ስለ ኃጢአት እውንነት አንድ ትርጉምና ሁለት ማረጋገጫዎችን ማቅረብ

ኃጢአት እግዚአብሔር ለሚያመዛዝኑ ፍጥረቱ መመሪያ እንዲሆን የሰጠውን ሕጉን ለመጠበቅ አለመቻል ወይም አመጽ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። የእግዚአብሔር ሕግ የእርሱ ምግባራዊ ማንነት መግለጫ ስለሆነ የእግዚአብሔርን ቅዱስ ባሕርይ ደስ ለማሰኘት የሰው ልጅ ከዚያ ሕግ ጋር መስማማት አለበት። መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ስለ ኃጢአት እውንነት እንደዚሁም ስለ አጀማመሩ፣ ባህርይው፣ ውጤቶቹና መፍትሔው ያስረዳናል። በትምህርቱ ወደፊት ስንገፋ እነዚህ ሁሉ የኃጢአት ገጽታዎች ይብራራሉ።

ቅደም ባለው ትምህርታችን እንደተመለከትነው ሰው የሚያመዛዝን ፍጡር ነው። ስለሆነም 1)ማድረግ የማይገባውን ካደረገ 2)ማድረግ የሚገባውን ካላደረገ 3)መሆን የማይገባውን ከሆነ 4)መሆን የሚገባውን ካልሆነ የኃጢአት ክስ እንዳለበት ያውቃል። ለኃጢአት እውንነት ብዙ ማስረጃዎች አሉ። ከእነዚህም የመጀመሪያው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛል።

ከመጽሐፍ ቅዱሳዊ መረጃ አንፃር ሲታይ

ኃጢአት ከመጽሐፍ ቅዱስ ዋና ዋና ጉዳዮች እንዱ ነው። በዘፍ 3 ለመጀመሪያ ጊዜ ሰው ኃጢት እንዳደረገ ተዘግቧል። ምዕራፍ አራትም ይህንኑ ሃሳብ በመቀጠል ችግሩ የመጀመሪያዎቹን እናትና አባታችንን ልጆች እንዴት እንደነዳቸው ይናገራል። በዚህን ወቅት እግዚአብሔር ለቃየን ጥብቅ ማሳሰቢያ ሰጠው፦ "ኃጢአት በደጅ ታደባለች፣ ፈቃዷም ወደ አንተ ነው፣ አንተ ግን በእርሷ ንገሥባት" (ዘፍ 4፡7)። ይሁን እንጂ ቃየን በውስጡ ይሰማው ለነበረው ቅንዓት፣ ለጥላቻና ለዓመጽ ለሜቱ ተሸንፎ የራሱን ወንድም ገደለው።

(1). በሁለት ቃላት የአዳምና የሔዋን እንዲሁም የቃየን ኃጢአት ባሕርይ ምን ነበር? (ዘፍ 3፡11፣ 4፡7)።

መጽሐፍ ቅዱሳችንን በምናገላብጥበት ጊዜ ኃጢአት ያስከተለውን ችግር ደጋግመን እንመለከታለን። በልምምዳቸው ጅማሬ ላይ ይመሩበት ዘንድ እግዚአብሔር ለእሥራኤል ሕዝብ ሕግን ሰጣቸው (ዘጸ 20፡1-7)። ደግሞም ለፈጸሙአቸው ኃጢአቶች ተገቢ የሆኑትን መሥዋዕቶች እንዲያቀርቡ መመሪያ በመስጠት ኃጢአት እንዴት እንደሚስተሰረይ በግልጽ አስታወቃቸው (ዘሌ 4-7)። መላው የእሥራኤል ሕዝብ ኃጢአቱን የሚናዘዝበትን ከዓመት አንድ ቀን ሰይሟል (ዘሌ 16)። ለቅድስና ሕይወትና ለኃጢአት ይቅርታ የሚገኝበትን መመሪያ በተመለከተ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያዘጋጃቸውን ሕግጋት በሙሉ የያዙ በመሆናቸው የብሉይ ኪዳን የመጀመሪያዎቹ አምስት መጻሕፍት የሕግ መጻሕፍት ይባላሉ።

ከኢያሱ እስከ አስቴር ያሉት የታሪክ መጻሕፍት ሕጉን ለመታዘዝ ያቃታቸውን የእግዚአብሔር ሕዝብ አሳዛኝ ታሪክ ያቀርባሉ። ወደ ኃጢአታቸው የተመለሱበትን፣ ያልታዘዙበትን፣ አንገተ ደንዳና የሆኑበትንና በእግዚአብሔርና በሕጉ ላይ ያመጹበትን ሁኔታ ይገልጻሉ።

(2). መጽሐፈ መሳፍንት 2፡6-7 ከ2፡10-19 ጋር እንጻጽር። ከኢያሱ ሞት በኋላ ሕዝቡ እንዴት ተለወጡ?

(3). መሳፍንት 3፡7፣9፣12፣15፤ 4፡1፤6፡1 አንብብ። በእነዚህ ጥቅሶች ተደጋግሞ የተገለጸው ሃሳብ የትኛው ነው?

መዝሙረኛው በግል ኃጢአቱ የተሰማውን ኃዘን ይገልጻል፦ "አቤቱ፣ እንደ ቸርነትህ መጠን ማረኝ፣ እንደ ምሕረትህም ብዛት መተላለፌን ደምስስ። ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ፣ ከኃጢአቴም አንጻኝ። እኔ መተላለፌን አውቃለሁና፤ . . . እነሆ በዓመፃ ተፀነስሁ፤ . . ." (መዝ 51፡1-3፡5)። በእሥራኤል ላይ ውድቀት ስላስከተለው ኃጢአት ነቢያቱ አልቅሰዋል (ሕዝ 23፣ ኤር 5፣ ዳን 9፡1-23)።

አዲስ ኪዳን የይሁዳ አስቆሮቱን ተንኮል ዘግቦታል (ማቴ 26፡14-16)። የዓለምን ኃጢአት በራሱ ላይ የተሸከመውን የእዳኛችንን ሥቃይ ያሳያል (ሉቃ 22፡39-44፤ ዮሐ 19-1-3፣ 18)። ሐናንያና ሰጲራ የፈጸሙትን አሳፋሪ ሴራ ይገልጻል (የሐዋ 5፡1-11)። ሰለ ኃጢአት አውንነት በጣም ጉልህ ከሆኑት መረጃዎች አንዱ በሮሜ 1፡28-32 ተዘግቧል። በዚህ ክፍል ኃጢአት የተገለጸው በሚከተለው ሁኔታ ነው፡-

"እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው፤ ዓመፃ ሁሉ፣ ግፍ፣ መመኘት፣ ክፋት ሞላባቸው፤ ቅናትን፣ ነፍስ መግደልን፣ ክርክርን፣ ተንኮልን፣ ክፉ ጠባይን ተሞሉ፤ የሚያሾኩሹኩ፣ ሐሜተኞችም፣ አምላክን የሚጠሉ፣ የሚያንገላቱ፣ ትዕቢተኞች፣ ትምክህተኞች፣ ክፉትን የሚፈልጉ፣ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፣ የማያስተውሉ፣ ውል የሚያፈርሱ፣ ፍቅር የሌላቸው ምሕረት ያጡ ናቸው። እንደነዚህ ለሚያደርጉት ሞት ይገባቸዋል የሚለውን የእግዚአብሔርን ሕግ እያወቁ እነዚህን ከሚያደርጉ ጋር ይስማማሉ እንጂ አድራጊዎች ብቻ አይደሉም" (ሮሜ 1፡18-32)።

(4). በተነጋገርነውና በ1ዮሐ 5፡17 በተገለጸው መሠረት የኃጢአትን ትርጉም ስጥ።

ከመንግሥት አስፈላጊነት አንፃር ሲታይ

መጽሐፍ ቅዱስ የኃጢአትን አውንነት የሚገልጸ ብዙ ምሳሌዎችን ማቅረብ ብቻ ሳይሆን፤ ችላ ሊባል በማይገባው በሕብረተሰብ ውስጥ በሚቋቋመው መንግሥት በኩል መረጃንም ያቀርብልናል። በመሳ 21፡25 ላይ "በዚያም ዘመን በእሥራኤል ዘንድ ንጉሥ አልነበረም፤ ሰው ሁሉ በፊቱ መልካም መስሎ የታየውን ያደርግ ነበር" የሚል ቃል እናነባለን። አስከዚያ ጊዜ ድረስ በርሱ መመሪያ መሠረት አሰራኤላውያንን እንዲመሩ እግዚአብሔር መሳፍንትን ተጠቅሞባቸዋል ሆኖም በ1ሳሙ 8 እሥራኤላውያን የሚመራቸው ንጉሥ እንዲሾምላቸው ሳሙኤልን እንደጠየቁት ተጽፎ እናገኛለን። በአካባቢያቸው ከነበሩት አገሮች ጋር ተመሳሳይ የሆነ መንግሥት (ቁ 5) እንዲኖራቸው ፈልገው ነበር። ሕዝቡ ለእግዚአብሔር ለመታዘዝ ፈቃደኞች ሰላልነበሩ መንግሥት ማቋቋሙ አስፋላጊ ነበር።

አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ፍጹም ፍትሕና ማኅበራዊ እንድነት ስለ ስፈነበት ተምኔታዊ (የሃሳብ) ሥፍራ ወይም ሁኔታ ወይም "ምድራዊ ገነት" ሕልም ያልማሉ። በ"ምድራዊ ገነት" ማንኛውም የራሱን ተግባር በሚገባ ይወጣል፤ ለሌላው ሰው በጎነት ለሚሆነው ነገር በደስታ አሰተዋጽአ ያደርጋል። ይግሞም በሕይወትም መልካም በሆኑት ነገሮች ሙሉ በሙሉ ይደሰትባቸዋል። ይሁን እንጂ የምድራዊ ገነት ሕብረተሰብ በምድር ላይ ሊኖር አይችልም። የሰው ልጆች በተፈጥሮአቸው ራስ ወዳዶችና ዓመጸኞች ናቸው። ኃጢአት በየዕለቱ የሚያጋጥመን የሕይወት አውነት ነው። ማንም ሰው ቢሆን ኃጢአት ከሚያስከትላቸው ውጤቶች ሊያመልጥ አይችልም።

በሕብረተሰብ ዘንድ የመንግሥት ቁጥጥር አሰፈላጊ መሆኑን በግልጽ በማመልከት የኃጢአት አሳዛኝ ውጤቶች በጋዜጦች ተዘግበዋል። እንደዚሁም በሬድዮና በሌሎች የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎችም ቀርበዋል።

ኃጢአት እውን ነው። የመላ ምት እምልኮ ወይም የትምህርት ጉድለት ውጤት አይደለም። ከእግዚአብሔር ሕግ ተቃራኒ በሆነ መንገድና እንደ ራሳቸው ክፉ ፍላጎት መሠረት የሚኖሩ ሰዎች ባህርይ ውጤት ነው።

(5). በማስታወሻ ደብተርህ ስኃጢአት አውንነት ሁለት ማረጋገጫዎችንና ለአያንዳንዱ አንዳንድ ምሳሌ ስጥ።

የኃጢአት አጀማመር

ስብዙ ዘመናት እንዳንድ ምሁራን ኃጢአት ከመልካም ነገር ጋር ስዘላለም የነበረ ስለመሆኑና ስላለመሆኑ ሲከራከሩ ቆይተዋል። እንዳንዶች በእውንትና በሐስት መካከል ያለው ትግል ለዘላለም ነበረ አሁንም ይቀጥላል ብለው ደምድመዋል። ለመሆኑ መልካምነት ለብቻው የነበረበት ዘመን ነበረ? ከነበረ ኃጢአት መቼ መታየት ጀመረ? ስዚህ ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት በዓ ለምና በስው ዘር ውስጥ የኃጢአት ጅማሬ ምን እንደሚመስል እንመልከት

ኃጢአት በዓለም ውስጥ

ዓላማ 2 የኃጢአትን አጀማመር በትክክል የሚገልጹትን መግለጫዎች መምረጥ

በክፍለ ትምህርት 5 ለውድቀት ሰላደረሳቸው የመላእክት ኃጢአትና በዓለም ላይ ኃጢአት እንዴት እንደተጀመረ የእግዚአብሔር ቃል የሚለውን ተመልክተን ነበር። እስኪ አሁን ደግሞ ኃጢአት በስው ዘሮች መካከል ከመሰፋፋቱ ጋር ያለውን ዝምድና በሚመለከት እነዚህኑ እውነቶች ከልስን እንመልከታቸው። በቅድሚያ በክፍለ ትምህርት 5 "የመላእክት ምግባራዊ ባሕሪ" በሚል ርዕስ የቀረበውን በድጋሚ እንብበው። በዚያ ክፍል የተነገረው ባጭሩ የሚከተለው ነው፡-

1. መላእክት ሲፈጠሩ ቅዱስና ፍጹም እንዲሁም ፈቃዳቸውን ወደ ፈጣሪያቸው ያዘነበሉ ባህሪ ያላቸው ጭፍራዎች ሆነው ነበር።
2. መላእክት የመምረጥ ኃይል እንደነበራቸውና የዓመፃቸውንም ውጤት ይረዱ እንደነበረ ግልጽ ነው።
3. ከእነርሱ መካከል አንዱ የነበረው ሰይጣን በክብር ሰፍራ ላይ የተቀመጠ ነበር (ሕዝ 28፡12፤ 2ቆሮ 4፡4፤ ኤፌ 2፡2)።

4. ሰይጣን ከመጀመሪያውም የአመጽ መሪ እንደነበረ ግልጽ ነው (ዮሐ 8፡44፤ 1ዮሐ 3፡8)።

5. የሰይጣን ምሳሌ ሆነው የቀረቡ ከሚመስሉት ምድራዊ ነገሥታት መግለጫ ሰይጣን ኃጢአቱን የጀመረው በምኞትና በአብሪት (ከመጠን ያለፈ ትዕቢት) እንደነበረ አንረዳለን (ሕዝ 28፡11-19) አንዲሁም ኢሳ 14፡13-14 ከ1ጢሞ 3፡6 ጋር በማነፃፀር ተመልከት)።

ቀደም ብለን የተመለከትናቸው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ሰይጣን በእግዚአብሔር ሥልጣን ሥር በተሰጠው ስፍራው ደስተኛ እንዳልነበረ ያስገነዝቡናል። እግዚአብሔርን ከማገልገል ይልቅ ሰገዛ ራሱ ምኞት የበለጠ ትኩረት ሰጥቶ ነበር። በገዛ ራሱ ውበት ዓይኑ ስለታወረ ከፈጣሪው እንኳ እንደሚበልጥ የሚያስብ ይመስላል። ሰይጣን ራስ ወዳድ፣ አርካታ የሌለው፣ ፈጣሪው ለእርሱ የሰጠውን ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር ለራሱ ብቻ የከለለውንም ሟምር የፈለገ ስግብግብ ነበር። በሰይጣን የምንመለከተው የኃጢአት በሽታ ምልክቶች በቀሩት የርኩሳን መላእክትም ዘንድ የኃጢአት ሥሮች እንደነበሩ ግልጽ ነው።

ይሄ ሁሉ ነገር ለእኛ ትልቅ እስፈላጊነት አለው፣ ምክንያቱም ሰይጣንና መላእክቱ በእግዚአብሔር ላይ ባመጹ ጊዜ ኃጢአት በዓለም ውስጥ ልንጋፈጠው የሚገባን የሕይወት ሥርዓት ሆነ። አነርሱ የፈጸሙት ኃጢአት በእፍቃሪ ሰማያዊ እባታችን አገዛዝ ላይ የተነሳውን ተቃውሞ ይወክላል። እሁን የሰይጣን ዓላማ በዓለም ውስጥ በማንኛውም ስፍራ የእግዚአብሔርን አቅድ ማሰናከል ነው። እግዚአብሔርንና አገዛዙን በመቃወም የተሰለፈውን የዓለም ሥርዓት ይመራል።

(6). በዓለም ውስጥ የኃጢአትን እጀማመር በሚመለከት ከቀረቡት አውነተኛ መግለጫዎች አንዱ ያሉትን ፊደሎች ክበቦቹ።

ሀ. እግዚአብሔር ኃጢአትን ወደ ዓለም ያስገባው ፍጡራኑ ለእርሱ ያላቸውን ታማኝነት የመፈተኛ መንገድ አድርጎ ነው።
ለ. ኃጢአት የመልካምነትን ሥርዓት ሚዘናዊ ለማድረግ የታቀደ ዘላለማዊ ሥርዓት ነው።
ሐ. ኃጢአት የተጀመረው ኃላፊነት የሚሰማቸው ፍጡራን በፈጣሪያቸው ላይ ለማመጽ በመምረጥ በራሳቸው መንገድ በሄዱ ጊዜ ነው።
መ. ኃጢአት በዓለም ውስጥ የተጀመረው በራሱ ምኞትና ትዕቢት ምክንያት ሰይጣን ከፍ ያለ ደረጃ በፈለገበት ጊዜ ነው።
ሠ. እግዚአብሔር ማንንም እንዲያመልኩት ስለማያስገድድ የመምረጥ መብት ለመላእክትና ለሰዎች አስፈላጊ ነበር።

በሰው ልጆች መካከል እንዴት እንደተጀመረ

እንደተመለከትነው እግዚአብሔር ሰውን የኃጢአት ባህርይ የሌለው እድርጎ ፈጠረው፣ ተስማሚ በሆነ አካባቢ አኖረው ደግሞም የሚያስፈልገውንም አቀረበለት። እግዚአብሔር ለእዳም ብርቱ እእምሮና ጊዜውንና ኃይሉን ተግባራዊ ማድረግ የሚያስችለውን በርካታ የሥራ መስኮች ከፈተለት።

ከዚህም በተጨማሪ እግዚአብሔር ለእዳም ተስማሚ ረዳትና ባልንጀራ እንድትሆነው ሔዋንን ሰጠው። ከዚያም በኋላ ፈጣሪ ለእዳምና ለሔዋን ሊጠብቋቸው የሚገቧቸውን እንዳንድ ግልጽ ሕጎችን ሰጥቶ ዓመጽ ሊያስከትልባቸው ስለሚችለው ውጤት አስጠነቀቃቸው። ይህንን ካደረገ በኋላ ከእነዚህ የመጀመሪያ ባልና ሚስት ጋር በጣም ቅርብ የሆነ ሕብረት መሠረተ።

እግዚአብሔር ለእዳምና ለሔዋን የሰጣቸው ማስጠንቀቂያ እንደ እንድ አነስተኛ ሙከራ እገልግሏል። በእነዚያ ሁሉ ብዙ መብቶችና በረከቶች መካከል እንድ ነገር ብቻ ተከልክሰው ነበር። የእንድ ዛፍ ፍሬ። ይህ ፈተና ለእግዚአብሔር ፈቃድ ለመታዘዝ ወይም ላለመታዘዝ የነበራቸውን ዝንባሌ ለመመዘን የታቀደ ነበር። እዳምና ሔዋን በዚህ ጉዳይ ላይ ምንም የራሳቸው ምርጫ ሳይኖራቸው እንደ መንኮራኩሮ (ሮቦት) ሆነው ለእግዚአብሔር ክብር እንዲኖሩ አልተፈጠሩም። ፈቃዳቸው ወደ እግዚአብሔር ያዘነበለ ነበር፣ ሆኖም ይህንኑ ዝንባሌ ለመቀበልም ሆነ ለመቃወም ኃይሉ ስለነበራቸው ነፃ ፈቃዳቸውን በመጠቀም የራሳቸውን ምርጫ ማድረግ ይችሉ ነበር። ለቀረበላቸው ፈተና ይህ ችሎታቸው አስፈላጊ ሁኔታ ነበር።

በእግዚአብሔር ላይ ባመጹ ጊዜ ሰይጣን ፈታኝ እልነበረበትም፣ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ግን ፈታኝ ነበረባቸው። እዳምና ሔዋን በኤደን ግነት እንዲቀመጡ እንደተደረጉ ወዲያውኑ ሰይጣን ወደ ሔዋን ተጠግቶ እግዚአብሔር ከእርሷና ከአዳም መልካምና ጠቃሚ የሆነ ነገር እንደከለ ከላቸው የሚያመለክት ሃሳብ ዘራባቸው። በእግዚአብሔር ላይ ለቀረበው ለዚህ ከባድ ክስ ሔዋን ተቃውሞ ያለማቅረቧ አስደናቂ ነው። አንዲያው እግዚአብሔር እንደዋሻቸው በማመልከት ሰይጣን "ሞትን አትሞቱም" (ዘፍ 3፡4) ባላት ጊዜ ሔዋን አልተቃወመችም ወይም በእግዚአብሔር ቅዱስ በሕርይ ላይ የተሰነዘረውን የውሸት ወቀሳ ለመቋቋም አልፈለገችም። ከዚያ ይልቅ የፈታኙን ምክር በመከተል ልታገኝ ስለምትችለው ትርፍ ብቻ ታስብ ነበር፣ ያ ምክር ስሜቱዋን፣ ሥጋዊ ፍላጎቱዋንና የተቀሰቀሰበትን ትኩስ ምኞት የሚማርክ ሆነባት።

ስለሆነም ሔዋን ፈቃዷን ተግባራዊ በማድረጓና በሰይጣንም ማታለል ምክንያት እግዚአብሔር የፈለገውን ሳይሆን ራሷ የፈለገችውን ለማድረግ ወሰነች። በዘፍ 3፡1-5 መሠረት እሷ የፈለገችው፦ ❶ እግዚአብሔር የክለከለውን ማግኘት ❷ እግዚአብሔር ያልገለጸውን ማወቅ እንዲሁም ❸ እግዚአብሔር እንድትሆን ያላቀደላትን መሆን ነበር።

ሔዋን ከእግዚአብሔር ይልቅ ራሷን እስቀደመች ይህም ኃጢአት ነበር። ምን ማድረግ እንደሚገባት እስላሰለች። ወደ ፍሬው ተመለከተችና መልካም ምግብ ከመሆኑም በተጨማሪ ፍሬው ውብ ስለነበረና ጥበብንም እንደሚያስገኝ ስለተነገረ እሱን መብላት ስህተት ሊሆን እይችልም በማለት

አመካኘች። ይህንንም በማድረጓ እጅግ በጣም አሰፈላጊ የሆነውን አንድ አውነት ዘነጋች። *እግዚአብሔር ፍሬው እንዳይበላ መከልከሉን!* ልታይ የምትፈልገውን ብቻ በመመልከቷ አሷና አዳም በእግዚአብሔር ቃል ላይ ግልጽ የሆነ ዓመጽ በመፈጸም ፍሬውን በሉ። የሚያስከትልባቸው ምን አንደሚሆን መረዳት የሚያስችላቸው በቂ የማወቅ ችሎታ ቢኖራቸውም አንኳ በድርጊታቸው እግዚአብሔር ይከብር ወይም አይከብር አንደሆነ አልጠየቁም። ምን አያደረጉ አንደነበረ ለምን በበለጠ ጥንቃቄ አላሰቡም?

በዚህ ዓይነት የመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችን ሆን ብለው የአግዚአብሔርን ማሰጠንቀቂያ ችላ ማለት መረጡ። ቢፈተኑም እንኳ ከአግዚአብሔር መመሪያ ውጪ አንዲሄዱ ማንም አላስገደዳቸውም። ይህ የዓመጽ እርምጃ በሰው ልጆች ዘንድ ኃጢአትን አስከተለ (ሮሜ 5:12 *ተመልከት*) ወደዚያም ውድቀት *ያመራው* ዝንባሌ አስከዛሬ በለምች ባህርይ ቀጥሏል። ይህ ዝንባሌ እኔን ተለምቶኛል፣ እናንተንም ይለማችኋል። በዚህም ዓይነት ኃጢአት ወደ ዓለም ገባ። ሰውም ከአግዚአብሔር ጋር የነበረውን የተባረከ ሕብረት በማጥፋት ክፉ ተጽእኖውን በሰው ልጆች ላይ አሳደረ። ኃጢአት በአያንዳንዱ የአዳም ዘር ላይ ተጽእኖ ማሳደሩን ይቀጥላል። አያንዳንዱ ሰው ካልታረመ በሰተቀር ወደ መንፈሳዊ ሞት ሊያመራ የሚችል ኃጢአታዊ ባህርይ ከአዳም ወርሷል።

(7). ዘፍ 3:22-23 እና ሮሜ 5:12 አንብብና ለሚከተሉት ጥያቄዎች መልስ ስጥ።

ሀ. ከራሱ ሕይወት ጋር በተዛመደ ሁኔታ የአዳም ኃጢአት ውጤት ምን ነበር?

ለ. የእርሱ ኃጢአት በአዳም ዘር ላይ ያስከተለው ውጤት ነበር?

(8). በማለታወሻ ደብተርህ አግዚአብሔር በአዳምና በሔዋን በአንርሱም ምክንያት በመላው የሰው ዘር ላይ ያስተላለፈው ፍርድ ለምን ትክክል አንደሆነ ግለጽ?

የኃጢአት ምንነት

ዓላማ 3 የኃጢአትን ገጽታዎች ለይቶ ማወቅ

ኃጢአት ገለል ልናደርገው የምንችል ቁሳዊ ነገር ቢሆን የተሻለ አልነበረምን? አንደዚያ ቢሆን ኖሮ አሱን የሚያጠፉ የሚዋጥ ክኒን ወይም የሚወጋ መርፌ አንዲያገኙልን አንዳንድ ተመራማሪዎችን አንጋብዝ ነበር። የዚያን ጊዜ የባለሙያዎች ቡድን ከአንዱ ክልል ወደ ሌላው ክልል በመሄድ ኃይሉና ውጤቱ ለዘላለም የሚቆይ መርፌ እየወጉ ይዘዋወሩ ነበር። ብዙም ሳይቆይ ሕብረተሰቡ ሙሉ በሙሉ ይለወጣል ሰዎችም

ለእግዚአብሔር ከብር መኖር ይችላሉ። ኃጢአት ጀርም ወይም ቫይረስ አንዳልሆነ አናውቃለን። የኃጢአት እርግጠኛ ባህርይ ምንድን ነው?

በዚህ ክፍለ ትምህርት የመጀመሪያ ክፍል አጠር ያለ የኃጢአትን ትርጉም ተመልከተን ነበር። ኃጢአት ዓመጽና ከአግዚአብሔር ቃል ጋር መለማማት አለመቻል ነው። ለዎች የሚያደርጓቸው ትክክል ያልሆኑ ነገሮች ሁሉ ኃጢአት ናቸው። ይህም ማድረግ የማይገባንን ማድረግንና ማድረግ የሚገባንን አለማድረግንም ይጨምራል።

የብሉይ ኪዳኑ የዕብራይስጥ ቋንቋና እዲስ ኪዳን የተጻፈበት የግሪክ ቋንቋ በእግዚአብሔር ላይ የሚፈጸመውን የኃጢአት ድርጊት ለመግለጽ ገላጭ የሆኑ ቃላትን ይጠቀማሉ። ስለ ቃላት ምስረታ ያጠኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሑራን ለቃላቱ መፈጠር ምክንያት የሆኑትን ሃሳቦች ይገልጻሉ። እነርሱ ያደረጓቸው የቃላት ምስረታ ጥናት የኃጢአት ትርጉም ምን ማለት አንደሆነ ሃሳቡን አንድንጨብጥ ያስችለናል። በተለያየ ዓይነት መንገድ እያንዳንዱ አገላለጽ የአግዚአብሔርን ቁጣ የሚያነሳሳ ድርጊትን ወይም ዝንባሌን ይገልጻል። አስኪ ከእነዚህ አገላለጾች አንዳንዶቹን እንመልከት። (*ዘመናዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች የተጠቀሙባቸው አገላለጾች በዚህ መጽሐፍ ከተጠቀምንባቸው ጋር በትክክል ላይመሳሰሉ ይችላሉ። እዚህ የቀረቡት ከዕብራይስጥ ወይም ከግሪክ አገላለጽ የተወረሱ ናቸው*)።

❶. *መተላለፍ* (ሮሜ 5:14-17)፦ ብዙውን ጊዜ "ከዚህ ማለፍ ክልክል ነው" የሚሉ ምልክቶችን አንመለከታለን። ይህ ምን ማለት ነው? አልፎ መሄድ የሌላውን ሰው ንብረትም ሆነ መብት መድፈር ነው። ለዎች ያንን ምልክት ካደረጉ ማንም ሰው ወደ ንብረታቸው አልፎ አንዲገባ አይፈልጉም ማለት ነው። ይህን መተላለፍ ለመከላከል ለዎች ንብረታቸውን በሳጥን ውስጥ ያደርጋሉ፣ አለዚያም ዙሪያውን ግልጽ የሆነ የድንበር ምልክት ያደርጋሉ። ብዙውን ጊዜ "ማለፍ ክልክል ነው" ከሚለው ምልክታቸው ላይ መተላለፉ የሚያስከትለውንም ቅጣት ይገልጻሉ። አንደዚሁም ሁሉ እግዚአብሔርም ሕግጋት ብለን የምንጠራቸውን የተወሰኑ የሥነ-ምግባር ድንበሮች ለሰዎች ደንግጓል። አንድ ሰው ሲተላለፍ ወይም ከድንበር ምልክቶቹ አልፎ ሲሄድ ኃጢአትን ያደርጋል የእግዚአብሔርን ሕግ ንቋል፣ ሕግ አልባ መሆን ኃጢአት ነው (1ዮሐ 3:4)።

❷. *ዓላማ መሳት* (ዘጸ 20:20)፦ እንድ ሰው ኃጢአት ሲያደርግ እግዚአብሔር ለሕይወት ያሰቀመጠለትን ዓላማ ለመፈጸም አልቻለም ማለት ነው። ከዚህ እንሳር ሰናየው ኃጢአት ዓላማን መሳት ነው። እግዚአብሔር ለአርሱ ያቀደለትን ማሟላት አልቻለም። ዓላማን መሳት የሚለው አገላለጽ እንድ ሰው ሊላማ ያደረገውን አለተካክሉ መምታት እንዳልቻለ ለመግለጽ ቀስተኞች የሚጠቀሙበት አገላለጽ ነው።

❸. *ራስ ወዳድነት* (መዝ 119:36፤ ፊልጵ 2:3)፦ የመጀመሪያው ዓመጽ ሰው እግዚአብሔር እንደከለከለው የመሰለውን ነገር በመፈለጉ ከራስ ወዳድነት የተነሳ የተፈጸመ ነው።

❹. ዓመጽ (ዘፀ 23:21፤ 1ሳሙ 24:11)፦ *ማመጽ* ማለት አለመታዘዝ ወይም ከባለሥልጣን ፈቃድ ውጪ መሄድ ነው። ከእግዚአብሔር ሕግ ፈቀቅ ማለት ነው። ኢሳይያስ እንዲህ ሲል በምሳሌ ይገልጸዋል፦ "እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ ከእኛ እያንዳንድዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ" (ኢሳ 53:6)። ዛሬ ሰዎች የሚያደርጉት ይህንኑ ነገር ነው። እያንዳንዱ ሰው "ራሱ ደስ ያለውን ያደርጋል" የራሱን መሻት ይከተላል። ይህ አጠቃላይ ክልሎችንና መንግሥታትን በሚመለከት እውነት ነው። ሰዎች እግዚአብሔር ያቀደላቸውን መስመር ተከትለው መንገዝ አይፈልጉም።

❺. *መበከል* (ያዕ 1:27) እንድ ሰው ሆነ ብሎ ኃጢአት ሲያደርግ ጎሊናው ስለሚወቅሰው ተገቢ ነገር እንዳላደረገ ያውቀዋል። በኃጢአት ምክንያት የተቀሰቀሰው የወንጀለኛነት ስሜት *መበከሉን* እንዲያውቅ ያደርገዋል። *መርከሱ* ይሰማዋል። የእግዚአብሔር ቃል ከኃጢአት *መበከል* መንፃት ያስፈልጋል የሚለው በዚህ ምክንያት ነው (መዝ 51:2፣ 7፤ 1ዮሐ 1:7)።

ሃሳቡን ባጭሩ ስናጠቃልለው ኃጢአት ሊያመዛዝኑ የሚችሉ የእግዚአብሔር ፍጥረቶች ለእግዚአብሔር ሕግ ለመታዘዝ አለመቻል ነው። እግዚአብሔርን ማክበርን ግቡ ያላደረገ ማንኛውም ነገር ኃጢአት ነው (ሮሜ 3:23)። የእግዚአብሔርን ቅዱስ ባሕርይ የማይገልጽ ወይም ከቅዱስ ባሕርይ ጋር ተፃራሪ የሆነ ማንኛውም ነገር ኃጢአት ነው።

(9). የኃጢአትን አንድ ገጽታ የሚወክሉትን እገላለጾች ለእያንዳንዳቸው ተስማሚ ከሆነው ትርጉም ጋር አቀናጃቸው።

1. *መተላለፍ*	3. *ራስ ወዳድነት*	5. *መበከል*
2. ዒላማን *መሳት*	4. *ዓመፅ*	

ሀ. የእግዚአብሔርን *መንገድ* ከመቀበል ይልቅ የራስን *መንገድ መፈለግ*።
ለ. የኃጢአታችንን *መንጻት* እንድንፈልግ ያደርጋል።
ሐ. እግዚአብሔር ለሕይወታችን ያቀደልንን ማሟላት አለመቻል።
መ. እግዚአብሔር ያስቀመጠውን የተከለከለ ወሰን አልፎ *መሄድ*።
ሠ. ከእግዚአብሔር ሕግ *መራቅ*፤ ከእግዚአብሔር *ሥልጣን* ውጪ *መሄድ*።

የኃጢአት ውጤት

ዓላማ 4 የኃጢአትን ውጤት የሚገልጹ እውነተኛ መግለጫዎችን መለየት

ዘፍ ምዕራፍ 3 ሰለ አሳዛኙ የኃጢአት ውጤት ይተርክልናል። "መልካምንና ክፉውን ከሚያስታውቀው ዛፍ አትብላ፤ . . ." በማለት እግዚአብሔር በርግጥ እንደተናገረ ሁሉ "ከርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህና" (ዘፍ 2:17) በማለትም አስጠንቅቋል። ሰው *መሰኮታዊውን* ማሰጠንቀቂያ ችላ በማለቱና የተከለከለውን በመውሰዱ ከተነገረው ውጤት ሌላ ምንም የተለየ ነገር መጠበቅ አይችልም። እስኪ ባጭሩ በሰው የመጀመሪያ ኃጢአት ምክንያት የተከተሉትን ዋና ዋና ውጤቶች እንመልከት።

ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ሕብረት መቋረጥ

በእግዚአብሔር ላይ ሆነ ብለው ማመፃቸውን ማወቃቸውና መገንዘባቸው በአዳምና በሔዋን ላይ ወዲያውኑ የወንጀለኛነት ስሜት አስከተለባቸው። ቅንነታቸው ቀረ፣ ጎሊናቸውም ድርጊታቸውን ኮነነባቸው። እርስ በርሳቸውም ሆነ በእግዚአብሔር ፊት ራቁታቸውን መሆናቸው ታወቃቸው፣ በኃፍረትም ከእግዚአብሔር ለመሸሽ ሞከሩ። ስላደረጉት ነገር እግዚአብሔር በጠየቃቸው ጊዜ እያንዳንዱ ሌላውን ለመክሰስ ሞከረ። አዳም ሔዋንን ከሰሰ፣ ሔዋንም እባቡን ከሰሰች (ዘፍ 3:12-13)። ከዚህም አሳዛኝ *ማመካኘት* የተነሳ ከእግዚአብሔር ጋር በግል የነበራቸው *መልካም* ግንኙነት እበቃ። *መንፈሳዊ* ሞት ደረሰባቸው (ዘፍ 2:17) ከኤደን ገነትም ተባርረው እስከዚያ ጊዜ ድረስ አይተውት ወደማያውቁት በጣም የተለየ ሕይወት ውሰጥ ገቡ።

የኃጢአተኛነት ባሕርይ

የአዳምና የሔዋን ኃጢአት ያበላሸው የእነርሱን ልብ ብቻ ሳይሆን የእነርሱን ዘር ልብ ሁሉ ነው። የእነርሱ እንድ ኃጢአት ከዘሮቻቸው ወደ እያንዳንዱ ሰው ከዚያም ወደ *መላው* የሰው ልጅ የተላለፈ ጠንቀኛ ሥርዓት *መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ* ይናገራል (ሮሜ 5:12)። በዚህም ዓይነት *መላው* ዓለም በኃጢአት ኃይል ሥር ዋለ (ገላ 3:22)፤ በዚህም ባርነት ምክንያት "የቁጣ ልጆች" ሆንን (ኤፌ 2፡ 3)። ይህ የኃጢአተኛነት ባሕርይ ሰዎችን እግዚአብሔርን ማስደሰት የማይችሉ እደረጋቸው። እያንዳንዱ ሰው የሚያደርገውን ነገር የሚያደርገው በተበላሸው ባሕርይው ወይም በባሕርይው በሆነው ነገር ምክንያት ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ከዚህ የተበላሸ ባሕርይ ጋር እንደተወለድን ይናገራል (መዝ 51:5)። ሕፃናት ልጆች ፍጹም ናቸው የኃጢአት ባህርይም የለባቸውም ብለን ማሰብ እንፈልጋለን። ይሁን እንጂ ወንድምና እህት እርስ በርሳቸው ሲጣሉ ስንመለከት ራስ ወዳድነት የሰው ባሕርይ አንዱ ክፍል

መሆኑን እንገነዘባለን። አንድ ሕፃን ላለመታዘዝ የሚያደርገው ዝንባሌም ከኃጢአታዊ ባሕርይው የመነጨ ነው።

(10). ከዚህ ቀጥሎ ከተራ ቁጥር 1-5 ያሉትን ጥቅሶች ከሀ-ሠ ካሉት በኃጢአት ከተበላሸው የሰው ሕላዌ ክፍል ጋር አዛምድ።

1. የማወቅ ችሎታ
2. ሰሜት
3. የመፍቀድ ችሎታ
4. ኅሊና
5. መንፈስ (የሞተ)

ሀ. 1ጢሞ 4:2፣ ቲቶ 1:15
ለ. ሮሜ 1:28፣ 1ቆሮ 2:14፣ 2ቆሮ 4:4፣ ኤፌ 4:8
ሐ. ኤፌ 2:1፣ 5፣ ቆላ 2:13፣ 18
መ. ኤር 17:9-10፣ ኤፌ 4:19
ሠ. ሮሜ 1:28፣ 7:18-20

እነዚህ ጥቅሶች የሰው ሕላዌ ማንኛውም ክፍል በኃጢአት የተመረዘ በመሆኑ በዚህም ሁኔታ እግዚአብሔርን ለማስደሰት ምንም ሊያደርግ እስመቻሉን ያሳያሉ። ይህ ማለት እግዚአብሔር የሌለው ሰው መልካምና ደጋግ ምግባሮችን እያደርግም ወይም በእነዚህ ድርጊቶች ደስ እይሰኝም ማለት እይደለም። ይህ ማለት በመንፈሳዊ ሕይወቱ እሰካልተነቃቃ ድረስ በእግዚአብሔር ዘንድ ምሰጋና የሚያስገኝ ነገር ማድረግ እይችልም ማለት ነው። በእርሱ ዘንድ ያለው የእግዚአብሔር እምሳል ተበላሽቷል ማለት ነው።

የምንለቃየው የአዳም ኃጢአት ባስከተለብን ውጤትና ከእርሱ በተረከብነው የኃጢአት ባሕርይ ውጤት ብቻ ላይሆን፣ የራሳችን ኃጢአትም ባስከተለብን ውጤት ምክንያትም ነው። ሰነፍ ብሆንና የማልሰራ ብሆን ከዚያ የተነሳ በውጤቱ እሰቃያለሁ።

ብዙውን ጊዜ ችግር ላይ የምንወድቀው የገዛ ራሳችን ኃጢአት ባስከተለብን መዘገ ብቻ ሳይሆን፣ በሌሎች ሰዎችም የኃጢአት ውጤት የተነሳ ነው። የመንግሥት ባለሥልጣኖች የተበላሹ በሆኑባቸው አገሮች የሚኖሩ ዜጎች መልካም መንግሥት ሊያስገኝ የሚችለውን ስረክት ሊያገኙ አይችሉም። የሰካራም አባት ልጆች በአልኮል የደነዘዘ አእምሮ በሚያስከትለው ውርደት ሊጎላቆሉ ይችላሉ። በሰካራም ሾፌሮች ምክንያት ሰዎች በመኪና እደጋ ይሞታሉ። ሕብረተሰብ ለአጠቃላይ ወንጀለኞች ባስከተሉት ሽብር ይሰቃያል። ሰው ያለ እግዚአብሔር ስንኩል ነው። ወደ ዘመኑ ፍጽሜ እየተቃረብን ስንሄድ ከየትኛውም ሥፍራ እስፈሪ ሁኔታዎችን ለማየት መጠባበቅ እንችላለን። ሰመንፈስ ቅዱስ ምሪት ሐዋርያው ጳውሎስ እንደዚህ ጽፏል፦ "ነገር ግን በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንደሚመጣ ይህን አወቅ። ሰዎች ራሳቸውን የሚዉዱ ይሆናሉና፣ ገንዘብን የሚወዱ፣ ትምክህተኞች፣ ትዕቢተኞች፣ ተሳዳቢዎች፣ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፣ የማያመሰግኑ፣ ቅድስና የሌላቸው፣ ፍቅር የሌላቸው፣ እርቅን የማይሰሙ፣

ሐሜተኞች፣ ራሳቸውን የማይገዙ፣ ጨካኞች፣ መልካም የሆነውን የማይወዱ፣ ከዳተኞች፣ ችኩሎች፣ በትዕቢት የተነፉ፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፣ የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል" (2ጢሞ 3:1-5)።

(11). የኃጢአትን ውጤት በሚገባ የሚገልጸው የትኛው መግለጫ ነው?

ሀ. ዛሬ የምንሰቃየው በአዳም ኃጢአትና እኛም በወረስነው የኃጢአተኛነት ባሕርይ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ሰዎች የኃጢአት ውጤትም ጭምር ነው።
ለ. አያንዳንዱ ሰው የሚሰቃየው የራሱ ኃጢአት ባስከተለው ውጤት ነው፣ የአንድ ሰው ኃጢአት ግን በሌሎች ሰዎች ሕይወት ላይ ምንም ለውጥ አያመጣም።
ሐ. ሰዎች በትምህርት እየተራቀቁ በሚሄዱበት በመጨረሻው ዘመን ኃጢአት የሚያስከትለው ውጤት እየቀነሰ ይሄዳል።

በሥጋዊ አካል ላይ የደረሰ ጉዳት

በኤደን ገነት በነበሩት በአዳምና ሔዋን ዘንድ በሽታና ሕመም ያልታወቁ ነበሩ። ጀርሞች፣ ቫይረሶችና የተሰያዩ ሕመሞች ሊታዩ የቻሉት ከኃጢአት የተነሳ ሲሆን ከዚያም በኋላ ከኃጢአትና ከፍርድ ጋር ስመያያዝ (ዘጸ 15:26፣ ዘዳ 28:58-82) መታየት ቀጥለዋል። የሕመም ስሜት፣ የጉልበት መዛልና የጤና ቀውስ በኃጢአት ምክንያት የተጀመረው ሂደት ክፍል ሲሆኑ ይህም የኋላ ኋላ ወደ ሥጋዊ ሞት የሚያመራ ነው (ዘፍ 3:16-19)። እንዲያውም ከሰው ውድቀት የተነሳ ሞት የሰው ልጅን እያጨደው ነው። የኑሮ ሂደትም ሰው ወደ እግዚአብሔር ለመድረስ፣ ለእርሱ ክብር ለመኖርና እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት የሚያደርገው ጥረት (ዘፍ 3:15) በሰይጣን ተቃውሞ መስተጓጎሉ እየታወቀ መጥቷል።

በጠላትነት የተሞላ አካባቢ

ኃጢአት ባስከተለው እርግማን ምክንያት መላው ዓለም ይሰቃያል (ዘፍ 3:17-18)። እንስሳዊ ሕይወት የእውሬነትን ባህርይ ያሳያል። ኢሳ 11:8-9 በመጪው የእግዚአብሔር መንግሥት የዱር እንሰሳት አራዊት ከመሆን ይልቅ ሰላማዊ እንደሚሆኑ ያመለክታል። ይህ ሁኔታ በየጥሻው ዛሬ የምንመለከተው ሥርዓት ማለትም ኃይለኛው ደካማውን ማደኑና በፍጥረት ውሰጥ ያለው ሕብረት መናጋቱ የኃጢአት ውጤት እንደ ሆነ እናያለን።

የእጽዋት ሕይወትም ኃጢአት ያስከተለውን ውጤት ያሳየናል። እረሞችና ኩርንችቶች ጥሩውን ተክል ያቀጭጫሉ። ከእካባቢው ምግብ ለማግኘት ሰው የሚያደርገው ትግል በሥጋው ላይ ከፍተኛ ጫና ያሳድርበታል። ሐዋርያው ጳውሎስ እንዲህ ሲል ይገልጸዋል።

"የፍጥረት ናፍቆት የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ ይጠባበቃልና. . . ተስፋውም ፍጥረት ራሱ ደግሞ ከጥፋት ባርነት ነጻነት ወጥቶ ለእግዚአብሔር ልጆች ወደሚሆን ክብር ነፃነት እንዲደርስ ነው። ፍጥረት ሁሉ እስከ አሁን ድረስ አብሮ በመቃተትና በምጥ መኖሩን እናውቃለንና" (ሮሜ 8:19-22)

ዘላለማዊ የሆነ መለየትና ቅጣት

ልንመለከተው ያሰው የኃጢአት የመጨረሻ ውጤት ከሁሉም ይልቅ አሳዛኙ ነው። ንስሐ የማይገባው ኃጢአተኛ በዘላለም ቅጣት እንደሚሰቃይ መጽሐፍ ቅዱስ ይገልጻል።

(12). እያንዳንዱን ጥቅስ አንብበህ በሰ ዘላለም ሞት ምን እንደሚያመለክቱ ግለጽ።

ሀ. ማቴ 25:41	ሐ. ሮሜ 2:8-9	ሠ. ራእ 14:10-11
ለ. ማር 9:48	መ. ይሁዳ 13	ረ.

የመጽሐፍ ቅዱስ መጻሕፍት ጸሐፊዎች ይህንን ቅጣት አስመልክተው አንዳንድ ጊዜ ጥፋት ብለው እንደገለጹት ብናገኝም ቅጣቱ ግን ለዘላለም የሚዘልቅ ነው (መዝ 52:5፣ 2ተሰ 1:6-9 ተመልከት)። በማቴ 25:46 መንግሥተ ሰማያትንና ገሃነመ እሳትን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለ "ዘላለም" የሚለው ያው አንድ ቃል እንደሆነ ልብ አድርግ። ሰዎች ኃጢአታቸውን ካልተናዘዙና ለኃጢአት ችግራቸው መፍትሔ ካላገኙ ከእግዚአብሔር ፊት ርቀው ለዘላለም ቅጣት ይሰቃያሉ።

የኃጢአተኛው መቃጸል

ዓላማ 5 ኃጢአተኛው እንዴት እንደሚመለስና የመታደሱ ውጤች ምን እንደሆኑ የሚያስረዱትን መግለጫዎች መምረጥ

በተስፋ መቁረጥ መካከል የተስፋ ጭላንጭል ብልጭ ይላል። እግዚአብሔር በቸርነቱ መንፈሳዊ ሞት ካለከተላቸው ውጤቶች ነፃ የምንሆንበትን ማም ሰጫ አዘጋጅቷል። ቸር ሰጦታውን ለሚቀበሉ ሁሉ በእርሱ ፊት ዘላለማዊ ክብርን የሚቀበሉበትን መንገድ አዘጋጅቷል። እንተና እኔ በመንፈሳዊና በሥጋዊ አቋማችን መታደስ እንችላለን ኃጢአትም ያስከተላቸው ውጤቶች ሊደመሰሱ ይችላሉ።

መንፈሳዊ ተሐድሶ

ለኃጢአታችን ቤዛ በሆነ በእንድ ልጁ በኢየሱስ ሞት በኩል እግዚአብሔር ለሰው መንፈሳዊ ተሐድሶ የሚያስፈልገውን አድርጓል።

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና። ዓለም በልጁ እንዲድን ነው እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ወደ ዓለም አልላከውምና" (ዮሐ 3:16-17)።

አንተና እኔ ኃጢአታችንን ከተናዘዝንና ኃጢአትን ሁሉ እርግፍ አድርገን ለመተው ከወሰንን መንፈሳዊ ተሐድሶን የመቀበል ዕድል አለን። ይሁን እንጂ የእግዚአብሔርን የደኅንነት ግብዣ መቀበልና እርሱም ሊረዳን የገባልን ተስፋ የኛም እንደሆነ አድርገን መቁጠር ይገባናል። ይህንን ለማድረግ የእምነት እርምጃ መውሰድን ይጠይቃል፤ መጽሐፍ ቅዱስ "አጋው በእምነት አድናአችኋልና፤ . . . " (ኤፌ 2:8) ይላል። ከእኛ የሚጠየቀው የመጨረሻው ነገር "ኢየሱስ ጌታ እንደሆነ" (ሮሜ 10:9) በአፋችን መመስከር ነው። በእርሱ በናምን፣ ኃጢአታችንን ሰንናዘዝና ሰንተው እንዲሁም ኢየሱስ የሕይወታችን ጌታ እንዲሆን ሰንፈቅድለት እንሰወጣለን። መንፈሳዊ ሕይወት እንቀበላለን (ኤፌ 2:1-9፤ ቆላ 2:13) በክርስቶስም አዲስ ፍጥረት እንሆናለን "ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል" (2ቆሮ 5:17)። ሐዋርያው አማኞች አሮጌውን ሰው አውልቀን እንድንጥልና እርሱን የሚያከብር አዲስ ሰው እድርን እግዚአብሔር ዳግመኛ እንዲፈጥረን እንድንፈቅድለት ይመክረናል (ኤፌ 4:17-28፤ ቆላ 3:1-17)።

ጌታችን በሞቱ የኃጢአታችንን ዕዳ ከፈለ፤ እግዚአብሔርም በእኛ ላይ ለነበረው የጽድቅ ቁጣ አጥጋቢ ምላሽ ሰጠ፤ በእርሱ በኩል ጻድቃን ሆነናል፤ ይቅርታን አሰገኝቶልናል፤ ነፃና ሙሉ መቤዠትም አንናጽፎናል። አዲስ ፍጥረት እንድንሆንም አድርጎናል። እንደዚህ የተሰላሸ ባህርይ ይዘን ብንወለድም እንኳን በቅዱሱ የእግዚአብሔር ቤተሰብ ውስጥ ልጆች ተብለን እንድንቆጠር አስችሎናል። ከዚህም በተጨማሪ የእግዚአብሔር ልጅነትን ክብር እንድናገኝና የእግዚአብሔርም ርስት ወራሾች እንድንሆን (ሮሜ 8:17) አስችሎናል። ጌታችን ለእኛ መንፈሳዊ ተሐድሶ እነዚህን ሁሉ ዝግጅቶች ማድረግ ብቻ ሳይሆን ሁሉን ቻይ ዳኛ ምሕረት እንዲያደርግልን የሚጠይቅና የሚማልድልን አማላጃችን፤ የጥብቅና አገልግሎትም የሚሰጠን ነው (ዕብ 7:25፤ 1ዮሐ 2:1)።

ከደኅንነት ሰጦታ ጋር አዲሱ አማኝ መፈጸም የሚገባቸው ልዩ ልዩ ኃላፊነቶች አሉ። "በብርሃን መመላለስ" አሰበት (1ዮሐ 1:7፤ ዮሐ 1:4-9)። ክርስቲያን በዚህ ሕይወት ወደ ፍጹምነት ጨርሶ ባይደርስም በብርሃን ሊመላለስና ለብርሃንም ምላሽ መስጠት ይችላል። ይህንን በሚያደርግበት ጊዜ ሁለት ነገሮች ይሆናሉ። 1) ከሌሎች አማኞች ጋር ኅብረት ይኖረዋል 2) ይነጻል። መንጻት የሚከናወነው አማኙ መንፈስ ቅዱስ ውድቀቱን፣ የተሳሳቱ አመለካከቶቹን ወይም ማንኛውም ዓይነት ኃጢአቶቹን እንዲገ ልጽለት ሲፈቅድለት ነው። እነዚህን ኃጢአቶች በመናዘዝ መቀጠል ይኖር በታል፤ በመንፈስ ቅዱስ ቁጥጥር ሥር መኖር እስከቀጠለ ድረስ (ሮሜ 8:5) ወደ ፊት የሚያጋጥሙትን ፈተናዎች ለመቋቋም መወሰን አለበት።

(13). ይህንን የጥናት ክፍል መሠረት በማድረግ ኢየሱስ በመሥዋዕትነት ሞቱ ለእኛ ያከናወናቸውን ሦስት ነገሮች በማስታወሻ ደብተርህ ግለጸቸው።

አካላዊ ተሐድሶ

ኢየሱስ ያደረገልን ስለመንፈሳዊ ተሐድሶ የሚሆነውን ብቻ አይደለም፣ የመስቀል ላይ ሞቱ ለአካላዊ ተሐድሶ የሚሆነውንም አከናውኖልናል። የእርግማኑ አንድ ክፍል የሆነው በሽታ ክርስቶስ በመስቀል ከተቀበለው ስቃይ የተነሳ በሰዎች ልጆች ላይ የነበረውን ሥልጣን አጥቷል። ኢየሱስ ካስገኛቸው ተሐድሶዎች አንዱ ክፍል ፈውስ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል። በመጽሐፍ ቅዱስ አጅግ ውብ ከሆኑት አገላለጾች አንደኛው ኢየሱስ ካስገኘልን ፈውስ ጋር ተያይዞ የተገለጸ ነው።

> "በእርግጥ እርሱ ደዌያችንን ወስዶ ሕመማችንንም ተሸከመ፣ እኛ ግን በእግዚአብሔር እንደ ተመታ፣ እንደ ተቀሠፈ፣ እንደተሰቃየም ቆጠርነው። ነገር ግን እርሱ ስለመተላለፋችን ተወጋ፣ ስለ በደላችንም ደቀቀ፣ በእርሱ ላይ የወደቀው ቅጣት ለእኛ ሰላም አመጣልን፣ በእርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን" (ኢሳ 53:4-5)።

(14). የሚከተሉትን ጥቅሶች አውጣና እያንዳንዳቸው ስለ መለኮታዊ ፈውስ የሚናገሩትን ግለጽ።

ሀ. ማቴ 8:17 ለ. 1ጴጥ 2:24

በምድር ስሰዎች ሁሉ ሲሰጥ በነበረው የአገልግሎት ወቅት ሁሉ ኢየሱስ አጅግ ብዙ በሽተኞችን ፈውሷል። የእግዚአብሔርን መንግሥት ወንጌል እንዲሰብኩና በሽተኞችን እንዲፈወሱ ለላካቸው ተከታዮቹ፣ ይህንኑ መመሪያ ሰጥቶአቸዋል (ማቴ 10:7-8፣ ማር 16:18፣ ሉቃ 9:1-2፣ 10:9)።

ኢየሱስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ የፈውስ ታምራቶች በተከታዮቹ መከናወን ቀጥሎው ነበር። የሐዋርያት ሥራ መጽሐፍ በፈውስ ታምራቶች የተሞላ ነው። ከዚህም ሰተጨማሪ የቤተክርስቲያን ሽማግሌዎች ሰበሽተኞች መጸለይና እግዚአብሔርም እንዲፈውሳቸው መጠበቅ እንደሚገባቸው ያዕቆብ አስተምሯል (ያዕ 5:14)። ይህ አባባል እኛ ሕይወት እንዲበዛልን ስለ መምጣቱ ኢየሱስ ከተናገረው (ዮሐ 10:10) ጋር ይስማማል።

ዓለም ከሕመምና ከስቃይ ገና ነፃ አልሆነችም፣ ሆኖም በቤተክርስቲያን ታሪክ በሙሉ ያለው ምስክርነት በኢየሱስ የሚታመኑ የእምነት ጸሎት ምላሽ የሆነውን ፈውስ ማግኘት እንደሚችሉ ነው። ስለሆነም ጌታችን በቀራንዮ መስቀል ከፈጸመው የተነሳ መንፈሳዊ፣ አካላዊና ዘላለማዊ በረከቶችን ለመለማመድ ችለናል። በአዳም በኩል ኃጢአት ወደ ሰው ልጆች ዘር ገባ፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከኃጢአትና ከሚያስከትላቸው ውጤቶቹ ነጻ ሆነናል። ስለ ስጠን ታላቅ የደኅንነት ስጦታ ከልባችን ምሥጋና እናቅርብለት!

(15). መንፈሳዊና አካላዊ ተሐድሶአችንን በሚመለከት እውነት ከሆኑ መግለጫዎች አንጻር ያሉትን ፊደሎች ክበባቸው።

ሀ. የመንፈሳዊ ተሃድሶ አጅግ አስፈላጊ የሆነው ገጽታ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረን ሕብረት መመለሱ ነው።
ለ. የኛ ኃጢአት ምትክ በመሆን ኢየሱስ በመስቀል ላይ በመሞቱ የሰው ልጅ አሁን ከኃጢአት ቅጣት ነጻ ነው።
ሐ. መንፈሳዊ ተሐድሶ ንስሐ መግባትን፣ ከኃጢአት መመለስንና በብርሃን መመላለስን ይጠይቃል።
መ. በሽታ ከመርገም አንዱ ክፍል በመሆኑ ልንቀበለው የሚገባን የሕይወት ገጽታ ነው።
ሠ. መለኮታዊ ፈውስን ለማግኘት የሚጠይቀው አምነት ነው።
ረ. በብርሃን መመላለስ ከኃጢአት መንጻትንና ከሌሎች አማኞች ጋር ሕብረት ማድረግን ያስከትላል።
ሰ. ከአዲስ ኪዳን ዘመን ጀምሮ እስከ ዛሬ ከቁጥር በላይ የሆኑ ለዎች መለኮታዊ ፈውስን ተለማምደዋል።
ሸ. መለኮታዊ ፈውስን ለማግኘት ብቸኛው አስፈላጊ ነገር የቤተክርስቲያን ሽማግሌ ጸሎት ነው።
ቀ. አዳም በሰው ልጆች ላይ ያስከተለው ማንኛውም ውጤት ክርስቶስ በመስቀል ላይ በከፈለው ቤዛነት ሞት ተሸንፏል።

ይህ የክፍል 2 የመጨረሻው ትምህርት ነው። የሙከራ ፈተናውን ካጠናቀቅህ በኋላ ክፍለ ትምህርት 5፣ 6 እና 7ን ከልሳቸው።

የሙከራ ፈተና

አጫጭር መልሶች፡-የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች አጠናቃቸው።

1. በሰው ልጆች ዘንድ የኃጢአት መጀመሪያ ከ ኃጢአት ጋር ሊያያዝ ይችላል።

2. በዓለም ላይ የኃጢአት እጀማመር ከ ዓመጽ ጋር ሊያያዝ ይችላል።

3. የኃጢአት እውንነት ሁለት ማረጋገጫዎች ናቸው።

4. ለኃጢአተኛው መታደስ አስፈላጊ የሆኑት እርምጃዎች ናቸው።

5. እጅግ አሳዛኙና ትልቅ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው የኃጢአት ውጤት ነው።

እውነት-ሐሰት መግለጫው እውነት ከሆነ "እ" ሐሰት ከሆነ "ሐ" ብልህ ጻፍ።

6. ሰይጣን መጀመሪያ ኃጢአት ባያደርግ ኖሮ ለው ኃጢአት ሊያደርግ የሚችልበት ሁኔታ አይኖርም ነበር።

7. ሰው ኃጢአታዊ ባህርይ ስላለው ሕጎች አስፈላጊ ናቸው።

8. ሰው በራሱ ባሕርይ እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት እንደማይችል መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ማስረጃዎችን ይሰጠናል።

9. ከመጽሐፍ ቅዱስ በምናገኘው መረጃ መሠረት ትዕቢትና ራስ ወዳድነት ሰስይጣን ውድቀት አስተዋጽኦ አድርገዋል።

10. በዛሬው ዘመን ሰይጣን በዓለም ላይ ያለው ስልት ከእግዚአብሔር ፕሮግራም ጋር ሙሉ በሙሉ ተቃራኒ የሆነ ፕሮግራም ማካሄድ ነው።

11. ሔዋን ፍሬውን መብላቷ ኅጢአታዊ ድርጊት የሆነው ፍሬው እንዳይበላ በእግዚአሔር በመከልከሉ ብቻ ነው።

12. ኃጢአት በለው ልጆች ዘንድ ስለገባ ሰው ሙት ከሆነ መንፈሳዊ ባሕርይ ጋር ተወልዷል።

የጥናት ማጠናከሪያ ጥያቄዎች መልስ

8. የምትሰጠው መልስ እነዚህን ሃሳቦች ማካተት ይገባዋል፡- እግዚአብሔር ሰው ራሱ እርሱን ለማገልገል የመምረጥ ችሎታን ሰሰው ለመሰጠት ፈቀደ። ይህ እደራረግ ምርጫ ማድረግ ይቻል ዘንድ ፈተና መሰጠትን አስፈላጊ አደረገው። የመጀመሪያዎቹ አባትና እናታችን አዳምና ሔዋን ወደ እግዚአብሔር ከማዘንበል ይልቅ የራስ ወዳድነት ፍላጎታቸውን መከተል መረጡ። በሕጉ ላይ በማመጽ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት በመፈጸማቸው እኛ የእነርሱን የኃጢአት ባሕርይ ወረስን። አዳምና ሔዋን ለፈጸሙት ለሀጥት ዋጋ እንደሚከፍሉ እያወቁ ሆን ብለው በበጎነትና በክፋት መካከል የግል ምርጫቸውን በማድረጋቸው የእግዚአብሔር ቅጣት ተገቢ ነበር።

1. እግዚአብሔርን አለመታዘዙ።

9. ሀ. 3 ሐ. 2 ሠ. 4
ለ. 5 መ. 1

2. አዲሱ ትውልድ በእግዚአብሔር ፊት ከፋትን አደረገ።

10. ሀ 4 ሐ. 5 ሠ. 3
ለ. 1 መ. 2

3. እስራኤላውያን ደጋግመው በእግዚአብሔር ፊት ክፋትን አደረጉ።

11. ሀ

4. ኃጢአት ዓመጽና ከእግዚአብሔር ሕግጋት ጋር ለመስማማት አለመቻል ነው። ሰዎች ያለአግባብ የሚያደርጉዋቸው ነገሮች ሁሉ ኃጢአት ናቸው።

12. ሀ. እርጉማን ከዲያቢሉስና ከመላእክቱ ጋር ዘላለማዊ አላትን ይካፈላሉ።
ለ. ቅጣቱን የሚቀበሉት ትሉ ወደ ማይሞትበት እሳቱም ወደ ማይጠፋበት ወደ ሲኦል ይጣላሉ።
ሐ. ክፋትን በሚያደርጉ ላይ መቅሰፍትና ቁጣ፣ ችግርና ጭንቀት ይሆንባቸዋል።
መ. ዘላለማዊ ቅጣት ድቅድቅ ጨለማንም ያካትታል።
ሠ. እግዚአብሔርን የሚቃወሙ በእሳት ዲን ይሰቃያሉ፣ ሌትና ቀን እረፍት የላቸውም።

5. የምትሰጠው መልስ እነዚህን ሃሳቦች የሚያካትት ሊሆን ይችላል። መጽሐፍ ቅዱስ በአዳም፣ በሔዋንና በቃየን በመጀመርና ከዚያም

በእስራኤል መንግሥት ተደጋግሞ የተፈጸሙትን ኃጢአቶች በመጥቀስ ስለ ኃጢአት እውንነት ታሪካዊ መረጃዎችን ያቀርባል። አዲስ ኪዳን በክርስቶስ ኢየሱስ እግዚአብሔር ለኃጢአት ስርየት ያደረገውን ይዘግባል፤ ብዙ የኃጢአት ምሳሌዎችንም ይሰጣል። ራሳቸውን እንዲያስተዳድሩ የተተዉ ሰዎች ራስ ወዳድና አመጸኛ ስለሆኑ በየትኛውም የዓለም ክፍል የመንግሥት መቋቋም አስፈላጊነት ይታያል።

13. ከሚከተሉት ሃሳቦች የትኞቹም መልስ መሆን ይችላሉ። እግዚአብሔር በኃጢአት ላይ ስነበረው ቁጣ ምላሽ ሰጥቶአል፤ የኃጢአታችንን ዕዳ ከፍሎልናል፤ ጻድቃን አደረገን፤ ይቅርታ አስገኘልን፤ ሙሉና ነፃ መቤገርት አስገኘልን። አዲስ ፍጥረት መሆንን ሰጠን፤ የእግዚአብሔር ልጆችና ወራሾች አደረገን። በእግዚአብሔር ፊት ይማልድልናል። ለእያንዳንዱ ቀን ኑሮአችን ብርሃን ይሰጠናል።

6. ሀ. ሐሰት ሐ. እውነት ሠ. እውነት
   ለ. ሐሰት መ. እውነት

14. ሀ. እርሱ ድካማችንን ተቀበለ ደዌያችንንም ተሸከመ።
    ለ. በመገረፉ ቁስል ተፈወስችሁ።

7. ሀ. እንዲሞት ተፈረደበት
   ለ. ሞት

15. ሀ. እውነት መ. ሐሰት ሰ. እውነት
    ለ. ሐሰት ሠ. እውነት ሸ. ሐሰት
    ሐ. እውነት ረ. እውነት ቀ. እውነት

8 ቅዱሳት መጻሕፍት
የእግዚአብሔር የጽሑፍ መገለጫ

ትምህርት

ቀደም ባሉት ትምህርቶች ስስ እግዚአብሔርና ስለ ስው ማንነት፣ ስለ ኃጢአት አጀማመርና ምንነት፣ ስለ መላእክትና አሰራራቸው እንደዚሁም በኃጢአት ለወደቀው የስው ልጅ እግዚአብሔር ሰላዘጋጀው የመቤገርት እቅድ ብዙ እውነቶችን ተምረናል። ለእነዚህ መሠረታዊ የእምነት ትምህርቶች ሁሉ ዓቢይ ምንጭ የሆነው መጽሐፍ ቅዱስ እንደሆነ በእርግጥ አስተውለሃል። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ስለ ራሱና ስለ ፍጥረቱ የሰጠው የጽሑፍ መገለጥ ነው።

ሉአላዊ፣ አፍቃሪ፣ ጻድቅና አካላዊነት ያለው እግዚአብሔር ማመዛዘን ለሚችሉ ፍጥረቱ በጽሑፍ በቀረበው ቃሉ አማካይነት ራሱን መግለጽ ይፈልጋል ብሎ ማመን ምክንያታዊ ነው። ለፈቃዱ የሚገዙ ለዎችን የእግዚአብሔርን ቃል ስብአዊ ጸሐፊዎች ይሆኑ ዘንድ መምረጡን ማስተዋል የከበረ ነገር ነው። ለ1600 ዓመታት ገደማ 40 የሚያህሉ ስዎች የጻፏቸው መጻሕፍት በመለኮታዊ ኃይል እንዴት እንደተጠበቁና በመጽሐፍ ቅዱሳችን እንዴት እንደተካተቱ ስለሚገልጸው እውነት ማጥናት የሚያነቃቃ ነው።

የክፍል ሦስት (ትምህርት 8-10) ጥናታችንን ስንጀምር በቅድሚያ በእግዚአብሔር ቃል ላይ እንደስፈረው የእግዚአብሔርን የመዋጀት ዓላማ በሚመለከት ያለውን መገለጥ እንመለከታለን። በሁስተኛ ደረጃ መጽሐፍ ቅዱስ በእርግጥም የእግዚአብሔር ቅዱስ ቃል ስመሆኑ ማረጋገጫ የሚስጡንን መረጃዎች እንከልሳለን። ከዚያም በኋላ ያልዳኑ ስዎችን ወደ እግዚአብሔር ስለ ምትጠራው፣ የእምነት አንክብካቤ ስለ ምታደርግላቸውና ውጤታማ ምስክሮች እንዲሆኑ ስስ ምታደርጋቸው የእግዚአብሔር ተቋም ለለ ቤተ ክርስቲያን በቅርብ እንከታተላለን። በመጨረሻም የቤዛነታችን ግብ የሆነውን የፍጻሜ ዘመን ጉዳይን እንመለከታለን።

የክፍለ ትምህርቱ አከፋፈል

- በጽሑፍ የቀረበ መገለጥ አስፈላጊነት
- የእግዚአብሔር ቃል በመንፈስ ቅዱስ ምሪት መጻፍ
- የእግዚአብሔር ቃል ልዩ መሆን
- የእግዚአብሔር ቃል አፈታት
- የእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን